**ጅማ ዩኒቨርሲቲ**

**የድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት**

**የአማርኛ ቋንቋና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል**

# በጂማ ዞን በሰኮሩ ወረዳ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በአማረኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት / Attitude/ ትንተና

**በ**

**ኢዮብ ፀጋዬ**

ነሐሴ 2010

ጅማ ኢትዮጵያ

**ጅማ ዩኒቨርሲቲ**

**የድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት**

**የአማርኛ ቋንቋና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል**

በጂማ ዞን በሰኮሩ ወረዳ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በአማረኛ ትምህርት ቋንቋ ላይ ያላቸው አመለካከት / Attitude/

**በ**

**ኢዮብ ፀጋዬ**

**ዋና አማካሪ**

**ዶ/ር ጌታቸው አንተነህ**

በኢትዮጵያ  ቋንቋዎች ና ስነ-ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር የአርት ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ትልመ ጥናት

ነሐሴ 2010

ጅማ ኢትዮጵያ

ማውጫ ገጽ


1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2 የጥናቱ አነሣሽ ምክኒያት ........ 2

1.3 መሪ ጥያቄዎች ........ 2

1.4 የጥናቱ ዓላማ ........ 3

1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 5

1.7 የቃላትና የሐረጎች ትርጉም /በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በገቡበት ሁኔታ/ ........ 5

ምዕራፍ ሁለት ........ 7

ክለሳ ድርሳን ........ 7

2.1. የአማርኛ ቋንቋ ........ 7

2.1.1. የአማርኛ ዕድገት ........ 7

2.1.2. የአማርኛ ተናጋሪዎች ........ 9

2.1.3. አማርኛ በትምህርት ቤት ........ 9

2.1.4. አማርኛ አሁን ያለበት ሁኔታ ........ 9

2.1.5. ፖለቲካዊ ገጽታዎች በአማረኛ ቋንቋ ላይ ........ 10

2.3. የተማሪው አዎንታዊና አሉታዊ አመለካከት አፈጣጠር ........ 15

2.4. ቋንቋና የቋንቋን ትምህርት አስመልክቶ በተማሪው አመለካከት ላይ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ነገሮች ........ 17

2.4.1. የእኩዮች /Preers/ ተጽዕኖ ........ 17

2.4.3. መማሪያ መጻህፍት በተማሪው አመለካከት ላይ የሚኖራቸው ሚና ........ 20

2.4.4. ትምህርት ቤቶች፣ መማሪያ ክፍሎች፣ ድጋፍ ሰጪ ነገሮችና ዘዴዎች ........ 22

2.5. አማርኛንና የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት አስመልክቶ የተደረጉ የአመለካከት ጥናቶች፣ ........ 22

ምዕራፍ ሦስት ........ 26

3. የጥናቱ ዘዴ ........ 26

3.1. የናሙናዎች አመራረጥ ስልት ........ 26

3.1.1. በጥናቱ የሚካተቱ ተማሪዎች ........ 26

3.1.2. በጥናቱ የሚካተቱ መምህራን ........ 27

3.1.3. በጥናቱ የሚካተቱ ትምህርት ቤቶች ........ 27

3.3.1 የጽሁፍ መጠይቅ ........ 29

3.3.2 ቃለመጠይቅ ........ 29

3.4 የመጠይቁ ስርጭት ........ 29

3.3.3 ምልከታ ........ 30

3.5 የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ........ 30

ምዕራፍ አራት ........ 32

4.1. የመላሾች አጠቃላይ ሁኔታ ........ 32

4.1.1. ጾታ ........ 32

4.1.2. ዕድሜ ........ 32

4.1.3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ........ 32

4.1.5. የአባቶችና የእናቶች የትምህርት ደረጃና የስራ ሁኔታ ........ 33

4.2. የመረጃዎች ስሌታዊ አሰራር ........ 35

4.3. ከእያንዳንዱ ጥያቄ የተገኘ ምላሽ ........ 36

4.3.1. የተማሪዎች ግላዊ አመለካከት ........ 36

4.4. የአማርኛ ቋንቋ መምህር ጠባይ፣ ችሎታና አመለካከት ........ 41

4.5 የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት ሁኔታ ........ 45

4.8. የተማሪዎች አስተያየት ........ 57

4.9. የምላሾች ንጽጽር ........ 60

4.10 የተላውጠዎች ተጣምሮ ........ 63

4.11 ቃለመይቃዊ መልሶች ........ 64

4.12 ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች ንፅፅር ........ 68

4.13 የምልከታ ሪፖርት ........ 70

4.14 የምልከታ ውጤትና የተማሪዎች ምላሽ ንፅፅር ........ 70
ምዕራፍ አምስት ........ 72
5. አጠቃሎ፣ ግኝትና አስተያየት ........ 72
5.1 አጠቃሎ ........ 72
5.2 ግኝት ........ 74
5.3 አስተያየት ........ 76
ዋቢ መፃህፍት ........ 79
አባሪዎች ........ 82

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

አንድ ተማሪ በሚማረው የቋንቋ ትምህርትና በቋንቋውም ላይ ቀና አመለካከት፣ እንዲሁም የመማር ፍላጎት እንዲኖረው ያስፈልጋል፤ (ታይገማን(2009) ብሩምፌት (2010)፤ እና ዱቢን (2009)፡፡ በቋንቋው ትምህርትና ልምምድ ውስጥ ወሳኝ ነገሮች የመማር ፍላጎትና አዎንታዊ አመለካት ናቸው ይላሉ፡፡ አንድ የቋንቋ ተማሪ አመለካከቱ አሉታዊ ከሆነ ቋንቋውን ከልብ አይማርም፡፡ እንዲያውም ከራሱ አለመማር አልፎ ለሌሎች ወደው ለሚማሩትም ተማሪዎች እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ አዎንታዊ አለመለካከት ያለው ተማሪ በንቃት ይማራል፤ ጥሩ ውጤትም ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም የቋንቋ ተማሪዎች ሁሉ ስለሚማሩት ቋንቋና በቋንቋው ትምህርት ላይ አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ የተማሪዎችን አመለካከት አሉታዊ ሊያደርጉ የሚችሉት ነገሮች አጥንቶ የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ ከላይ የጠቀስናቸው ምሁራን፣ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ለማዘጋጀትና ሌሎች ትምህርታዊ ግብዓቶችን ለማደራጀት በቅድሚያ ተማሪዎችና ሌሎች የሚመለከታቸው ሁሉ አመለካከታቸው መጠናት እንዳለበት ያስረዳሉ ፋርጉሰን (2010)፡፡

ይሁንና የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለከት የተማሪዎች ፍላጎትና አመለካከት ሳይጠና የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶችና መማሪያ መጻህፍት እስካሁን ድረስ ሲዘጋጅ ቆይተዋል፡፡ ይህ ደግሞ የቋንቋው ትምህርት የሚፈለገውን አላማ እንዳይመታ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡ ማውንት ፎርድና ማከይ (2009)፣ ትክክለኛ የቋንቋ ኮርስ ለማዘጋጀት በሙሉ የሚመለከታቸውን ሰዎች በግልጽ ማነጋገር ተገቢ እንደሆነ ይጠቅሳል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ውጤቱ ብላሽ እንደሚሆን ይናገራሉ፡፡ እደገና ፋርጉሰን (2010፣ 5) "በኢትዮጵያና በሌሎችም ቦታዎች ብዙ መረሐ-ግብሮች የሚከሽፉት የተመሰረቱለትን ህዝብ አመለካከት ግምት ውስጥ ስለማያስገቡ ነው" በማለት በኢትዮጵያ የአመለካከት ጥናት ትኩረት እንዳልተደረገላቸው ትምህርቶች (2009) መግቢያ ላይ "የመርሐ ትምህርቱ አዘገጃጀት በጥናት ላይ ያልተመሰረተ መሆኑ ግልጽ ነው" በማለት ያቀረቡ ሀሳብ የፈርጉሰንን ሀሳብ የሚደግፍ ነው፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው በአገራችን የአመለካከት ጥናት (Attitude Survey) ከትምህርት መሳሪያዎች ዝግጅት በፊት አለመደረጉ አንደኛው ትልቅ ጉድለት ሲሆን መሳሪያዎች ስራ

ላይ ከዋሉ በኋላም ተማሪዎች ስለመሳሪያዎቹ ያላቸውን አመለካከት አጥንቶ ማሻሻያዎችን ለማቅረብ አለመሞከሩ ደግሞ ሁለተኛው ጉድለት ነው፡፡

ስለዚህ ይህ ትልመ ጥናት ለወደፊቱ ያገለገል ዘንድ የተማሪዎችን ፍላጎትና አመለካከት አጥንቶ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ለማቅረብ ያለመ ሲሆን በመምህራን፤ በተማሪዎችናበትምህርት ቤቶች የሚገኙ መርጃ መሳሪያዎች አንጻር የሚታዩ ክፍተቶችን በጥናት በመለየት አስፈላጊውን የመፍትሔ ሀሳብ የጠቆመ ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሣሽ ምክኒያት

ከላይ ስለ ጥናቱ መነሻ ሀሳብ ስንገልጽ በአገራችን የተማሪዎች ፍላጎትና አመለካከት ሳይጠና የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት መማሪያ መጻህፍት ይዘጋጃሉ ብለናል፡፡ የዚህ ጥናት ውጤት ደግሞ፣ የተማሪዎችን ፍላጎትና አመለካከት፣ በአማርኛ ትምህርት ላይ የሚታዩትን ችግችና ተማሪዎች ከመምህራን የሚጠብቁትን ሁሉ ማንፀባረቅ እስከቻሉ ድረስ የሚመለከታቸው ወገኖች ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ በመሰረቱ በአንድ አገር ውስጥ የሚደረጉ ጥናቶች በተገቢ ሰዎች እጅ ገብተው በአግባቡ ስራ ላይ መዋል ይኖርባቸዋል፡፡ አጥኚው በምሰራበት ትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪዎች በአማረኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ የሚያሳዩት፤ በክፍለግዜ አለመገኘት፤ መልመጃዎችን አለመስራት ና ደካማ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ዲርጊቶች ስለሆኑና በፋርጉሰን (2010) “በኢትዮጵያና በሌሎችም ቦታዎች ብዙ መረሐ-ግብሮች የሚከሽፉት የተመሰረቱለትን ህዝብ አመለካከት ግምት ውስጥ ስለማያስገቡ ነው” በሚለው ጥናት ውስጥ፤ አጥኚው ከልምድ ካያቸው ጉዳዮች በተጨማሪ በፋርጉሰን የተደረገው ጥናት የአጥኚውን የልምድ እይታ ስለሚያጠናክሩ ጥናቱን ለማካሂድ አጥኚው በመነሳሳት ለማጥናት ተችሏል፡፡ በዚህ ረገድ ካሮል (2011፣ 275) “የቋንቋ ጥናት ውጤት ተጠቃሚዎች የመምህራን አሰልጣኞች፣ የትምህርት ፖሊሲ አውጪዎችና የትምህርት መሳሪያ አዘጋጆች ናቸው” ይላል፡፡

## 1.3 መሪ ጥያቄዎች

ይህ ትልመ ጥናት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች ለመመለስ ያለመ ነው፡፡

- አማርኛ ቋንቋና የቋንቋው ትምህርት በተማሪዎች ዘንድ ያለው ተቀባይነቱ ምን ያህል ነው ?

- የተማሪው እኩዮች ስለ አማርኛና ስለተማሪው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎት ያላቸውን  አመለካከት ምን ይመስላል ?
- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በስልጠናቸው፣ በትምህርት አቀራረባቸውና በጠባያቸው ቋንቋውን ለማስተማር የሚገኙበት ሁኔታ ምን ይመስላል ?
- የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ከተማሪዎች ፍላጎት አኳያ ምን ያህል ተቀባይነት አለው?
- ትምህርት ቤቶች፣ መማሪያ ክፍሎች፣ ድጋፍ ሰጪ ነገሮችና የማስተማር ዘዴዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ምቹ ናቸው?

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

### 1.4.1 የጥናቱ ዋና አላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላም በሰኮሩ ና በደነባ ከተማ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በአማረኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸውን አመለካከት / Attitude/ መመርመር ነው፡፡

### 1.4.2 የዚህ ጥናት ዝርዝር ዓላማዎች፡-

- አማርኛ ቋንቋና የቋንቋው ትምህርት በተማሪዎች ዘንድ ተቀባይነቱ ምን ያህል እንደሆነ ተመርምሯል፤
- የተማሪው እኩዮች ስለ አማርኛና ስለተማሪው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎት ያላቸውን አመለካከት ተተንትኖል፤
- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በስልጠናቸው፣ በትምህርት አቀራረባቸው ፣ የተማሪዎችን ፍላጎት ለመቀስቀስ ያላቸውን አቅም ተተንትኖል፤
- የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ከተማሪዎች ፍላጎት አኳያ ያላቸውን ተቀባይነት ተመርምሯል፤

- ትምህርት ቤቶች፣ መማሪያ ክፍሎች፣ ድጋፍ ሰጪ ነገሮችና የማስተማር ዘዴዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ምቹ መሆን አለመሆናቸውን ተመርምሯል

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ መሰረት የሚያደርገው ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋና በአማርኛ ትምህርት ላይ ያላቸውን አመለካከት መመርመርና የመፍትሄ ሀሳብ መፈለግ ይሆናል፡፡

ጥናቱ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

1. መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚኖራቸውን አመለካከት ለማወቅና አሉታዊ አመለካከቶች ካሉ ምንምን እርምጃዎችን መውሰድ እንዳለባቸው የሚያመላክቱ የመፍትሄ ሀሳቦችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

2. ተማሪዎች አንድን ውጤታማ ስራ ለመስራት አመለካከት አስፈላጊ እንደሆነ ግንዛቤ ሊሰጥ ይችላል

3. በዚህ  ርእስ ዙሪያ ወደፊት ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ አጥኚዎች እንደመነሻ ሊያገለግል ይችላል፡፡

በካሮል ሀሳብ መሰረት የዚህ ጥናት ውጤት ግንባር ቀደም ተጠቃሚ ትምህርት ሚኒስቴር ሲሆን በሶስት የተለያዩ መንገዶች ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ እነሱም፡-

- የአማርኛ መርሐ ትምህርቶችና መማሪያ መጻህፍት ከተማሪዎች ፍላጎት አኳያ እንዲሻሻል በማድረግ፣

- በመምህራን ስልጠና ላይ ከተማሪዎች አመለካከት አኳያ ጠቃሚ የሆኑ ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች እንዲተኮርባቸው በማድረግ፣

- ትምህርት ቤቶች፣ መማሪያ ክፍሎች፣ እንዲሁም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጋዥ ነገሮች ከተማሪዎች አመለካከትና ፍላጎት አኳያ እንዲደራጁ በማድረግ ነው፡፡

ሌሎች የዚህ ጥናት ውጤት ተጠቃሚዎ ደግሞ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የሚያሰለጥኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ሲሆን የጥናቱን ውጤትና የአጥኚውን አስተያየቶች በትምህርታቸው ውስጥ በማካተት የተሻሉ መምህራን ሊያፈሩ ይችላሉ፡፡

ስለዚህ ጥናቱ ከላይ የተዘረዘሩትን ጠቀሜታዎች ሁሉ የሚያስገኝ በመሆኑ በዚህ ወቅት መከናወኑ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በጂማ ዞን በሰኮሩ ወረዳ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ሲሆን የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶች በጥናቱ አልታቀፉም፡፡ በወረዳው 38 ቀበሌዎች ሲኖሩት አብዛኛዎቹ የገጠራማ አካባቢዎች የአማረኛ ቋንቋ የማይዘወተርባቸው በመሆኑ ለጥናቱ ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ሲባል ሁለት የከተማነት ባህሪይ ያላቸውን ት/ቤትች በጥናቱ እንዲካተቱ በአጥኚው ተመረጠዋል፡፡ ትምህርት ቤቶቹ፡- የሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና የደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በጥናቱ ውስጥ የሚካተቱ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡

በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ካሉት ተማሪዎችም የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለናሙና ተመርጠው መጠይቁን እንዲሞሉ የሚደረግ ሲሆን፣ ፣ ቃለመጠይቃዊ መረጃ እንዲሰጡ የሚመረጡት ደግሞ በትምህርት ቤቶች የሚገኙት የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተጠሪዎችና የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ይሆናሉ፡፡ የናሙና አመራረጥንና አጠቃላይ መግለጫን በተመለከተ በምዕራፍ ሶስት ውስጥ በዝርዝር ቀርቧል፡፡

## 1.7 የቃላትና የሐረጎች ትርጉም /በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በገቡበት ሁኔታ/

1. አመለካከለት፡- አንድ ሰው ስለ አንድ ነገር የሚኖረው ቀና ወይም ቀና ያልሆነ ውስጣዊ አስተሳሰብ ነው፡፡
2. ግላዊ አመለካከት፡- አንድ ሰው በአንድ ወቅት የሚኖረው የራሱ ብቻ የሆነ ውስጣዊ አስተሳሰብ ነው፡፡
3. አዎንታዊ አመለካከት፡- አንድን ነገር የመውደድ፣ የመቀበል፣ የመደገፍ፣ ወዘተ. ዝንባሌ ነው፡፡
4. አሉታ አመለካከት፡- አንድን ነገር የመቃወም፣ የመጥላት፣ የመንቀፍ፣ ወዘተ. ዝንባሌ ነው፡፡
5. ህብረተሰብ፡- ተማሪው በሚመላለስበት ክልል ውስጥ የሚገኙ የቅርብም ሆነ የሩቅ ነዋሪ ሰዎች ናቸው፡፡ /ቃሉ ሰፋ ተደርጎ ሲታይ ልማድ፣ ወግ፣ እምነትና የመሳሰሉትንም ያቅፋል/

6. እኩዮች(ብጤ)፡- ከተማሪው ጋር በዕድሜ የሚመጣጠኑና አብረውት የሚመላለሱ የክፍል ውስጥ ወይም ከክፍል ውጭ ያሉ ጓደኞች ናቸው፡፡

7. ታላሚ ቋንቋ፡- ተማሪው እንዲማረውና እንዲያውቀው የሚፈለግ ቋንቋ ነው፡፡

8. ድጋፍ ሰጪ፡- በዋው የትምህርት መሳሪያ ላይ ተጨማሪ ሆኖ የሚቀርብ አጋዥ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳን

## 2.1. የአማርኛ ቋንቋ

አማርኛ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ኢትዮሲማዊ ቋንቋዎች አንዱ ሲሆን በሴም ቋንቋነቱ ከዐረብኛ ቀጥሎ ብዙ ተናጋሪዎች ያሉት ቋንቋ ነው፡፡ ቋንቋው ከረጅ ዓመታት በፊት የኢትዮጵ ኦፊሴላዊ ቋንቋ ሆኖ ማገልገል የጀመረና ዛሬም የአገሪቱ ማዕከላዊ መንግስት የስራ ቋንቋ ሆኖ በማገልገል ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ይህ ቋንቋ እንዴት እንዳደገ፣ ተናጋሪዎቹ እነማን እንደሆኑ፣ በትምህርት ቤት መሰጠት የተጀመረው መቼ እንደሆነ፣ አሁን ያለበትን ሁኔታና ፖለቲካዊ ገጽታዎችን አጠር አጠር ባለ መልክ ተመልክተናል፡፡

### 2.1.1. የአማርኛ ዕድገት

አማርኛ መነገር የተጀመረበትን ጊዜ በትክክል መናገር ባይቻልም፣ ሴማዊ ዝርያዎ ሁሉ የዛሬ ሶስት ሺህ ዓመታት ገደማ በሰሜን በኩል ወደ ኢትዮጵያ የገቡ መሆኑን ሀብተማርያም ማርቆስ (2009) ይገልፃል፡፡ አማርኛ ከአስራ ሶስተኛው ክፍለ ዘመን በፊት የነበረው ታሪክ ከመላምት ያላለፈ ሲሆን፣ በአጼ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግስት (1270) በስፋት ማገልገል የጀመረና ልሳነ መንግስታዊ ደረጃ የነበረው መሆኑን የሚገልጹ ታሪካዊ መረጃዎች ተገኝተዋል (አምሳሉ አክሊሉ 1976)፡፡

በአስራ አራተኛውና በአስራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን በተለይም በአጼ አምደጽንና በይስሐቅ ዘመን ቋንቋው ዕድገቱን አፋጥኖ ወደ ጽሁፍ ደረጃ ሊሸጋገር ችሏል፡፡ ለዚህ ማስረጃው በተጠቀሱት ዘመናት ስለሁለቱ ነገስታት በግጥም የቀረቡት ጽሁፎች ናቸው፡፡ ግጥሞቹ እነ ዮናስ አድማሱ ባዘጋጁ መጽሐፍ (1966) በገጽ 118 እና 119 ላይ ይገኛሉ፡፡

በዘመናችን ያለውን አማርኛ ካለፉት ዘመናት ጋር ሲነፃፀር ብዙ ልዩነቶች ይታዩባቸዋል፡፡ የበፊቱ አማርኛ ከሌሎች የሴም ቋንቋዎች ጋር በጣም የሚቀራረብ ሲሆን የዘመኑ አማርኛ ግን ራቅ ብሏል፡፡ ለዚህ አንዱ ምክንያት አማርኛ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት የኩሽ ቋንቋዎች በርካታ ቃላትንና የአገላለጽ ስርዓቶችን በመውሰድ መሆኑን ሌስላወው (1945) ይገልፃል፡፡ ሌላው ምክንያት አማርኛ የነገስታትና የትምህርት ቋንቋ በመሆን ያገኘውን አጋጣሚ በመጠቀም ከተለያዩ የውጭ ቋንቋዎች የተለተያዩ ቃላትን በተውሶ በማስገባቱና

ከራሱ ጋር በማቀላቀሉ ሲሆን ውሰቱን በተመለከተ አብሃም ደሞዝ (1963) በስፋት ይገልፃል፡፡ ዘመን አልፎ ዘመን፣ ትውልድ አልፎ ትውልድ ሲተካ ቋንቋ ቀስ በቀስ መልኩን እየቀየረ ይሄዳል፡፡ እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተደማምረው አማርኛ ከበፊቱ እንዲቀየርና አደግ ብሎ እንዲገኝ አድርገውታል፡፡ ለአማርኛ ቋንቋ ዕድገት አስተዋጽኦ ያደረጉት ነገሮች በርካታ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የከተሞች መስፋፋት (ማክናብ 2012፤ ኩፐር 2014)፣ ይህ ማለት የተለያዩ ብሔረሰቦች በአንድ አካባቢ ተሰባስበው መኖር ሲጀምሩ አማርኛ የጋራ መግባቢያ /Lingua Franca/ ሆኖ ማገልገል በመጀመሩ እያደገ ሄደ፡፡

- የመንግስትና የሚሽን ትምህርት ቤቶች መስፋፋት፣ ቀድም ብለው የተቋቋሙት ትምህርት ቤቶች አማርኛን እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ሲሰጡ ቆይተው ወዲያውኑ ከነጻነት በኋላ የአንደኛና የሁለተኛ ክፍሎች የትምህርት ቋንቋ፣ ትንሽ ቆይቶ በመላው ኢትዮጵያ የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ አድርገው በመጠቀማቸው ለአማርኛ ዕድገት በጣም ረድተዋል፤ በተለይ የተለያዩ ማሽኔሪዎች በርካታ ትምህርት ቤቶችን በገጠር በማስፋፋታቸው አማርኛ ለመማርና ለመናገር አጋጣሚ ያልነበራቸው ብዙ የኢትዮጵያ ህዝቦች ቋንቋውን ለመማርና ለመናገር ችለዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ አማርኛ በተወላጅነት ከሚናገሩት ህዝቦች ውጭ ወደሆኑት ብሔር ብሔረሰቦች ዘልቆ የመግባትና የመስፋፋት ዕድል አግኝቷል፡፡ /ቤንደር 2009፤ ደሴ ሙሉዓለም 1972 ዓ.ም፤ ማክናብ 2011/፡፡ የሁሉም በላይ ለረጅም ጊዜ ኦፊሴላዊ ቋንቋ ሆኖ በመገናኛ ብዙሃን፣ በማህበራዊ አገልግሎት፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ይዞ በመገኘቱ ለአማርኛ ቋንቋ ዕድገት የረዳ ትልቅ ጉዳይ ነው፡፡

## 2.1.2. የአማርኛ ተናጋሪዎች

አማርኛ ከብሔረሰብ ማደግና መስፋፋት፣ ብሎም ወደ ስልጣን መምጣት ጋር ቀስ በቀስ ወደ ደቡብና ወደ ሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ሁሉ እየተስፋፋ ሄዶ የአገሪቱ ማህበራዊ ቋንቋ ሆኗል፡፡ ይህንን አስመልክቶ የቋንቋ ጥናት ኢንስቲትዩት በ1975 ባወጣው አትሙ ላይ "የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ማነው?" የሚለው ጥያቄ አማራጭ የሚል መልስ ብቻ እንደ ማናገኝና ከአማራው ክልል ውጭ በተለያዩ ከተሞች ውስጥ የሚኖሩ ብሔር ብሔረሰቦችና የተማሩና ወገኖች ሁሉ የሚገለገሉበት የኢትዮጵያውያ ቋንቋ እንደሆነ አቅርቧል፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ አማርኛን በአፍ መፍቻነት የሚናገሩት 55.4% ሲሆኑ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚናገሩት 44.6% መሆናቸውን ማክና (2009) ትገልጻለች፡፡

## 2.1.3. አማርኛ በትምህርት ቤት

አማርኛ በትምህርት ቤት ውስጥ የጎላ እንቅስቃሴ ማድረግ የጀመረው በ1908 የዳግማዊ ምሊኒክ ትምህርት ቤት ከተከፈተ ወዲህ ነው፡፡ በዚህ ትምህርት ቤት አማርኛ እንደ አንድ የትምህርት አይነት መስጠት የጀመረ ሲሆን፣ ከዚያ በኋላ የተቋቋሙት የመንግስትም ሆኑ የሚሽን ትምህርት ቤቶች ሁሉ አማርኛን እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ይሰጡ ጀመር /ቤንደር 2011/

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት ከተጀመረ ጀምሮ እስከ ኢጣሊያ ወረራ ድረስ ፈረንሳይኛ የትምህርት ቋንቋ ሆኖ ከቆየ በኋላ፣ በ1941 ጀምሮ እንግሊዝኛ ቦታውን በመውሰድ ለሶስተኛና ከዚያ በላይ ካሉት ክፍሎች ሁሉ በትምህርት ቋንቋነት ማገልገል ሲጀምር፣ አማርኛ ለአንደኛና ለሁለተኛ ክፍሎች የትምህርት ቋንቋ ሆኖ ማገልገል ጀመረ፡፡ 1953 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ አማርኛ የትምህርት ቋንቋነቱ ለኢትዮጵያ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሁሉ ሆነ፡፡

## 2.1.4. አማርኛ አሁን ያለበት ሁኔታ

አማርኛ በ1987 ዓ.ም ለህዝብ ውይይት በቀረበው ረቂቅ ህገ መንግስት አማካይነት የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት የስራ ቋንቋ እንዲሆን በመመረጡ የኢትዮጵ ፌደራላዊ መንግስት የስራ ቋንቋ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡

አማርኛ ለኢትዮጵያ ህዝቦች የስራ ቋንቋ ከመሆን ጎን በአማራ ክልል ና በፌድራል ከተሞች ለሚኖር ህዝብ የዕለት ተዕለት ተግባር ማከናወኛ ዋነኛ ቋንቋ፣ እንዲሁም የመንግስቶቻቸውን የስራ ቋንቋ ነው፡፡ ደቡብ ህዝቦች ተብለው በአንድ መስተዳደር ስር የተጠቃሉ ብሔር ብሔረሰቦች፣ ብሎም የጋምቤላና የቤነሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህዝቦች አማርኛን የክልላቸውን መንግስት የስራ ቋንቋ አድርገው በመጠቀም ላይ ይገኛሉ፡፡

አማርኛ በሁሉም የኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቤቶች ከአራተኛ ክፍል ጀምሮ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት የሚሰጥ ሲሆን፣ በአማራ ክልል ና በፌድራል ከተሞች ግን ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ከመሰጠት አልፎ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ የትምህርት ቋንቋ ሆኖ እንዲያገለግል ተወስኗል፡፡ (የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ረቂቅ 1985)፡፡

አማርና በመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ዘርፍ ከጥንት ጀምሮ ሲያገለግል የቆየና አሁንም ቢሆን ከፍተኛውን ድርሻ ይዞ የሚገኝ ቋንቋ ነው፡፡ በጽሁፍ እንቅስቃሴዎች አኳያም ሲታይ በልዩ ልዩ ልቦለድና ምንባባዊ ጽሁፎች የደረጀ ነው፡፡

አማርኛ በአሁኑ ጊዜ ለበርካታ የውጭ ቃላትና ሀረጎች ተተኪ ያሉት፣ ከዘመናዊ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር ራሱን ያቀራረበ፣ በአንፃራዊ መልክ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ቋንቋዎች ሁሉ በተሻለ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ፣ ብዙ ተጠቃሚዎች ያሉት ቋንቋ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከፖለቲካዊ ገጽታዎች አኳያ ያሉበትን ችግሮች ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 2.1.5. ፖለቲካዊ ገጽታዎች በአማረኛ ቋንቋ ላይ

ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ መልኩ በአማርኛ ቋንቋ ላይ ጥላቻ ያላቸው የተወሰኑ ብሔር ብሔረሰቦች አሉ፡፡ የጥላቻው ታሪክ የተነሳው ከአጼ ምኒሊክ ዘመነ መንግስት ጀምሮ ነው ይባላል፡፡ አጼ ምኒልክ ወታደራዊ ወረራን ተጠቅመው ግዛታቸውን ወደ ደቡብ፣ ወደ ምዕራብና ምስራቅ ባስፋፉበት ወቅት፣ በነፍጥ ኃይል ሌሎቹን ብሔረሰቦች ካስገባሯቸው ወታደሮች አብዛኛዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ነበሩ፡፡ በዚህ ምክንያት "ነፍጠኞችን" የጠሉት ብሔር ብሔረሰቦች አማርኛ ቋንቋንም ከነፍጥ ጋር አያይዘው ጠሉት፣ "የጨቋኞች ቋንቋ" ብለው ጠሩት፡፡ አንደርሰን (2009) በኢትዮጵያ፣ የጌሳ ቋንቋ ተጠቃሚዎች በአማርኛ

ቋንቋ ላይ ዝቅተኛ አመለካከት እንዳላቸው አረጋግጧል፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢም ከገጠመኙ እንደሚያስታውሰው፣ በኢትዮጵያ ወታደራዊ ደርግ ስልጣን ከያዘ በኋላ፣ በተለይ በ1969 ዓ.ም አካባቢ በተወሰኑ ቦታዎች፣ ብሔር ብሔረሰቦች አማርኛን እንደማይፈልጉ የሚገልጹ ጽሁፎች ይበተኑ ነበር፤ ገልጻዎችም ይደረጉ ነበር፡፡ ይህ ቅስቀሳ ወደ ትምህርት ቤቶችም ዘልቆ፣ ተማሪዎች "አማርኛን አንማርም፣ የአማርኛ መምህራን ይውጡ" ብለው መፈክር ያሰሙበትና ግርግር የፈጠሩበት ሁኔታ ነበር፡፡

ዛሬም ቢሆን በአንዳንድ ክልሎች፣ በአማርኛ ቋንቋ ላይ አሉታዊ አመለካከት ካላቸው ብሔር ብሔረሰቦች የውጤት ተማሪዎች ከወላጆቻቸውና ከጓደኞቻቸው ባገኙት ልምድ መሰረት በአማርኛ ቋንቋና በትምህርቱም ላይ የጥላቻ ስሜት እንደሚያንጸባርቁ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስለ አማርኛ ቋንቋ ይህን ያህል ግንዛቤ ካገኘን ቀጥለን ስለአመለካከት አጠቃላይ ባህሪያት፣ ስለተማሪው አዎንታዊና አሉታዊ አመለካከት አፈጣጠር፣ እንዲሁም በተማሪ አመለካት ላይ ተጽዕኖ ስለሚያደርጉት ነገሮች እንመለከታለን፡፡

አመለካከት በትምህርት የሚገኝ በተለያዩ ሰዎች ወይም ሁኔታዎች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የአስተሳሰብ ሁኔታ ነው፡፡ ዐጉናስ (1976፣407) "አመለካከት በቀጣይነት የሚቀስም በተወሰነ የመነሳሳት (Stimuli) ደረጃ ላይ የሚታይ የማሰብ፣ የማድረግ፣ ወይም የውስጣዊ ስሜት (feeling) ሁኔታ ነው" ይላል፡፡ ውሉድስውስኪ (1985፣46) "አመለካከት በትምህርት ይቀስማል፤ በልምድ ሂደት፣ በቀጥታ ትምህርት ፣ በመምህርና ተማሪ ግንኙነት፣ በልጅና ወላጅ ግንኙነት በአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት፣ ወዘተ. ይዳብራል" ይላል፡፡

እንግዲህ እነዚህን ሀሳቦች በቀላሉ ቋንቋ ስናጠቃልል፣ አመለካከት በአዎንታዊነትም (positive) ሆነ በአሉታዊነት (Negative) ከአካባቢ በትምህርት የሚቀስም፣ በልምድ ሂደትና በተለያዩ ግንኙነቶች የሚዳብር፣ የተወሰነ ደረጃ ያለው የማሰብና የማድረግ ውስጣዊ ስሜት ነው፡፡

አመለካከትን ከሁኔታዎች አካሄድ ገምተን "እንዲህ ሊሆን ይችላል" እንላለን እንጂ በዓይን አይታይም፡፡ ሆኖም በንቃት ከተጠራቀመ ገጠመኝ፣ ከቃላዊ ሪፖርት፣ ከጥቅል ጠባይና ከተፈጥሯዊ አሰራር ምልክቶች ሊታወቅ ይችላል፡፡

የአመለካከት ጽንሰ ሀሳብ የሚመነጨው በግለሰብ ጠባይ ውስጥ ከሚታይ ስርዓት መሆኑንና የአንድ ሰው የአመለካከት ጥራት የሚዳኘው በዓይን ከሚታይ እንዲሁም ግለሰቡ ለግምገማ ከሚሰጠው ምላሽ መሆኑን የባሪታኒካው ኢንሳይክሎፒዲያ (1986) እና ሽሪፍ (2008) ይናገራሉ፡፡

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ፍላጎትና አመለካከት አስፈላጊ መሆናቸውን በርካታ ጠበብት ይናገራሉ፡፡ በዚህ መሰረት ታይዳማን (2011)፣ ብሩምፊት (2012)፣ አነጀነሲ (2009)፣ ዴቢን (2013) በቋንቋ ትምህርትና ልምምድ ውስጥ ወሳኝ ነገሮች ፍላጎትና አዎንታዊ አመለካከት መሆናቸውንና፣ በቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ጥሩ ውጤት ሊያመጡ እንደሚችሉ ተናግረዋል፡፡

እፖለስኪ (2013) በቋንቋ ትምህርት ላይ ዋነኛው ጉዳይ ተማሪው ለቋንቋውና ለቋንቋው ተናጋሪዎች የሚኖረው አመለካከት መሆኑን ከገለጸ በኋላ የተማሪው የጎሰኝነት አመለካከትና ስለ ሌሎች ቡድኖችም ያለው አመለካከት የቋንቋውን ትምህርት ውጤት ትምህርትን ጠቅሶ ይቀርባል፡፡

አመለካከት ከማንነታችን የማይለይና ወሳኝ መሆኑን ውሌድ ከዊስኪ (2014) እንደሚከለተው ይገልፃል፡፡ "አመለካከት በአስደናቂ ሁኔታ ሰዎችን ያንቀሳቅሳል፡፡ የማንኛውም ሰው ህይወት በአመለካከት ዙሪያ ትኖናለች፤ አመለካት ሁል ጊዜ ከኛ ጋር ሆኖ በቋሚነት በጠባያችንና በትምህርታችን ላይ ተጽእኖ ያደርጋል፡፡"

አመለካከትና ሌሎች ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች በትምህርት ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ቀላል እንዳልሆነ ከተለያዩ ምሁነራን ጥናታዊ ጽሁፎች ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ አመለካከትና መነቃቃት (Motivation) ለአስተዋይነትና (Intelligence) ጥቅል ዕውቀት (atitude) ልዩነት ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ቋንቋ ትምህርት ላይ ስነ ልቦናዊ ሁኔታ የሚያሳድሩት ተጽእኖ ቀላል እንዳልሆነ ግንዛቤ ተገኝቷል፡፡ (አልፍሬድ 2009፤ ሌትልውድ 2012፤ ፔይ 2009

ክላውዝማየርና ጎድዊን (2009) "… ጥሩ ስሜቶች፣ ድልና ሽልማቶች፣ ምቹና ጥሩ ዕድሜ ወዳለው አዎንታዊ አመለካከት ሲወስዱ፣ በአንፃሩ ደግሞ ውድቀትና ቅጣቶች መጥፎ ወደ ሆነው አሉታዊ አመለካከት ይወስዳሉ፡፡" ይላሉ፡፡

አመለካከት ስሜታዊነትና ተገቢነት /Sociablility/ በትምህርት ቤት በትምህርትነት መቅረብ ገና ባይጀምሩም በጣም በርካታ ጥናታዊ ጽሁፎች ተማሪዎች እነዚህን ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች በትምህርት ቤት መማር እንዳለባቸው ይጠቁማሉ፡፡

ስለዚህ በቋንቋ ትምህርት አመራር ላይ የተሳተፉ ማንኛውም ሰው ተማሪዎች ከሚማሩት ነገሮች አመለካከት አንዱ ሆኖ እንዲቀርብ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ማወቅ አለበት፡፡ (ስታይንሳክ 2009፤ ኦልራይት 2013፤ ፔይን 2014)፡፡

በትምህርት ቤት ተማሪዎች መማር የሚገባቸው የአመለካት ዓይነቶች የሚከተሉት መሆናቸውን ክላውዝማየርና ጎድዊን (2014) ይገልጻሉ፡፡

- ናሙና የሚሆኑ ምሳሌዎችን፣
- ቀና ውስጣዊ ስሜት እንዲያድርባቸው የሚያደርግ፣
- መረጃ የመስጠትን ልምድ የሚያጎለብት፣
- ጥሩ ስልቶችን መጠቀም የሚያስችል፣
- ትክክለኛውን ልምድ ማቀነባበር የሚያስችል፣
- ነፃ አመለካከታቸው እንዲበለጽግ የሚያደፋፈር፡፡

በነዚሁ በነክላውዝማየር (2014) አገላለጽ በትምህርት ቤቶች ከሚገባዩትና በጣም ጠቃሚ ከሆኑት ነገሮች አመለካከትና ዋጋ “Value” ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች ተማሪው መስተጋብራዊ ሁኔታዎችንና ሌሎች የሚፈልጋቸውን ነገሮች እንዴት ተነጋግሮ ማግኘት እንዳለበት ያመለክታሉ፡፡

አመለካከት ውስጣዊ ስሜት ሁኖ ለረጅም ጊዜ በሰዎች ጠባይ ላይ ተጽዕኖ በማድረግ ኃይሉን መግለጽ የሚችል ነው፡፡ በተመሳሳይ መልክ አንድ ሰው ለአንድ ነገር መነቃቃት አለመነቃቃት ከአመለካከቱ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ቻስቴይን (2013) “ከፍተኛ ፍላጎት፣ ዝግጅት፣ ተሳትፎና ትምህርት የመቅሰም ብቃት በስጣዊ የመነቃቃት ባህሪይ ይወሰናሉ” ይላል፡፡

እንደ ኤላይ (2009) አገላለጽ ደግሞ ጥሩ የቋንቋ ትምህርት እንዲካሄድ መነቃቃት፣ አጠቃላይ ዕውቀት፣ ውጤት መሻትና የክፍል ተሳትፎ አስፈላጊ ሲሆኑ፣ በክፍል ተሳትፎ ላይ ተጽዕኖ ከሚያደርጉት በርካታ ነጥቦች አንዱ አመለካከት ነው፡፡

ማህበራዊ ሁኔታ አመለካትን ይወስናል፤ አመለካከት ወደ መነቃቃት ያመራል፤ የመነቃቃት ሁኔታ ትምህርቱ በጥሩ ወይም በመጥፎ ሁኔታ እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡

ስፓሊስኪ (2014)፣ አመለካከት በመማር ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ የሚያደርግ ሳይሆን ተጽዕኖ ሊያመጣ ወደሚችለው መነቃቃት የሚወስድ መሆኑን ይናገራል፡፡ ፒምዝሌር (2012) ይህንን ሀሳብ ሲጠናከር "መነቃቃት ሁለት ዋና ጉዳዮችን ያቅፋል፤ ኃይለኛነትና አሳቢነት፡፡ አሳቢነት ብዙ ጊዜ ተማሪዎች ለመማር ካላቸው ዋና ዓላማና ግብ ጋር ተያዞ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ደግሞ ለአመለካከት ጋር በጣም የተቆራኘ ነው፡፡" ይላል፡፡ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሀሳብ በካንንግስ ዎርዝ (2011) እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*መነቃቃት ለቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ ድርሻ አለው በጥሩ ሁኔታ የተነቃቃ ወይም ጥሩ አመለካከት ያለው ተማሪ ጥሩ ውጤት ሲኖው በመጥፎ ሁኔታ የተነቃቃ ተማሪ ወይም አመለካከት የተበላሸ ተማሪ ውጤቱ የማይረባ ይሆናል፡፡*

ካንንግስ ዎርዝ ስለመነቃቃት ጠቃሚነት ሀሳቡን ሰፋ በማድረግ "… በጥሩ ሁኔታ የተነቃቃ ተማሪ ሆኖ በመጥፎ ሁኔታ እንኳን ቢማር፣ በጥሩ ሁኔታ ተምሮ በጥሩ ሁኔታ ካልተነቃቃው ተማሪ የተሻለ ውጤት ይመረጣል" ይላል፡፡ (2012) አመለካከት ግትርና ቋሚ ሳይሆን እንደሁኔታው ሊሻሻልና ሊቀየር የሚችል መሆኑን ውላድስ ዊስኪ (2014) እና ፔይን (2010) ይናገራሉ፡፡ ስለዚህ አንድ ተማሪ በቋንቋ ትምህርት ላይ የሚያንፀባርቀው አሉታዊ አመለካከት በልዩ ልዩ የአቀራረብ ስልት ወደ አውንታዊነት ሊቀየር ይችላል፡፡ ዊልጋ (2012) የውጭ ቋንቋ ትምህርትን ከማስተዋወቃችን ወይም ከመጀመራችን በፊት ተማሪዎቹ ስለዚህ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት፣ በዚያን ወቅት ቋንቋውን መማር ለምን እንዳስፈለገንና ከቋንቋው ትምህርት የሚያስገኙት ጥቅም በቅድሚያ መታወቅ እንዳለበት ትናገራለች፡፡ ዊልጋ ለውጭ ቋንቋ ትምህርት ትኩረት ሰጥታ ትናገር እንጂ ጽንሰ ሀሳቡ ለሁሉም የቋንቋዎች ይሰራል፡፡ ጹቤን (2013) "ማንኛውም የቋንቋ ትምህርት ከመከናወኑ በፊት ማህበረሰቡና ተማሪው ስለ ቋንቋው ያላቸው አመለካከት በጥራትና በጥልቀት መጠናት አለበት" ትላለች፡፡ ከዚህ ጋር በጣም ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ማክይና ማውንት

(2012) ጥሩ የቋንቋ ኮርስ ለማዘጋጀት በቅድሚያ ከሚመለከታቸው ሰዎች ጋር መደበኛ ግንኙነት ማድረግ ተገቢ መሆኑን ይጠቁሙናል፣ ይህ ካልሆነ ውጤቱ ብላሽ እንደሚሆን ያሰምሩበታል፡፡ ስለዚህ ከማንኛውም የቋንቋ ትምህርት በፊት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ህብረተሰቡና የትምህርት ባለሙያዎች አመለካከታቸው መጠናት አለበት፡፡

## 2.3. የተማሪው አዎንታዊና አሉታዊ አመለካከት አፈጣጠር

በመጀመሪያና በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ በተማሪዎ መሀል የአቀባበል ደረጃ ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ ይህን በተመለከተ ስፓሊስኪ (2014) የሚከተለውን አስፍሯል፡፡

*የመጀመሪያ ቋንቋን በተመለከተ ማንኛውም ጤነኛ ሰው ቢያንስ እስከ መግባባት ደረጃ ድረስ ችሎታ ይኖረዋል፡፡ የሁለተኛ ቋንቋን በተመለከ ግን ምንም ከማይችሉ እስከ ከፍተኛ ችሎታ ድረስ ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ በነዚህ የትምህርት አቀባበል ልዩነቶ ተፅዕኖ የሚያደርጉት ነገሮች የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ፣ ዕድሜ፣ አጠቃላይ ዕውቀትና አመለካከት ናቸው፡፡*

በስፓሊስኬ አገላለጽ በቋንቋ ትምህርት አቀባበል ላይ ተጽዕኖ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ አመለካከት መሆኑን እንረዳለን፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ቻስቴይን (2012) "ተማሪዎች ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በሚመጡበት ጊዜ የተለያዩ አመለካከቶች ይዘው ይመጣሉ፡፡ ከነዚህ አመለካከት ጥቂቶች ለጥሩ ውጤት ትምህርቱን የሚያግዙ ቢሆኑ ጥቂቶች ደግሞ ትምህርቱን ያዳክማሉ ይላል፡፡

ተማሪዎች ስለ ትምህርቱ፣ ስለ መጻህፍቱ ስለ ክፍል ጓደኞቻቸው እንዲሁም ስለራሳቸውና ስለመምህሩም ያላቸው አመለካከት በትምህርታቸው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡ በተለይ ተማሪዎች መምህራቸውን የማይወዱትና የማያከብሩት ከሆነ ማለትም ከመምህራቸው ላይ አሉታዊ አመለካከት ካላቸው እሱ የሚጠውን ትምህርት አይከታተሉም፡፡ በዚህን ጊዜ መምህሩ በትምህርቱና በተማሪዎች መሀል ግርዶሽ ሆኖ ይቆማል ማለት ነው፡፡ (ውሎድሰኮውስኪ 2012፣ ላምበርት 2010፣ ሀርመን 2009)፡፡ ከወደዱቸው ግን አዎንታዊ አመለካከት እንደሚኖራቸው ነው፡፡

በሌላም በኩል ቻከቴይን (2014) የሚከተለውን ጽፏል፡፡

*ተማሪዎች ስለ ቋንቋው፣ ስለ ቋንቋው ተናጋሪዎችና ስለባህላቸው አዎንታዊ፣ አሉታዊ ወይም ድብልቅ አመለካከት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ለቋንቋውና ለቋንቋው ተናጋሪዎች ከፍተኛ ግምት የሚሰጡ ከሆነ የመማር ፍላጎታቸውም ከፍተኛ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ቋንቋውን ማወቅ ለወደፊቱ ትርፋማ መሆኑን ካመኑ ጊዜያቸውን ሰውተው ተግባቦታዊ (communicative) ችሎታቸውን ያዳብራሉ፤ ወደ ቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ ለመሄድ የሚማሩም ከሆነ አመለካከታቸው የበለጠ ቀናና ከፍ ያለ ይሆናል፡፡*

*በቋንቋ ላይ አዎንታዊ አመለካከት ካለ ቋንቋውና ቋንቋው ለሚወክለው ባህል አድናቆት እንዲኖር ያደርጋል፤ ደግሞም ቋንቋውን ለመማር ግላዊ ከፍተኛ መነቃቃት እንዲነሳሳ ያደርጋል፡፡ ከሁሉም በላይ ተማሪው ለቋንቋው ትምህርት በጣም የሚጓጓ ይሆናል፡፡ በቋንቋ ላይ የሚታይ ቡድናዊና ግላዊ አዎንታዊ አመለካከት በቋንቋው ትምህርት ከፍተኛ ውጤት እንዲገኝ ያደርጋል፡፡* ይህንን ሀሳብ ስፓሊስኪ (2013) ሲያጠናክር "ተማሪው ለታላሚው ቋንቋ ተናጋሪዎች አዎንታዊ አመለካከት ካለው ለቋንቋውም ትምህርት አዎንታዊ ውጤት ይኖረዋል" ይላል፡፡ በሌላም በኩል ተማሪዎች በቋንቋው ትምህርት የሚያገኙት ውጤት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡ ጥሩ ውጤት አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡ ይህንን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን በቀረቡት ሀሳብ መሰረት፡-

በቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውጤት ያመጣ ትጉህ ተማሪ ቀና አመለካከቱ ከፍ ይላል፡፡ ይህ ከፍ ያለው አመለካከት ደግሞ ሌላ ከፍተኛ ውጤት እንዲመዘገብ ምክንያት ይሆናል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ በቋንቋው ትምህርት ተደጋጋሚ ውጤቱ ደካማ የሆነ ተማሪ አሉታዊ አመለካከት ሊያድርበት ይችላል፡፡ ይህ አሉታዊ አመለካከት ደግሞ አዕምሮውን ቆልፎ ሌሎች ደካማ ውጤቶች እንዲከተሉ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ መምህራን ተማሪዎቻቸው ጥሩ ውጤት እንዲያገኙና እንዲቀሳቀሱ (motivation) የየራሳቸውን ዘዴ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ማለት ግን ተማሪዎቹ ሁሉ ጥሩ እንዲያመጡ ተብሎ ከደረጃ በታች የሆነ በጣም ቀላል ፈተና ይሰጥ ማለት አይደለም፤ በጣም ቀላል ፈተና መሆኑ ራሱ እንዳይቀሳቀሱና አሉታዊ አመለካት እንዲያድርባቸው ሊያደርግ ይችላል፡፡ (ሃርመር 2012፣ ስተርን 2014፣ ልትልውድ 2014)፡፡ የተማሪዎችን ውጤት አስመልክቶ ፣ ሃርመር (2015) "ጥሩ ውጤት ማግኘት አለማግኘት በተማሪው እጅ ቢሆንም መምህሩ በሂደቱና በአፈፃፀሙ ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል" ይላል፡፡

የተማሪው ቀደምት ልምዶችም በትምህርቱ ላይ ተጽዕኖ እንዲያደርጉበት ሃርመር (2013) እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

> *… ምናልባት ተማሪው ቀደም ሲል ይህንን ቋንቋ ተምሮ ያቋረጠ ከሆነና አሁን እንደገና እንዲማር ከተደረገ የበፊት ገጠመኙ መንፀባረቅ ይጀምራል፡፡ በፊት ሲማ ከብደት እንዶት እንደሆነ አሁን ትምህርቱን ገና ሳይጀምር "እኔ ይከብደኛል፣ አልችል" በማለት ከወዲሁ አሉታዊ አመለካከት ይዞ ትምህርቱን ይጀምራል፡፡ በአንፃሩ ደሮም የሚወደውና ጥሩ ውጤት ያስመዘገበበት ከሆነ አሁንም በአዎንታዊ አመለካከት ሊነሳሳ ይችላል፡፡*

ቻስ ቴይን (2009) "በክፍል ውስጥ ንግግርን ለመማርና ከሌሎች ጋር ለመግባብ ተማሪዎች አዎንታዊ የግል ሀሳብና የመተባበር አመለካከት ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የሌሎችን ሀሳብ ለማዳመጥና የራሳቸውንም ሀሳብና ስሜት ለመግለጽ ፍቃደኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል" ይላል፡፡

## 2.4. ቋንቋና የቋንቋን ትምህርት አስመልክቶ በተማሪው አመለካከት ላይ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ነገሮች

### 2.4.1. የእኩዮች /Preers/ *ተጽዕኖ*

በአንድ ልጅ የህይወት አቅጣጫ ላይ ድርሻ ያላቸው ነገሮች በርካታ ናቸው፡፡ ትምህርት ቤት፣ ቤተሰብ፣ ጓደኞች፣ የአካባቢ ነዋሪዎችና፣ የእምነት ሁኔታዎች አስተዋጽኦ አሏቸው፡፡ ይህን በተመለከተ ኩምብስ (2010) "… በተጨማሪነት ቤተሰብ፣ ጓደኞች፣ ቤተ ክርስቲያንና የአካባቢ ኃይሎች በየራሳቸው መንገድ የተማሪውን ህይወት ወይም ማንነት ይቀርፃሉ …" ይላል፡፡

ከቋንቋ ትምህርት አኳያም ሲታይ የተማሪው እኩዮች ተማሪው በቋንቋ ትምህርት ላይ ሊኖረው የሚችለውን አመለካከት በአንድ ወይም በሌላ መልክ ተፅዕኖ ሊያደርጉበት ይችላሉ፡፡ ስፓሊኪ (2013) ተማሪው ስለሚማረው የቋንቋ ትምህርት ከሌሎች የሚያገኘው መግለጫ የቋንቋ ትምህርት ፍላጎቱንና አመለካከቱን ከሚወሰኑት ነገሮች አንዱ መሆኑን ላምበርትን ጠቅሶ ያቀርባል፡፡ ፒኪናስ (2013) ደግሞ የሚከተለውን ጽፏል፡፡

ህፃናት ገና በጨቅላነታቸው ከወላጆቻቸው የሚያገኙት የአስተዳደግ ሁኔታ ማለትም ቁጣ፣ ጥላቻ፣ የሚደረግና የማይደረግ፣ የሚስጠላና የሚማርክ፣ ለሰዎ ስለ እንስሳት፣ ስለ ጾታ፣ ወዘተ. የሚገኙት ትምህርት፣ ተረቶችና ቀልዶች ሁሉ በልጁ የወደፊት አመለካከት ላይ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል፡፡

## 2.4.2. መምህራን በተማሪው ቋንቋ አቀባበል የሚኖራቸው ሚና

በርካታ መምህራን ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዲወዱና አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ፡፡ ስለሆነም በተለያየ መልክ ይቀስቅሳሉ፣ ይመክራሉ፣ ለማሳመን ይጥራሉ፡፡ ውሎድኮ ዊስኪ (2012) እንደሚለው እነዚህ ባዶ ቃላት ወይም ንግግር ብቻቸውን በተማሪዎች ላይ አመለካከት አያመጡም፡፡ ተማሪዎች ራሳቸው በትምህርቱ እንቅስቃሴ ተሳትፈው በመምህሩ አቀራረብና በትምህርቱም መሳብ መቻል ይኖርባቸዋል፡፡

መምህር ተማሪው በቋንቋ ትምህርት ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከት እንዲያሳድር ለማድረግ "ትልቁ ወሳኝ አካል ነው" ቢባል የተጋነነ አይሆንም፡፡ ስፓሊስኪ (2012) የመምህራን አመለካከት ለተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ወሳኝ መሆኑን የጠቀሰ ሲሆን አዜብ (2014) "የመምህሩ አመለካከት በወጣቶች ስብዕና ------- ወይም መጥፎ ተጽዕኖ ሊደርገው ይችላል" በማለት የስፓሊስኪን ሀሳብ የሚያጠናከር ሀሳብ አቅርባለች፡፡ እንደገና ዳንኤል (2015) "በቂ ዕውቀት ያለውና በደንብ የሚያስተም ዝነኛ መምህር በተማሪዎቹ ተመስጦና ተሳትፎ እንዲሁም ባህርይ ላይ ጥሩ ተጽዕኖ ያደርጋል" ይላል፡፡ ሃርመር (2015) እና ውሎድኮ ዊስኪ (2010) መምህሩ ተማሪዎችን በአቅራረቡ የሚስብና የሚማርክ፣ ስብዕናቸውን የሚጠብቅና የሚንከባከባቸው ከሆነ ተማሪዎች እንደሚወዱትና እንደሚያከብሩት ብሎም በትምህርቱ ላይ አዎንታዊ አመለካትን በማሳደር ከልብ እንደሚማሩ ይገልጹና በሌላ በኩል መምህር ነጭናጫና ተሳዳቢ፣ እንዲሁም ተደባዳ ከሆነ ተማሪዎቹ ትምህርቱን እንዲጠሉና አሉታዊ አመለካከት እንዲያድርባቸው እንደሚያደርግ ያስረዳሉ፡፡

ከላይ በተከታታይ ሀሳባቸውን የሰጡት ምሁራን ሁሉ አንድ መምህር በተማሪዎች አመለካከት ላይ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ያመለክታሉ፡፡ ስለዚህ መምህር ሙያውን አፍቃሪና ከልብ የሚሰራ፣ ሀቀኛና ተማሪዎቹን የሚወድ ጥሩ አርአያ መሆን የሚችል ሰው መሆን አለበት፡፡ ይህ ከሆነ በተማሪዎ ላይ አዎንታዊ አመለካትን ሊያሳድር ይችላል፡፡

ይህንን አስመልክቶ ሃርመር (2013) ለተማሪዎች አዎንታዊ አመለካከት ሲባል አንድ የቋንቋ መምህር ማድረግ የሌለበትንና ማድረግ የሚኖርበትን እንደሚከተለው ያቀርባል፡፡

- መምህር ሲሰድብ፣ ሲቆጣ፣ ስራውን እንደነገሩ ሲሰራ መታየት የለበትም፣
- ሳይዘጋጅ ክፍል መግባት የለበትም፣
- ወላዋይ መሆን የለበትም፣ /ለምሳሌ አርፋጆችን  አንዳንዴ ይቀበላል አንዳንዴ ያባርራል ወዘተ.../
- በቅጣት መደራደር የለበትም፣ /መምህር ኮስታራ ካልሆነ በሚል አሮጌ ፈሊጥ አካልና ስነ ልቦናን የሚጎዳ ቅጣት አለመስጠት፣
- በኃይለ ቃል መናገር ወይም ማንቧረቅ የለበትም፣
- ትምህርቱን አሰልቺ ማድረግ የለበትም፣ /በድግግሞሽ፣ ምቹ ዘዴ ባለመምረጥ፣ ወዘተ.../
- አድሏዊ መሆን የለበትም፣ /ለአንድ ተማሪ ያደረገውን ለሁሉም ማድረግ አለበት/

በአንፃሩ የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርበታል፡-

- ህጎችን ማክበርና ስብዕናውን መጠበቅ አለበት፡፡ /የማያረፍድ፣ የማይሰክር፣ የማይባልግ ወዘተ.../
- ትምህርቱ ማራኪ እንዲሆን በጣም መጣር አለበት፣
- ተማሪዎን በእኩል ዓይን የሚመለከት፣ ችግራቸውን የሚፈታና የሚያማክራቸው የቅርብ ጓደኛ መሆን አለበት፣
- በታላሚው ቋንቋ በደንብ የሚናገርና አርአያ መሆን የሚችል መሆን አለበት፣
- ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ መናገር እንዲችሉ የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅሞ ማስተማር የሚችል ዘዴኛ መሆን አለበት፡፡

### 2.4.3. መማሪያ መጻህፍት በተማሪው አመለካከት ላይ የሚኖራቸው ሚና

የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የተማሪን አመለካከት በመቀየር በኩል ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡ በመሆኑም መጻህፍት በሚዘጋጁበት ጊዜና ከመዘጋጀታቸውም በፊት የተማሪዎችን አመለካከት ጠንቅቆ ማወቅ ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህንን በማስመልከት ሙርሲያ (2010) "የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ከማዘጋጀታችን በፊት ተማሪዎቹ ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው አመለካት አዎንታዊነት ወይም አሉታዊነት መታወቅ አለበት" ትላለች፡፡ ይህችው ሴት ስለመማሪያ መጻህፍት አመለካከትን የማስቀየር ኃይል አላቸው፡፡ ስለዚህ ጥሩ መጻህፍት በአዎንታዊ መልክ ሲቀሰቅሱ መጥፎዎቹ ደግሞ በአሉታዊነት ይቀሰቅሳሉ ትላለች፡፡ መማሪያ መጻህፍት በአባሪዎች፣ በቃላት ዝርዝርና በስዕላ ስዕል ከታጀቡ የተማሪዎችን ስሜት ወደ አዎንታዊ አመለካከት እንደሚስቡና እንደሚማርኩ ሙርሲያ (2013) ትናገራለች፡፡ ካንንግ ስዎርዝ (2015) አንድ መማሪያ መጽሀፍ የቃላት ዝርዝርና ኤንዴክስ መያዝ እንደሚገባው ይናገርና "እነዚህም መምህሩና ተማሪዎች የተፈለገውን ነገር ቶሎ ብለው ማግኘት እንዲችሉ ይረዷቸዋል" ይላል፡፡ ስለዚህ አንድ መማሪያ መጽሐፍ በሚዘጋጁበት ጊዜ የቃላት ዝርዝር፣ ኢንዴክስ፣ ስዕላ ስዕሎችንና አባሪዎችን አሟልቶ መገኘት አለበት፡፡

መማሪያ መጻህፍት ከውጫዊ መልካቸውና ከቅርጻቸው ጀምረው እስከ ውስጣዊ የአፃፃፍ ስልትና ስዕላ ስዕላዊ ቅንብሮች ድረስ ጥሩ ቅርጽ የያዙና ተማሪዎችን መሳብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ ይህን አስመልክቶ ሸልደን (2012) መማሪያ መጽሀፍ አጠቃላይ ሁኔታው የሚስብ መሆን እንዳለበትና አንድ ደራሲ፣ መማሪያ መጽሀፍ ውጤታማ እንዲሆን ቅርጹ፣ የአፃፃፍ ስልቱና ስዕላዊ ቅቦቹ ሁሉ አስፈላጊ መሆናቸውን ማወቅ ተገቢው መሆኑን ይገልፃል፡፡ በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ የመማሪያ መጻህፍት ተጠቃሚዎች በቀለማት ያሸበረቀና የሚያነቃቃ መጽሀፍ እንደሚፈልጉ ፀሐፊው ይጠቅስና ደራሲያን መጽሀፍ በሚያዘጋጁበት ጊዜ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው ያብራራል፡፡ ነገር ግን በብዙ መንገዶች ከላይ የተጠቀሱት መሰረታዊ ጉዳዮች አስፈላጊውን ትኩረት እንደማያገኙና የመጽሀፍ ዋነኛ ባለቤት የሆኑት ተማሪዎችም እንደማይታወሱ ያስረዳል፡፡ በመሰረቱ ከተጠቃሚዎች ፍላጎት ውጭ የሚዘጋጅ መጽሀፍ ፋይዳ ሊኖረው አይችልም፡፡ እንዲያውም ተማሪዎች በመጽሀፉም ሆነ በትምህርቱ ላይ አሉታዊ

አመለካከት እንዲያሳድሩ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ መሰረታዊ የሆኑ መስፈርቶችን ማሟላት ይኖርበታል፡፡

በሸልደን (2014) አገላለጽ አንድ የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

- በቂ የቋንቋ ዕውቀቶችን የያዘና ተማሪዎችን በደንብ የሚመራ፣
- ለተማሪው ነፃነት ሰጥቶ የሚያሰራ፣
- ከተማሪዎች ፍላጎትና ዝንባሌ አኳያ የተዘጋጀ፣
- ከተማሪዎች የአጭርና የረጅም ጊዜ ዓላማ ጋር ተጣጥሞ የሚሄድ፣
- የቋንቋ ዘርፎችን በሚገባ አመጣጥኖ የሚይዝ፣
- ከጊዜ ጋር የተመጣጠነ፣
- የተማሪዎችን ግላዊ ስሜት የሚጠብቅና የሚማርክ፣
- ቅደም ተከተሉ የተስተካከለ፣
- በምዕራፍና በክፍለ ትምህርት የተከፋፈለ፣
- በክፍል ውስጥ የትምህርት ሂት የተመቻቸ፣
- ተማሪዎችን ለውይይትና ለችግር ፈቺነት የሚጋብዝ፡፡

አንድ የቋንቋ ተማሪ መማሪያ መጽሐፉን በግሉ ማግኘትና እንደ ልቡ መጠቀም መቻል አለበት፡፡ ካለመማሪያ መጽሀፍ የቋንቋ ትምህርት ተፈላጊውን ግብ ሊመታ አይችልምና፡፡ ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ መማያ መጻህፍት ለሁሉም ተማሪዎች በግል መዳረስ ይኖርባቸዋል፡፡

የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ለሁሉም ተማሪ ቢዳረስ መልካም ውጤት እንደሚኖው ካይሎድስ (2014) ሲጽፍ "የመጻህፍትና የሌሎች ትምህርታዊ ቁሳቁሶች ችግር ካለ የትምህርቱ ተቀባይነትና ውጤት ዝቅ ይላል፡፡ እያንዳንዱ ተማሪ በግሉ መጽሀፍ ካገኘ ግን የትምህርቱ ተቀባይነትና ውጤቱም ከፍ ይላል …" ይላል፡፡

ስለዚህ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በተማሪዎች አመለካከት ላይ ተጽዕኖ የማድረግ ኃይል ያላቸው መሆናቸው ታውቆ በዝግጅት ላይ ትኩረት ሊሰጣቸውና ለያንዳንዱ ተማሪ በግል መዳረስ መቻል ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.4.4. ትምህርት ቤቶች፣ መማሪያ ክፍሎች፣ ድጋፍ ሰጪ ነገሮችና ዘዴዎች

በተማሪው ስብዕና ቀረጻ ላይ ድርሻ ካላቸው ነገሮች ትምህርት ቤት ዋነኛና ከፍተኛ ድርሻ ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህን በተመለከተ ክምብስ (2013) "… ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከየትም ሊያገኙ የማይችሉትን ነገሮች ማቅረብ ይጠበቅበታል…" ይላል፡፡

ትምህርት ቤት ገና ሲመሰረት ቦታው ምቹ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡ ሂሪክና ሌሎች (2014) "በተቻለ መጠን ትምህርት ቤት በመኖሪያ ቤቶች አካባቢ እንጂ በንግድና በኢንዱስትሪ አካባቢ መሰራት የለበትም፤ ምክንያቱም ሁካታና ግርግር ከትምህርት ጋር አይሄድምና…" ይላሉ፡፡ እንግዲህ ከትምህርት ዓይነቶች አንዱ ቋንቋ እንደመሆኑ መጠን ተማሪው የቋንቋውን ትምህርት ለመማር የሚሄድበት ትምህርት ቤት ያልተመቻቸና በተለያየ ሁኔታዎች ተማሪውን የሚያስጠላ ከሆነ ተማሪው በትምህርት ቤቱና በትምህርቱም ላይ አሉታዊ አመለካከት ሊያሳድር ይችላል፡፡ ለምሳሌ ትምህርት ቤቶች ሽንት ቤት የሌላቸው መጫወቻ ሜዳ የጠበባቸው በርና መስኮት የወላለቁና በብርድ የሚያስመቱ ፣ ወዘተ. ከሆኑ ተማሪው ይሐላቸዋል ማለት ነው፡፡ ከዚህ ቀጥለን በአማርኛ ቋንቋ ዙሪያ የተሰሩ ቀደምት ስራዎችን እንመለከታለን፡፡

## 2.5. አማርኛንና የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት አስመልክቶ የተደረጉ የአመለካከት ጥናቶች፣

### 2.5.1. እንደርሰን እንደርስ በ1967 በኡጥላላ ዩኒቨርስቲ የትምህርት ተቋም ያደረገው ጥናት

በኢትዮጵያ በታንዛኒያ ያሉት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በእንግሊዝኛና በአገሪቱ ብሔራዊ ቋንቋ ላይ ያላቸውን አመለካት ለመለካት ነው፡፡ በአንደርሰን ጥናት የተጠኑት ሰዎች የሁለቱም ነገሮች የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ሲሆኑ ከኢትዮጵያ አምስት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ተማሪዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ተማሪቹ የተመረጡት ከስድስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆን፣ ሶስቱ በአዲ አበባ ውስጥ የሚገኙ፣ ሶስቱ ደግሞ ከአዲስ አበባ ውጭ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ነበሩ፡፡

አጥኚው መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተጠቀመበት ዘዴ የጽሁፍ መጠይቆችን በመበተን ሲሆን የሚከተሉትን ውጤቶች መዝግቧል፡፡

- በሁለቱም አገሮች በትምህርት ቤት ደረጃ ከብሔራዊ ቋንቋው ጎን እንግሊዝኛ ጠቃሚ ቦታ ያለው መሆኑን፣
- ከሁለቱም አገሮች የጎሳ ቋንቋ ተናጋሪዎች ለብሔራዊ ቋንቋው ዝቅተኛ አመለካከት ያላቸው መሆኑን፣
- በሁለቱም አገሮች በትምህርት ቋንቋነት ከብሔራዊ ቋንቋ ይልቅ እንግሊዝኛ ተመራጭነት ያለው መሆኑን፣
- በኢትዮጵያ የክፍል ደረጃ በጨመረ ቁጥር ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አሉታዊ አመለካከት እየጨመረ የሚሄድ መሆኑን ያሳያል፣

በመጨረሻም እንደርሰን የሚከተሉትን አስተያየቶች ሰጥቷል፡፡

- እንግሊዝኛ የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቋንቋ ስለሆነና፣ ተማሪዎችም ከፍተኛ አዎንታዊ አመለካከት ስላላቸው መንግስት ለቋንቋው ልዩ ትኩረት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- አሁን ያለው የፌድራል ቋንቋ የሚቀጥል ከሆነ ቋንቋው ተቀባይነትን እንዲያገኝ አስፈላጊው ጥረት ሁሉ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በተለይ ቋንቋቸው ከአማርኛ ውጭ የሆነ የጎሳ ቋንቋ ተናጋሪዎችን ማሳመን ተገቢ ነው፡፡

2.5.2. ፀሐዬ ተፈራ በ1977 በጆርጅ ታዎን ዩኒቨርስቲ በስነ ልሳን ትምህርት በፒ.ኤች፣ዲ ዲግሪ ማሚያ ያቀረበው ጥናት “A sociolinguistice srrvey of language use and attitudes towards language in Ethiopia: Implications for languages policy in education.”

የቀረበ ሲሆን የጥናቱ ዋነኛ ዓላማ፣ ኢትዮጵያውያን ለትምህርትና ለቢሮ ስራዎች እንዲሁም ከቢሮ ውጭ ላሉት ተግባራት በሚያገለግሉ ቋንቋዎች ላይ ያላቸውን አመለካት ለማወቅና ውጤቱን በወቅቱ ካለው እንዲሁም ወደፊት ሊኖር ከሚገባው የትምህርት ፖሊሲ ጋር ለማዛመድ ነው፡፡

በጽሁፉ የተጠኑት ሁለት መቶ አስራ አንድ ሰዎች ሲሆኑ በወቅቱ በነበረው የትምህርት ስርዓት ውስጥ በማገልገል ላይ የነበሩ ባለሙያዎች፣ የዩኒቨርስቲ መምህራንና ተማሪዎች፣ እንዲሁም የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም መምህራን ናቸው፡፡ ከተማሪዎቹ ዘጠና ሰባቱ በአሜሪካ ዩኒቨርስቲዎች በመማር ላይ የነበሩ ናቸው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች ከጾታ ስርጭት አኳያ ሲታዩ 91% ወንዶች 9% ሴቶች ሲሆኑ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አኳያ ደግሞ አኳያ ደግሞ በአራት ቡድን የተከፈሉ ናቸው፡፡ እነሱም፡-

- በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ = 41.7%
- በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ = 33.4%
- በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ = 11.4 %
- በሌሎች ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ = 13.5% ናቸው፡፡

ፀሐዬ መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀመበት ዘዴ የጽሁፍ መጠይቆችን በመበተን ሲሆን የሚከተሉትን ውጤቶች መዝግቧል፡፡

- የአፍ መፍቻ ቋንቋ የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን የብዙዎች ፍላጎት መሆኑን፣
- አብዛኞዎቹ ምላሾች የአፍ መፍቻ ቋንቋ የሁለተኛ ደረጃና የዩኒቨርስቲ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን አለመደገፋቸውን፣
- አብዛኞዎቹ መላሾ እንግሊዝኛ የሁለተኛ ደረጃና የዩኒቨርስቲ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን መደገፋቸውን፣
- አብዛኞዎቹ መላሾች አማርኛ ኦፊሲላዊ ቋንቋ እንዲሆንና ኦሮምኛና ትግርኛም ሁለተኛና ሶስተኛ ኦፊሳላዊ ቋንቋ እንዲሆኑ መደገፋቸውን፣
- የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጡ የሚወደድ ዓይነት አለመሆኑን፣

ፀሐዬ ከነዚህ የጥናቱ ውጤቶች በመነሳት የሚከተሉትን አስተያየቶች ሰንዝሯል፡፡

- አማርኛን በአፍ መፍቻነትና በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ የተለያዩ ወገኖች እንዳሉ እየታወቀ፣ አንድ አይነት መፃህፍትና መረጃ መሳሪያዎችን እየተጠቀሙ ማስተማር ጥሩ አይደለም፡፡ ስለዚህ አማርኛ አፍ መፍቻቸው የሆኑትንና ሌሎችን በተለያዩ መሳያሪያዎችና ዘዴዎች ማስተማር ተገቢ ሲሆን በሌላም በኩል ቋንቋውን ሳይሆን ስለ ቋንቋው ሰዋሰው ማስተማ አይጠቅምም ብቻ ሳይሆን፣ ተማሪዎቹ ትምህርቱን እንዲጠሉት ያደርጋል፡፡ ስለሆነም በዚህ ላይ ትኩረት ማድረግና ሁለቱ ወገኖች በተለያየና በዘመናዊ መል እንዲማሩ ቢደረግ፣
- ተማሪዎች ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል ድረስ በአፍ መፍቻ ቋንቋው ቢማሩና፣ በሁለተኛና በሶስተኛ ክፍል ላይ አማርኛን እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ቢማሩ፣
- እንግሊዝኛ ከዘጠነኛ ክፍል እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ የትምህርት ቋንቋ ቢሆን፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# 3. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት የተከተለው ቅይጥ የጥናት ዘዴ፤ ሲሆን ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ተማሪዎች በአማረኛ ትምህርት ቋንቋ ላይ ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል በተመለከተ ለችግሮች የመፍትሔ ሐሳብ በመጠቆም ተመራጭ የምርምር ስልት በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ሲባል ሌሎች የምርምር አይነቶች ለችግሮች የመፍትሔ ሀሳብ አያቀርቡም በማለት ሳይሆን አሰሳዊ የምርምር ዘዴ፤ ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከሌሎች የምርምር ዘዴዎች በተሻለ የሚጠቅም እንደሆነ በአጥኚዉ ስለታመነበት ነው፡፡ በተጨማሪም መጠናዊ የምርምር ዘዴን የተመረጠበት ምክንያት ተማሪዎች በአማረኛ ትምህርት ቋንቋ ላይ ያላቸው አመለካከት ምን እንደሆነ ለመለየት ሊነሱ የሚችሉ በርከት ያሉ ምክንያቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ ዋና ዋና ከሆኑት ምክንያቶች መካከል ይበልጥ በተማሪዎች የአማረኛ ቋንቋ አመለካከት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ ብሎ የሚያስባቸውን የተወሰኑ ተለዋዋጮች በመምረጥ ለማጥናት ስለሚጠቅም ነው፡፡

## 3.1. የናሙናዎች አመራረጥ ስልት

### 3.1.1. በጥናቱ የሚካተቱ ተማሪዎች

በጥናቱ ናሙናነት በሰኮሩ ከተማ ና በደነባ ከተማ ውስጥ የሚገኙ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ፣ የዚህ ክፍል ተማሪዎች የተመረጡበት ምክንያት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማዕከላዊ ደረጃ ላይ የሚገኙና አንጻራዊ በሆነ መልኩ በዕድሜና በትምህርት በሳል ተማሪዎችና ቁጥራቸውም የጥናቱን ተአማንነት ከፍ የሚያደርጉ በመሆናቸው ነው፡፡ የሌሎቹ ክፍል ተማሪዎች የዚህን ክፍል ተማሪዎች ያህል ምቹ አይደለም፡፡ ለምሳሌ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆናቸው ና ከ ሁለቱ ከተሞች አንድ ቦታ ላይ ብቻ ስለሚገኝ አጥኚው ከጥናቱ ውጭ እንዲሆኑ አድርጓዋል፡፡ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ለብሔራዊ ፈተና ስለሚዘጋጁና አጥኚው መረጃ በሚሰበስብበት ወቅት በትምህርት ቤቶች ሊገኙ ስለማይችሉ፣ በጥናቱ ሊታቀፉ አይችልም፡፡ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ገና ከመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጡና በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በቂ ልምድ የሌላቸው በመሆናቸው በጥናቱ አይታቀፉም፡፡ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በመሀል ያሉና መጠነኛ ልምድ ያላቸው ቢሆኑም የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በዘጠነኛ ክፍል (9) ውስጥ ያለፉ፣ ከዘጠነኛ ክፍል

ተማሪዎች ይበልጥ ልምድ ያካበቱና በዕድሜም የበሰሉ በመሆናቸው ሊመረጡ በቅተዋል፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ትምህርት ቤቶች ስምንት መቶ ሃያ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ሶስት መቶ ሃያ ተማሪዎች ወንዶች ሲሆኑ አምስት መቶ ተማሪዎች ሴቶች ናቸው፡፡

የናሙና ተማሪዎችን አመራረጥ በተመለከተ፣ ቀላል የእጣ ንሞና በመጠቀም እያንዳንዱ የጥናቱ አካላይ አባል ናሞና ሆኖ ለመመረጥ እኩል እድል አለው፡፡ በናሙናነት የሚመረጠው እያንዳንዱ የጥናቱ አካላይ አባል እጣው አንዱ ከሌላው አይበልጥምም ወይም አያንስምም (ያለው እንዳወቅ፡2011)፡፡ በዚህ መሰረት በሰኮሩ ና በደነባ ከተማ ባሉት ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ስምንት መቶ ሃያ ተማሪዎች ሲኖሩ አጥኚው ከነዚህ መካከል 230 ሁለት መቶ ሰላሳ ተማሪዎችን በቀላል የእጣ ንሞና ዘዴ መምረጥ ተችሎዋል፡፡ እያንዳንዱ ተማሪ የመመረጥ እድሉ 28 % (230/820*100%=28%) ነው፡፡ በእጣ ንሞና ዘዴ የተገኘውን የተማሪዎች ናሙና ዕጣ የማውጣት ዘዴን በመጠቀም ድምሩ በሁለቱም ት/ቤቶች 230 እስክደርስ ድረስ እጣ በማውጣት ናሙናውን መምረጥ ተችሎዋል፡፡

### 3.1.2. በጥናቱ የሚካተቱ መምህራን

በጥናቱ እንዲሳተፉ በናሙናነት የሚመረጡት መምህራን በየትምህርት ቤቶቹ የሚገኙ የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው፡፡ የአስረኛ ክፍል መምህራን የሚመረጡበት ምክንያት ከላይ እንደተገለጸው በናሙናነት የሚመረጡት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ስለሆኑና መልሶቻቸውን ከአስተማሪዎቻቸው አስተያየት ጋር ማነፃፀር አስፈላጊ ነው ተብሎ በመታመኑ ነው፡፡ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ስድስት አማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚገኙ ሲሆን ሁለት ወንዶች፣ አራቱ ሴቶች ናቸው፡፡ በጠቅላይ የንሞና ዘዴ የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን ለቃለ መጠይቅ ተመረጠዋል፡፡

### 3.1.3. በጥናቱ የሚካተቱ ትምህርት ቤቶች

በጥናቱ ውስጥ በናሙናነት የሚታቀፉት በሰኮሩ ወረዳ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ፤ በዚህ ጥናት የሚመረጡት የሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና የደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይሆናሉ፡፡ሌሎች የቴክኒክ ትምህርት ቤቶች በጥናቱ አልታቀፉም፡፡

ስለዚህ ከላይ እንደተገለጸው የሰኮሩ ከተማ ና በደነባ ከተማ ብዙሃን ተማሪዎች የሚማሩባቸው ትምህርት ቤቶች የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመሆናቸው ለጥናቱ ናሙና ሆነው ተመረጠዋል፡፡ እነዚህ ትምህርት ቤቶች የተመረጡበት ምክኒያት በሰኮሩ ወረዳ ካሉት ስድስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከፍተኛ የተማሪ ቁጥር የያዙ ትምህርት ቤቶች ስለሆኑና ሌሎቹ የአማረኛ ቋንቋ የማይዘወተርባቸው ገጠራማ አካባቢዎች ስለሆኑ በጥናቱ ውስጥ አልተካተቱ ፡፡

## *3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች*

እንደ ጥናቱ መለያየት ሁሉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ይለያያሉ፡፡ ይህ ጥናት የተማሪዎችን ዝንባሌ ለማወቅ ዓላማ አድርጎ የተነሳ በመሆኑ ለዝንባሌ ጥናት ምቹ የሆኑ ዘዴዎችን መምረጥ ግድ ይሆንበታል፡፡

ታሮንና ያል (2013)፣ ኪችን (2014)፣ ስፓሊስኪ (2010) “የተማሪች አመለካከት ለማወቅ ግልጽ የሆነው መንገድ እነሱን መጠየቅ ነው” ይላሉ፡፡ ከጥያቄ በተጨማሪ የተማሪዎችን አመለካከት ለማወቅ የምልከታ ሂደት መጠቀም እንደሚቻል ታሮንና ያል (2014) ይገልጻሉ፡፡ የአንድን ሰው ዝንባሌ ለማወቅ ለሰውየው ለራሱ ከሚቀርብለት ጥያቄ በተጨማሪ ሁኔታዎችን በዓይን ተመለክቶ መረጃ ማግኘት እንደሚቻል ከላይ የቀረበውን ሀሳብ በመጠናከር የብሪታኒካ ኢንሳይክሎፒዲያ (1986፣687) ሲገልጽ “አንድ ሰው ዝንባሌው የሚታወቀው ሊታይ ከሚችለው ሁኔታና ለግምገማ ከሚሰጠው ምላሽ ነው” ይላል፡፡

በዚህ መሰረት አጥኚው የተማሪዎችን አመለካከት ለማወቅ ሶስት ዘዴዎችን ተጠቅሞዋል፡፡

1. ለተማሪዎች በተለያየ መልክ የተዘጋጀ የጽሁፍ መጠይቅ በማቅረብ ነፃ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ በማድረግ፡፡
2. ለመምህራን ቃለመጠይቅ በማቅረብ ስለተማሪዎቻቸው የሚያውቁትንና ያዩትን እንዲናገሩ በማድረግ፡፡
3. በትምህርቱ ሂደት ላይ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል ለማወቅ የክፍል ትምህርት ምልከታ በማድረግ፡፡

### 3.3.1 የጽሁፍ መጠይቅ

ዱቢንና አልሸቸይን (1986፣17) "የአመለካከት ጥያቄዎች ዝግ መሆን ሲኖርባቸው በጣም ጥቂቶቹ ብቻ ክፍት ይሆኑና ለሌሎች መጠይቆች ድጋፍ ሰጪ በመሆን ለአጥኚው ያገለግላሉ" ይላሉ፡፡ በዚህ መሰረት የጽሁፍ መጠይቆቹ ለቋንቋ የአመለካከት መለኪያ ምቹ እንዲሆኑ አማራጭ መልሶቹ ዝግ ሆነው አምስት ነጥብ ደረጃ ባላቸው የሊከርት አፃፃፍ ስልት እንዲቀመጡ ይደርጋል፡፡ በተጨማሪም ሀሳቡን የሚያዳብሩና ለማብራሪያ የሚረዱ ጥቂት ክፍት ጥያቄዎችም ታቅፋዋል (አባሪ "ሀ" ከገጽ 1-6 ይመልከቱ)

እነዚህ ዝግ ጥያቀዌች የሆኑ አምስት ነጥቦች ደረጃ ያሏቸው የሊከርት አፃፃፍ በአሉታዊ ሀሳቦች አኳያ አማራጮች የተለያዩ ነጥቦችን እንዲሸከሙ ተደርጎዋል፡፡

### 3.3.2 ቃለመጠይቅ

ለመምህራን በሚቀረበው ቃለመጠይቅ ውስጥ የሚቀረቡት ክፍት ጥያቄዎች ስድስት ናቸው፡፡ (አባሪ "ለ"ን ይመልከቱ)፡፡ በምልልሱ ወቅት መምህራን የሚሰጡትን አስተያየት ሁሉ እንዳለ በጽሁፍ ለማስቀረት አስቸጋሪ ስለሚሆን የምልልሱ ሂደት በካሴት እንዲቀረጽ ከተደረገ በኋላ ወደ ጽሁፍ ተለውጦ ቀርቧል፡፡

### 3.4 የመጠይቁ ስርጭት

የመጠይቁን ስርጭትና አሞላል በተመለከተ አጥኚው ጥናቱ የሚመለከታቸው ትምህርት ቤቶች ሁሉ አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርጉ ከዩኒቨርስቲው ደብዳቤ አጽፎ ወደ የትምህርት ቤቶቹ በመንቀሳቀስ ከዳሬክተሮቹና ከዩኒት መሪዎቹ ጋር ተገቢውን ምክክር አድርጎዋል፣ ቅድመ ሁኔታዎችን ሁሉ አመቻችቶዋል፡፡ መጠይቁ ከመሞላቱ በፊት ከየትምህርት ቤቱ መጠይቁን እንዲሞሉ ለተመረጡ ተማሪዎች አጠቃላይ የመጠይቁን አሞላል በተመለከተና ለየት ባለ መልኩ ለሚመለሱት ጥያቄዎች ሁሉ መግለጫና ማብራሪያ ሰጥቶዋል፡፡

ተማሪዎች መጠይቁን የሚሞሉት እዚያው ከትምህርት ቤቱ አዳራሽ ውስጥ ተሰብስበው ነው፡፡ ይህ እንዲሆን የሚደረገው፡-

1. ተማሪዎች መጠይቁን ወደ የቤታቸው ይዘው ከሄዱ ሊቀደድ ወይም ሊጠፋባቸው ይችላል ከሚል ፍራቻ የተነሳ፣

2. መጠይቁን ከክፍል ውጭ ይዘው ከሄዱ ብዙዎቹ ተማሪዎች ተነጋግረው ተመሳሳይ መልስ ብቻ ይዘው ይመጣሉ ከሚል ፍራቻ የተነሳ፣

3. መጠይቁን ይዘው ከሄዱ አንዳንድ ወደ ተሳሳተ ግምታዊ መልስ ይሄዳሉ ከሚል ፍራቻ የተነሳ ነው፡፡

ይህ አጥኚው የተጠቀመበት በግንባር ቀርቦ መጠይቁን የማስሞላት ስልት ብክነትን ከመቆጣጠሩም በላይ መረጃ ሰብሳቢው እዚያው ሆኖ የሚሆነው ጥያቄዎችን እየመለሰ በማስሞላቱ ሁሉም መጠይቁን በትክክል ይሞላሉ በሚል ታሳቢነት ነው፡፡

## 3.3.3 ምልከታ

የክፍል ትምህርት ምልከታን በተመለከተ አጥኚው በየትምህርት ቤቶች ካሉት አስረኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን በሚማሩበት ጊዜ ተመልክቶዋል፡፡

ይህ የክፍል ምልከታ ያስፈለገበት ምክንያት በትምህርቱ ሂደት ላይ የተማሪዎች ተሳትፎና የመምህሩ ጥረት ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅና በተጨማሪም ተማሪዎች ትምህርቱን ወደውና ፈቅደው ከልብ መቀበል አለመቀበላቸውን፣ መምህሩም በደንብ ማቅረብ አለማቅረቡን ለማረጋገጥ ነው፡፡ በሌላ በኩል የክፍሉ አጠቃላይ ሁኔታ ለመማር ምቹ መሆን አለመሆኑን፣ በተማሪዎቹ ከሚቀርቡት መረጃ በተጨማሪ በዓይን አይቶ ለማረጋገጥ ነው፡፡ በመጨረሻም ይህ ትልመጥናት በዊሊያምና ሜሪ (2003) የዳበረን ቼክሊስት ተጠቅሞዋል፡፡

## 3.5 የመረጃ መተኝተኛ ዘዴዎች

ከተማሪዎች የሚሰበሰቡት መረጃዎች ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይኖራቸዋል፡፡ አንደኛው፣ ስለተማሪው ማንነትና ስለቤተሰቡ ሁኔታ የሚገልጸው ዳራዊ መረጃ ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ ተማሪው በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያለውን አመለካከት የሚያመላክት መረጃ ነው፡፡

መረጃዎቹ ከተማሪዎች እንደተሰበሰቡ መለያ ቁጥር ይሰጣቸውና በየትምህርት ቤቶች ተለይተው " በኤስ.ፒ.ኤስ.ኤስ ተደራጅቶዋል"፡፡ በዚህ አሰራር የእያንዳንዱ ጥያቄ አማራጭ መልሶች በምን ያህል ሰዎች እንደተመረጡ ታውቆ ተመዘግቧል፤ የመቶኛና የአማካይ ነጥብ ስሌትም ተሰርቶዋል፡፡ ቀጥሎ እያንዳንዱ ተማሪ በያንዳንዱ ተላውጦ ላይ ያገኘው

ነጥብ ተለይቶ ከታወቀና ከተመዘገበ በኋላ፣ ለልዩ ልዩ ስታቲስቲካዊ ንጽጽር በተገቢዎች ቀመሮች ተሰልቶዋል፡፡ የዚህ ክንውን ዓላማ በትምህርት ቤቶች፣ በወንዶችና በሴቶች፣ በየትምህርት ቤቶች ከሚገኙ ተማሪዎች ስታቲስቲካዊ ፋይዳ ያለው የምላሽ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማነፃፀር ሲሆን፣ በተጨማሪነት ከሁለት እስከ አምስት ባሉት ተለውጦዎች የተመዘገቡት ውጤቶች ከተለውጦ አንድ ውጤት ጋር ሊቀናጁ መቻል አለመቻላቸውን ለማወቅ ነው፡፡ ተላውጦ አንድ ከጥናቱ ርዕስ ጋር የተያያዘ ዋነኛ ጉዳይ ሲሆን ሌሎቹ በሱ ዙሪያ የሚታዩ ሁለተኛ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ስለዚህ የእያንዳንዳቸው ውጤት ከተለውጦ አንዱ ውጤት ምን ያህል ተጣምሮ እንዳለው መታየት ይኖርበታል፡፡ በሌላ በኩል በያንዳንዱ ተላውጦ ላይ የተገኙት መረጃዎን በመጠይቁ ላይ በሰፈሩት ተራ ቁጥርና ቅድመ ተከተል መሰረት እንደባህሪያቸው ሁኔታ በመቶኛና በአማካይ ነጥብ እየተጠቀሱ ተተንትኖዋል፣ በሠንጠረዦች ተቀነባብረው ቀርበዋል፡፡ በመጨረሻም በቃለመጠይቅ አማካይነት ከመምህራን የተሰበሰቡት መረጃዎች ከተማሪዎች ከተሰበሰቡት መረጃዎች ጋር እየተጣቀሱ ተብራርቶዋል፡፡ የአጥኚው የምልከታ ውጤቶችም ከተዘረዘሩ በኋላ ከተማሪዎች ምላሾች ጋር እየተነፃፀሩ ተገለጸዋል፡፡

## 3.6 የጥናቱ ተለዋዋጮች

ይህ ምርምር ነጻ ና ጥገኛ ተለዋዋጮች ሲኖሩት እንደሚከተለው ተለይተዋል

የተማሪዎች ግላዊ አመለካከት

የመምህራን ጸባይ

የእኩዮች ተጽኖ

የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ሁኔታ

የትምህርት ቤቶች ፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ ዲጋፍ ሰጪ ሁኔታዎችና የማስተማር ዘዴዎች

የተማሪው አመለካከት

**ነጻ ተለዋዋጭ** ⟶ **ጥገኛ ተለዋዋጭ**

# ምዕራፍ አራት

## 4.1. የመላሾች አጠቃላይ ሁኔታ

ናሙና የሁኔታ የመጠይቁ መላሾች ከሁለት ትምህርት ቤቶች የተመረጡና ሁለት መቶ ሰላሳ ተማሪዎች መሆናቸው በምዕራፍ ሦስት ተገልጿል፡፡ እነዚህን ተማሪዎች በጾታ፣ በዕድሜ፣ በሃይማኖት፣ በብሔረሰብና በአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ እንዲሁም በቤተሰብ ገቢ፣ በአባትና በእናት የትምህርት ደረጃና የስራ ሁኔታ አኳያ እንመለከታለን፡፡

### 4.1.1. ጾታ

በናሙናነት የተመረጡት ተማሪዎች ሁለት መቶ ሃምሳ ሁለት /60%/ ወንዶች ሲሆኑ አንድ መቶ ስልሳ ስምንት /40%/ ሴቶች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በየትምህርት ቤቱ የተገኘውን መረጃ ስንመለከት ቁጥሩ የተለያየ ሆኖ ይገኛል፡፡ ለዝርዝሩ ሠንጠረዥ አራትን ይመለከቱ፡፡

### 4.1.2. ዕድሜ

የናሙና ተማሪዎች ዕድሜ በአስራ አምስትና በሃያ ዓመት መሐል ሲሆን በሁለት ተመድበዋል፡፡ ከአስራ አምስት እስከ አስራ ሰባት ያሉትን በአንድ ወገን፣ ከአስራ ስምንት እስከ ሃያ ያሉትን ደግሞ በሌላ ወገን፡፡ በዚሁ መሰረት ከአስራ አምስት እስ አስራ ሰባት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙት ሁለት መቶ ሰባ አንድ /64.5%/ ሲሆን ከአስራ ስምንት እስከ ሃያ ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙት አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ /35.5%/ ናቸው፡፡ የዚህም ዝርዝር ሁኔታ በሰንጠረዥ አራት ላይ ይገኛል፡፡

### 4.1.3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ

የአፍ መፍቻ ቋንቋን በተመለከተ ሶስት መቶ ሰማኒያ ሁለቱ /91%/ በአማርኛ አፋቸውን የፈቱ ሲሆኑ ሰላሳ ስምንት /9%/ በኦሮምኛ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ናቸው፡፡

በመረጃዎቹ መሰረት አንድ መቶ ሰባ /40.5%/ ተማሪዎች አማራ ያልሆኑ ብሔረሰቦች ሲሆኑም ከሰላሳ ስምንቱ /9%/ በስተቀር ሌሎቹ ሁሉ በአማርኛ አፋቸውን የፈቱ ናቸው፡፡ ከጥናቱ ዓላማ አኳያ ብሔረሰቦችን "አማራ" እና "ሌላ" ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው "አማርኛ"

እና “ሌላ” በማለት እያንዳንዱ በሁለት ከፍለን ከትምህርት ቤቶች አኳያ ለማየት ሞክረዋል፡፡ በሰንጠረዥ አራት ይመልከቱ፡፡

*ሠንጠረዥ አራት*

*የተማሪዎች ጾታ፣ ዕድሜና የአፍ መፍቻ ቋንቋ*

| ትምህርት ቤት | ጾታ | | ዕድሜ | | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ከ15-17 | ከ18-20 | አማርኛ | ሌላ |
| ደነባ 2ኛ ደረጃ | 19 | 20 | 22 | 23 | 20 | 12 |
| ሰኮሩ 2ኛ ደረጃ | 20 | 21 | 23 | 22 | 22 | 6 |
| ድምር | **39** | **41** | **45** | **45** | **42** | **18** |
| አጠቃላይ ድምር | | | | | | 230 |

## 4.1.5. የአባቶችና የእናቶች የትምህርት ደረጃና የስራ ሁኔታ

አብዛኛዎቹ የተማሪ የትምህርት ደረጃቸው ከአስራ ሁለተኛ ክፍል በታች ነው፡፡ ከላይ ስለቤተሰብ የገቢ መጠን መግለጫ ላይ የሁለቱም ትምህርት ቤቶች ወላጆች ገቢ ዝቅተኛ መሆኑ ተገልጾ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ በትምህርት ደረጃም እንዳለ ተንፀባርቋል፡፡ የደነባና የሰኮሩ ትምህርት ቤት ወላጆች 50% ያልተማሩና በመሰረቱ ትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆን በዲግሪና በዲፕሎማ ደረጃ ላይ ያሉት 20% ብቻ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከ1 እስከ 12ኛ ክፍል ያጠናቀቁ ወላጆች 30% መሆናቸውን በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የስራ ሁኔታን በተመለከተ 23% ወላጆች የመንግስትና የሌሎች ድርጅቶች ተቀጣሪ ሲሆኑ 20.5% ወላጆች ደግሞ በንግድና በግል ስራ የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ ከእናቶች ደግሞ 21.9% ስራ የሌላቸውና የቤት እመቤቶች ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 33.9% ደግሞ ጡረተኞች፣ ስራ አጥና ስራቸው ያልተገለጸ ናቸው፡፡ ሰኮሩ ትምህርት ቤት ካሉት ወላጆች እናቶች 25% የቤት

እመቤቶች ሲሆኑ በተቃራኒው ደነባ ትምህርት ቤት ካሉት ወላጆች እናቶች 25% ብቻ የቤት እመቤት ናቸው፡፡ በዝርዝሩ ሠንጠረዥ ስድስት “ለ”ን ይመልከቱ፡፡

ሠንጠረዥ አምስት

የአባቶችና የእናቶች የትምህርት ደረጃና የስራ ሁኔታ

| “ሀ” የትምህርት ደረጃ | ሰኮሩ | ደነባ | ድምር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| የትምህርት ደረጃ | | | | |
| ያልተማረና መሰረት ትምህርት | 62 | 51 | 113 | 50 |
| ከ1-12 | 28 | 39 | 67 | 30 |
| ዲፕሎማ | 16 | 15 | 31 | 13 |
| ዲግሪ | 9 | 10 | 19 | 7 |
| ድምር | 115 | 115 | 230 | 100 |
| “ለ” የስራ ሁኔታ | | | | |
| በንግድና በሌላ የግል ስራ | 6 | 3 | 39 | 20.5 |
| በመንግስትና በሌሎች ድርጅቶች | 12 | 20 | 59 | 23 |
| ስራ አጥና ጡረተኛ | 18 | 22 | 40 | 21.9 |
| ስራቸው ያልተገለጸ | 10 | 8 | 30 | 12 |
| የቤት እመቤት | 38 | 24 | 62 | 25 |
| ድምር | 115 | 115 | 230 | 100 |

## 4.2. የመረጃዎች ስሌታዊ አሰራር

መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ አወንታዊና አሉታዊ ዐረፍተ ነገሮች ከያዙት ነጥቦች አኳያ እያንዳንዱ መላሽ ያገኘው ነጥብ ተለይቶ ተመዝግቧል፡፡ በያንዳንዱ ጥያቄ ላይ የተገኙት ነጥቦች ተደምረው ከአምስት የተገኘው አማካይ ነጥብ ተሰልቷል፡፡ ስለ አማካይ ነጥብ አሰራር አንድምሳሌ እንመለክከት፡-

"አማርኛን መማር እወዳለሁ" ለዚህ ዐረፍተ ነገር የሚከተለው ምላሽ ተሰጠ እንበል፡፡

በጣም እስማማለሁ፡ 25 መላሾች

እስማማለሁ …፡ 7 መላሾች

መወሰን ያስቸግረኛል፡10 መላሾች

አልስማማም ፡ 6 መላሾች

ፍጹም አልስማማም፡ 2 መላሾች

በምዕራፍ ሦስት እንደተገለጸው ይህ ዐረፍተ ነገር አዎንታዊ በመሆኑ "በጣም እስማማለሁ" /5/፣ እስማማለሁ /4/፣ መወሰን ያስቸግረኛል/3/፣ አልስማማም /2/፣ ፍጹም አልስማማም /1/ ነጥብ ይዘዋል፡፡ ስለዚህ የስሌቱ አካሄድ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

አማካይ ለማግኘት የስምምነቱን ነጥብ በድግግሙ ብዛት ማባዛትና መደመር ከዚያ ለመላሾች ቁጥር ማካፈል፡፡ /በዚህ ምሳሌ የመላሾች ቁጥር ሃምሳ ነው/ ስለዚህ፡-

$$\text{አማካይ} \frac{/5x25/ + /4x7/+ /3x10/ + /2x6/ + /1x2/}{50}$$

$$= \frac{125 + 28 + 20+ 12+2}{50}$$

$$= \frac{197}{50} = 3.94$$

በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ ከአማካይ ነጥቡ ጎን ለመላሾች ብዛት በመቶኛ ተሰልቶ ቀርቧል፡፡ ከላይ የወሰድነውን ምሳሌ በመቶኛ ስሌት እንደሚከተለው መስራት ይቻላል፡፡ የመቶኛ ስሌት የመላሽ ብዛት ሲካፈል ለጠቅላላ የመላሽ ቁጥር ሲባዛ በመቶ ይሆናል፡፡ ስለዚህ "በጣም እስማማለሁ" ያሉት ሃያ አምስት መላሾች በመቶኛ ሲሰላ 25/50 x 100= 50%:: በዚህ ቀመር መሰረት ስንሰራ "እስማማለሁ" የሚለው 7/14%/፣ "መወሰን ያስቸግረኛል" የሚለው 10/20%/፣ "አልስማማም" የሚለው 6/12%/፣ "ፍጹም አልስማማም" የሚለው 2/4%/ ይሆናል ማለት ነው፡፡

አማካይ ነጥብና የመቶኛ ስሌት በሚሰራበት ጊዜ ወደ አስረኛ ቅርበት ተጠጋግቷል፡፡

## 4.3. ከእያንዳንዱ ጥያቄ የተገኘ ምላሽ

### 4.3.1. የተማሪዎች ግላዊ አመለካከት

ይህ የመጀመሪያና ዋነኛ ተላውጦ ሲሆን ስድስት አዎንታዊና ስድስት አሉታዊ ሀሳቦችን በድምሩ አስር ዝግ ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ ይህ ክፍል እያንዳንዱ መላሽ ለ "1.11" እና ለ "1.12" ለሰጠው መልስ ምክንያት እንዲሰጥ ይጠይቃል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ የታቀፈ ሌላው ዋነኛ ጥያቄ በቁጥር "13" ላይ የቀረበው ነው፡፡ ይህ ጥያቄ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ሊቀርቡ የሚችሉትን ዐቢይ ትምህርቶችን ይዘረዝርና ተማሪዎች በፍላጎታቸው መሰረት በቅደም ተከተል እንዲመርጡ ይጋብዛል፡፡ ሌላው በዚህ ክፍል የታቀፈው ጥያቄ በቁጥር "14" ላይ የተቀመጠ ሲሆን ከሌሎች የተምህርት ዘርፎች ጋር ሲነፃፀር ተማሪዎ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጡትን ቦታ ለማወቅ የታሰበ ነው፡፡

ከዚህ ቀጥለን በዚህ ተላውጦ ስር ለቀረቡት አስራ አራት ጥያቄዎች ለእያንዳንዳቸው የተሰጠውን መልስ በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

1.1 በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ገፍቼ ጋዜጠኛና ደራሲ መሆን እፈልጋለሁ፡፡

| አማራጭ መልሶች | የመላሽ ብዛት | የተገኘ ነጥብ | መቶኛ |
|---|---|---|---|
| ሀ. በጣም እስማማለሁ | 80 | 665 | 31.72 |
| ለ. እስማማለሁ | 46 | 276 | 16.42 |
| ሐ. መወሰን ያስቸግረኛል | 58 | 318 | 25.22 |
| መ. አልስማማም | 26 | 126 | 15.01 |
| ሠ. ፍጹም አልስማማም | 20 | 49 | 11.76 |
| ድምር | 230 | 1434 | 100 |
| አማካይ | 3.41 | | |

1.2 ግድ ሆኖብኝ እንጂ አማርኛን መማር አልፈልግም

| አማራጭ መልሶች | የመላሽ ብዛት | የተገኘ ነጥብ | መቶኛ |
|---|---|---|---|
| ሀ. በጣም እስማማለሁ | 26 | 32 | 7.62 |
| ለ. እስማማለሁ | 20 | 44 | 5.2 |
| ሐ. መወሰን ያስቸግረኛል | 46 | 0 | 4.8 |
| መ. አልስማማም | 58 | 488 | 29.0 |
| ሠ. ፍጹም አልስማማም | 80 | 1120 | 53.3 |
| ድምር | 230 | 1744 | 100 |
| አማካይ | 4.15 | | |

ለአዎንታዊ ሀሳቦች ሁሉ የስሌት አሰራር ምሳሌ እንዲሆንና ደግሞ ለአሉታዊ ሀሳቦች ሁሉ የስሌት አሰራር ምሳሌ እንዲሆን በዝርዝሩ ያስቀመጥን ስለሆነ ሌሎቹን በአጭሩ በመቶኛና በአማካይ ነጥብ እየገለጽን እናልፋለን፡፡ ደግሞም በዚህ ጥናት መጨረሻ አጠቃላይ ሁኔታውን የሚያቀርብ አባሪ ስላለ እያንዳንዱ ጥያቄ ላይ ስለ አሰራሩ ዝርዝር ጉይ ውስጥ መግባት አያስፈልግም፡፡

**1.3 አብዛኛዎቹ የመማራቸው የአማርኛ ዘርፎች ከፍላጎቴ ጋር ይጣጣማሉ፡፡**

በዚህ ሀሳብ ላይ 31.4% “በጣም እስማማለሁ”፣ 33.3%፣ “እስማማለሁ”12.1%፣ “መወሰን ያስቸግረኛል” 13.8%፣ “አልስማማም” 9.3% ደግሞ “ፍጹም አልስማማም” በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.64 ነው፡፡

**1.4 የአማረኛ ቋንቋ ያስጠላኛል፡፡**

በዚህ ዐረፍተ ነገር ላይ 5.2% “በጣም እስማማለሁ”፣ 6.2% “እስማማለሁ”፣ 8.1% “መወሰን ያስቸግረኛል” 32.6%፣ “አልስማማም” 47.9% “ፍጹም አልስማማም” የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 4.12 ነው፡፡

**1.5 የአማረኛ ቋንቋ ተናጋሪ ብሔረሰቦችን አከብራለው፡፡**

ለዚህ ሀሳብ “በጣም እስማማለሁ” ያሉት 55.7%፣ “እስማማለሁ” ያሉት 18.1%፣ “መወሰን ያስቸግረኛል” ያሉት 11.4%፣ “አልስማማም” ያሉት 7.4% ፣ “ፍጹም አልስማማም” ያሉትም 7.4% ናቸው፡፡ አማካይ ነጥቡ ደግሞ 4.07 ነው፡፡

**1.6 ብዙ ግዜ የአማረኛ ትምህርት ውጤት ዝቅተኛ ነው፡፡**

በዚህ ላይ 4.3% “በጣም እስማማለሁ” 1.2%፣ “እስማማለሁ” 3.6%፣ “መወሰን ያስቸግረኛል” 22.4%፣ “አልስማማም” 68.6%፣ “ፍጹም አልስማማም” በማለት መልሰዋል፡፡ አማካይ ነጥቡ 4.50 ነው፡፡

**1.7 ሳነብና ሳዳምጥ ከሌሎች ቋንቋዎች ይልቅ በደንብ የሚገባኝ በአማረኛ ቋንቋ ሲሆን ነው፡፡**

ለዚህ ሀሳብ 43.3% "በጣም እስማማለሁ" 22.6%፣ "እስማማለሁ" 16.7% ፣ "መወሰን ያስቸግረኛል" 7.9%፣ "አልስማማም" 9.5% ፣ "ፍጹም አልስማማም" የሚል መልስ ተሰጥቷል፡፡ አማካይ ነጥብ 3.82ነው፡፡

1.8 ጓደኞቼ አማርኛ ቋንቋን ይጠላሉ፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 12.1% "እስማማለሁ" ያሉት 14%፣ "መወሰን ያስቸግረኛል" ያሉት 14.3%፣ "አልስማማም" ያሉት 27.1%፣ "ፍጹም አልስማማም" ያሉት 32.4% ናቸው፡፡ አማካይ ነጥቡ 3.54 ነው፡፡

1.9 ጓደኞቼ ከሌሎች ቋንቋዎች ይበልጥ አማርኛን በስፋት ይጠቀማሉ፡፡

ለዚህ ሀሳብ 65.2% "በጣም እስማማለሁ" 15.2% "እስማማለሁ" 7.1% "መወሰን ያስቸግረኛል" 8.1% "አልስማማም" 4.3% ብለዋል፡፡ አማካይ ነጥቡ 4.29 ነው፡፡

1.10 ጓደኞቼ የአማርኛ ትምህርት ቀላል ነው እያለ ይንቃሉ፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ 27.9% "በጣም እስማማለሁ" 17.6% "እስማማለሁ" 14%፣ "መወሰን ያስቸግረኛል" 12.6% "እስማማለሁ" 27.9%፣ "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል፡ አማካይ ነጥቡ 2.95 ነው፡፡

በዚህ ተላውጦ ላይ ከፍተኛ አዎንታዊ ነጥብ የተመዘገበው "አማርኛ ቋንቋ ያስጠለኛል" በሚለው አሉታዊ አረፍተ ነገር ላይ ሲሆን 91% ተማሪዎች ሀሳቡን ተቃውመውታል፡፡ አማካይ ነጥቡም 4.50 ነው፡፡

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ የነበረው መድኃኒ ሀብተጊዮርጊስ /1986፡22/ የአዲስ አበባ ተማሪዎች አማርኛን እንደሚጠሉ አድርጎ ያቀረበውና በተወሰኑ ሰዎችም እየተደገፈ የሚነገረው ሀሳብ ፍጹም ውሸት ነው፡፡ ማንም ሰው ቋንቋውን አይጠላም፡፡ ጊዋራ /1983/ የአንድ አካባቢ ቋንቋ ከተናጋሪዎች ህልውና ጋር የተያያዘ ዋነኛ ጉዳይ መሆኑን ይጠቅሳል፡፡ አንድ ጊዋራ አባባል የራሱን ቋንቋ የሚጠላ ህሊናውን የሚጠላ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የደነባና የሰኮሩ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋቸው እንደሆነ ድረስ /ከጥቂቶች በስተቀር/ ሊጠሉት አይችሉም፡፡ ከጥናቱ የተገኘው መረጃም ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡

ሌላው ከፍተኛ ነጥብ የተመዘገበው "ሳነብና ሳዳምጥ ከሌሎች ቋንቋዎች ይልቅ በደንብ የሚገባኝ በአማርኛ ቋንቋ ሲሆን ነው" በሚለው ሀሳብ ላይ ሲሆን 80.4% መላሾች ተቀብለውታል፡፡ አማካይ ነጥቡም 4.29 ነው፡፡ ከዚህ ሀሳብ ጋር ተጣምሮ ሊታይ የሚችለው ወደ አሉታዊነት ያዘነበለ ምላሽ የተገኘበት "አማርኛ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቋንቋ ሲሆን ደስ ይለኛል" የሚለው ሀሳብ ነው፡፡ በመሰረቱ አንድ ሰው ለመማር የቋንቋ ምርጫ ቢሰጠው መምረጥ ያለበት ለማንበብም ሆነ ለማዳመጥ ይበልጥ የሚቀለውንና የሚገባውን መሆ አለበት ነገር ግን በዚህ ጥናት ከተማሪዎቹ የተገኘው ምላሽ በተቃራኒው ነው፡፡ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች "ይበልጥ የሚገባን አማርኛ ነው" እያሉ አማርኛ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን አልደገፉም፡፡ አማርኛ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን አለመደገፉ በዚህ ጥናት ብቻ የታየ ሳይሆን ቀደም ብለው በተደረጉት በአንደርሰን አንደርሰ ጥናት /1967/፣ በፀሐይ ተፈራ ጥናት /1977/፣ በብርሃኑ ገብረማርያም ጥናት /1976 ዓ.ም/፣ በወርቁ በሻዳ ጥናት /1982 ዓ.ም/ ሁሉ ላይ ነው፡፡ ተማሪዎቹ በዚህ ጥናት ላይ አማርኛ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን ላለመደገፋቸው የሰጡትን ምክንያቶች ወረድ ብለን እናገኛለን፡፡

ሁለት ከፍተኛ የተቃውሞ መልስ የተሰጣቸው አሉታዊ ሀሳቦች "ግድ ሆኖብኝ እንጂ አማርኛን መማር አልፈልግም" የሚለውና "የአማርኛ ትምህርት ስለሚቀለኝ እንቀዋለሁ" የሚሉት ናቸው፡፡ የመጀመሪያውን ሀሳብ የተቃወሙት 82.3% ሲሆኑ ሁለተኛውን ሀሳብ የተቃወሙት 86.5% ናቸው፡፡ አማካይ ነጥባቸው እንደቅደም ተከተላቸው 4.15 እና 4.12 ናቸው፡፡ እነዚህ መረጃዎች ተማሪዎች አማርኛን እንደሚንቁና መማር እንደማይፈልጉ በብርሃኑ ገብረማርያም ጥናት /1976 ዓ.ም/ የቀረበውንና በአነዳንድ ሰዎችም የሚናገረውን ሀሳብ ውድቅ ያደርጉታል፡፡

በ"1፣1" ላይ እንደቀረበው፣ በአማርኛ ትምህርት ገፍተው ጋዜጠኛና ደራሲ መሆን የሚፈልጉት ተማሪዎች 48% ሲሆኑ የማይፈልጉት 26.7% ናቸው፡፡ "ጋዜጠኛና ደራሲ መሆን እንፈልጋለን" ያሉት ተማሪዎች አማርኛንና የአማርኛን ትምህርት እንደማይጠሉ እንገምታለን፡፡ በሌላ በኩል "ጋዜጠኛና ደራሲ መሆን አንፈልግም" ያሉት ተማሪዎች ሁሉ አማርኛንና ትምህርቱን ይጠላሉ ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን ከቋንቋው ትምህርት ጋር የተያያዘውን ሙያ ምን ያህሉ ተማሪዎች እንደሚያልሙትና ከዓላማቸው አኳያ ለትምህርቱ ሊሰጡ የሚችሉትን ትኩረት ለመገመት ይረዳል፡፡

በ "1.3" ላይ እንደተገለጸው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች /64.7%/የሚመሯቸው የአማርኛ ትምህርት ዘርፎች ከፍላጎታቸው ጋር ይጣጣማሉ፡፡ ፍላጎትን የጠበቀ ትምህርት ይወደዳል፡፡ ስለዚህ የአማርኛ ትምህርት የብዙዎቹን ፍላጎት ከጠበቀ በብዙዎቹ ተማሪዎች ይወደዳል ማለት ነው፡፡ በርግጥ 22.5% ተማሪዎች ከፍላጎታቸው ጋር እንደማይጣጣም ገልጸዋል፡፡ ቀሪዎቹ መወሰን አልቻሉም፡፡

በ"1.7" ላይ እንደቀረበው 65.9% ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ብሔረሰቦችን ያከብራሉ፡፡ ብሔረሰቡን ያከበረ የብሔረሰቡን ቋንቋ እንደሚያከብር በተዛማጅ ጽሁፍ ክለሳ ክፍል አይተናል፡፡ ስለዚህ አብዛኛዎች ተማሪዎች ብሔረሰቦችንና አማርኛ ቋንቋን አያከብሩም /17.4%/፣ ቀሪዎቹ ደግሞ አቋም ያልወሰዱ ናቸው፡፡

በ "1.8" መረጃ መሰረት ብዙ ጊዜ የአማርኛ ትምህርት ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆነው 26.1% ሲሆኑ 59.5% ውጤታቸው ጥሩ ነው፡፡ በተዛማጅ ጽሁፍ ክለሳ ክፍል እንደተገለጸው በአንድ ቋንቋ ጥሩ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት ጥሩ አመለካከት ይኖራቸዋል፡፡ በዚህ መሰረት በርካታዎ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ጥሩ አመለካከት አላቸው ማለት ነው፡፡

ተማሪዎቹ ራሳቸው በ "1.9" ላይ በቀረበላቸው ጥያቄ መሰረት ሲያነቡና ሲያዳምጡ ከሌሎች ቋንቋዎች ይበልጥ በአማርኛ ሲሆን እንደሚገባቸው ተናግረዋል፡፡

## 4.4. የአማርኛ ቋንቋ መምህር ጠባይ፣ ችሎታና አመለካከት

በዚህ ተላውጦ ስራ የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች ስለመምህራን ጠባይ፣ ችሎታና አመለካከት የሚያውቁትን ሀሳብ እንዲሰጡ የሚያደርጉ ሁለት ናቸው፡፡ ጥያቄዎችንና መልሶቻቸውን እንደሚከተለው እናቀርባለን፡፡

4.4.1. መምህሩ ተማሪዎች አማርኛንና የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት እንዲወዱ ጥረት ያደርጋል፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ 52.9% "በጣም እስማማለሁ"፣ 23.6% "እስማማለሁ" 6.2% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 6% "አልስማማም"፣ 11. 4% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 4.00 ነው፡፡ ስለዚህ 76.5% ተማሪዎች ሀሳቡን ስለደገፉ መምህራን ተማሪዎች አማርኛንና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንዲወዱ ጥረት ያደርጋሉ ማለት ነው፡፡

4.4.2. መምህሩ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በቂ ዕውቀት የለውም፡፡

ለዚህ ሀሳብ "በጣም እስማማለሁ" 7.6%፣ "እስማማለሁ" 8.1%፣ "መወሰን ያስቸግረኛል" 13.8%፣ "ፍጹም አልስማማም" 52.1% መልስ የተሰጠ ሲሆን አማካይ ነጥቡም 3.99 ነው፡፡

በመረጃው መሰረት 70.4% ተማሪዎች ሀሳቡን ስለተቃወሙት ጥቂት ደጋፊዎችና አቋም ያልወሰዱ ቢኖሩም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለክፍል ደረጃ የሚበቃ ዕውቀት እንደላቸው እንገነዘባለን፡፡

4.4.3. መምህሩ የተማሪዎችን ተሳትፎ የሚቀሰቅስ ማራኪ አቀራረብ አለው፡፡

ለዚህ ሀሳብ 32.4% "በጣም እስማማለሁ"፣ 24.5% "እስማማለሁ"፣ 14% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 9.5% "አልስማማም"፣ 19.5% "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.41 ነው፡፡

በመረጃው መሰረት 56.9% ተማሪዎች የመምህሩ አቀራረብ ማራኪ መሆኑን የደገፉ ሲሆን 29% ተቃውመውታል፡፡ ሌሎቹ መወሰን ያልቻሉ ናቸው፡፡ ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት አቀራረብ ሙሉ በሙሉ የተደገፈ ባይሆንም አዎንታዊ ምላሹ ከአሉታዊ ምላሹ በልጦ ይታያል፡፡

4.4.4. መምህሩ ተማሪዎችን የሚያቋሽሽ ቁጡና ተሳዳቢ ነው፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ 10.5% "በጣም እስማማለሁ"፣ 7.4% "እስማማለሁ"፣ 8.3% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 22.6% "አልስማማም"፣ 51.2% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.97 ነው፡፡

ከመረጃው በግልጽ እንደሚታየው በአሉታዊ ሀሳቡ ላይ የተሰሙት 17.9% ብቻ ሲሆኑ መወሰን ያልቻሉትም ጥቂቶች ናቸው፡፡ በርካታ ተማሪዎች /73.8%/ ሀሳን ተቃውመውታል፡፡ ስለዚህ በርካታዎ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎችን አያንቃሽሹም፣ አይቆጡም፣ አይሳደቡም ማለት ነው፡፡

4.4.5. መምህሩ የግል ጥረቱን እያከለ የቋንቋ ችሎታዎችን /ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ/ በሚገባ ያለማምዳል፡፡

ለዚህ ሀሳብ 40.7% "በጣም እስማማለሁ"፣ 23.8% "እስማማለሁ"፣ 9.7% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 11.7% "አልስማማም"፣ 19% "ፍጹም አልስማምም" ብለዋል አማካይ ነጥቡም 3.65 ነው፡፡

ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የግል ጥረታቸውን እያከሉ እንደሚሰሩ ብዙ ተማሪዎች /64.5%/ መስክረዋል፡፡

4.4.6. መምህሩ ብዙ ጊዜ ሳይዘጋጁ ክፍል ይገባል፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ 9.5% "በጣም እስማማለሁ"፣ 7.6% "እስማማለሁ"፣ 12.6% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 24% "አልስማማም"፣ 46.2% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.90 ነው፡፡

ይህንን አሉታዊ ሀሳብ የደገፉት 17.1% ብቻ ሲሆኑ 70.2% ተቃውመውታል፡፡ ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሳይዘጋጁ ክፍል አይገቡም ማለት ነው፡፡

4.4.7. መምህሩ ተማሪዎች ከፍላጎታቸው መሰረት ተደስተው እንዲማሩ ያማክራቸዋል፡፡

ለዚህ ሀሳብ 30.2% "በጣም እስማማለሁ"፣ 19.3% "እስማማለሁ"፣ 16.9% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 18.1% "አልስማማም"፣ 15.5% "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.31 ነው፡፡

በመረጃው መሰረት የሀሳቡ ደጋፊዎች 49.5% ሲሆኑ ተቃዋሚዎች 33.6% ናቸው፡፡ ስለዚህ የሀሳቡ ተቃዋሚዎች ቁጥር የማይናቅ ቢሆንም ደጋፊዎች በልጠው በመገኘታቸው ሚዛኑ ወደ አዎንታዊ ሀሳብ አጋድሎ ይታያል፡፡

4.4.8. መምህሩ ማርክ /ነጥብ/ አሰጣጡ አድሏዊ ነው፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ 9.5% "በጣም እስማማለሁ"፣ 2.6% "አልስማማም"፣ 8.8% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 21.9% "አልስማማም" 57.1% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 4.15 ነው፡፡

ከመረጃው በግልጽ እንደሚታየው አሉታዊ ሀሳቡን 12.1% ብቻ የደገፉትና ጥቂቶ “መወሰን ያስቸግረኛል” ሲሉ 79% ሀሳቡን ተቃውመውታል፡፡ ስለዚህ የአማርኛ መምህራን የማርክ /ነጥብ/ አሰጣጣቸው አድሏዊ አይደለም ማለት ነው፡፡

4.4.9. መምህሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንዲገፉ ያበረታታቸዋል፡፡

ለዚህ ሀሳብ 35.7% “በጣም እስማማለሁ”፣ 28.1% “እስማማለሁ”፣ 13.6% “መወሰን ያስቸግረኛል”፣ 11.9% “አልስማማም”፣ 10.7% “ፍጹም አልስማማም” ብለዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.66 ነው፡፡

በመረጃው መሰረት 63.8% ተማሪዎች ሀሳቡን የደገፉ ሲሆን የተቃወሙት 22.6% ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ መወሰን ያልቻሉ እንደመሆናቸ ው መጠን ሁለቱን ወገኖች ስናነፃፅር አወንታዊ ሀሳብ የሰጡት በልጠው ስለታዩ በብዙሃን ሀሳብ መሰረት መምህራኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንዲገፉ ያበረታቷቸዋል ማለት ነው፡፡

4.4.10. መምህሩ አማርኛን እንደማይወድና ለደሞዙ ሲል ብቻ እንደሚያስተምር ይናገራል፡፡

ለዚህ ሀሳብ 6.2% “በጣም እስማማለሁ”፣ 1.2% “እስማማለሁ”፣ 10% “መወሰን ያስቸግረኛል”፣ 21% “አልስማማም”፣ 61.7% “ፍጹም አልስማማም” በማለት መልሰዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 4.31 ነው፡፡

ከመረጃዎቹ በግልጽ እንደሚታየው አሉታዊ ሀሳቡን 7.4% መላሾች ብቻ ሲደግፉት 82.7% መላሾች ተቃውመውታል፡፡ ስለዚህ የአማርኛ መምህራን አማርኛን እንደሚጠሉና ለደሞዝ ሲሉ ብቻ እንደሚያስተምሩ አይናገሩም፡፡

4.4.11. መምህሩ የሚሰጠው የክፍልና የቤት ስራዎች ያርማል፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ 42.1% “በጣም እስማማለሁ”፣ 31% “እስማማለሁ”፣ 7.1% “መወሰን ያስቸግረኛ”፣ 10.7% “አልስማማም”፣ 9% “ፍጹም አልስማማም” በማለት መልሰዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.93 ነው፡፡

ከመረጃው እንደሚታየው 73.1% ሀሳቡ የተደገፈ ሲሆን 19.7% ብቻ ተቃውሞ ገጥሞታል፡፡ ስለዚህ በብዙሃን አስተያየት መሰረት የአማርኛ መምህራን የሚሰጡትን የክፍልና የቤት ስራ ያርማሉ ማለት ነው፡፡

4.4.12. መምህሩ ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ በቂ ዕድል አይሰጥም፡፡

ለዚህ ሀሳብ 12.6% "በጣም እስማማለሁ"፣ 11.9% "እስማማለሁ"፣ 6.7% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 24.8% "አልስማማም" 44% "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.76 ነው፡፡

ይህን አሉታዊ ሀሳብ የደገፉት 24.5% ሲሆኑ ጥቂቶቹ መወሰን አልቻሉም፡፡ በአንፃሩ 68.8% በሀሳቡ ላይ ተቃውሞ ስላቀረቡ መሰረት መምህራን ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ በቂ ዕድል ይሰጣሉ ማለት ነው፡፡

የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን በተመለከተ በዚህ ተላውጦ የቀረቡት ጥያቄዎች ሁሉ አዎንታዊ ምላሽ ያገኙ ሲሆን አማካይ ነጥቡም 3.84 ነው፡፡ ስለተላውጦ ሶስት የተጠቃለሉ መረጃዎችን ለማግኘት አባሪ "ሰ"ን ይመልከቱ፡፡

## 4.5 የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት ሁኔታ

ይህ ክፍል ስለመማሪያ መፃህፍት አጠቃላይ ሁኔታ ተማሪዎች የሚያውቁትን እንዲመልሱ የሚጠይቅ ሲሆን አስራ ሁለት ጥያቄዎችን አቅፏል፡፡ ቀጥለን ዝርዝር ጥያቄዎችንና መልሶቻቸውን እንመለከታለን፡፡

4.1. በትምህርት ቤታችን በቂ የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት አሉ፡፡

ለዚህ ሀሳብ 35% "በጣም እስማማለሁ"፣ 15.5% "እስማማለሁ"፣ 16.4% "መወሰን ያስቸግረኛ"፣ 12.4% "አልስማማም"፣ 20.7% "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.36 ነው፡፡

በተገኘው መረጃ መሰረት 50.5% መላሾች በቂ መማሪያ መጻህፍት እንዳሉ ሲያቀርቡ 33.1% መላሾች ደግሞ ብቁ መማሪያ መጻህፍት እንደሌሉ ተናግረዋል፡፡ መወሰን ያልቻሉትም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም፡፡ የሆነው ሆኖ አብላጫው እጅ በቂ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍት እንዳ አቅርበዋል፡፡

4.2. የአስራ አንደኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ የተማሪዎችን ፍላጎት አያንጸባርቅም፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ 18.8% "በጣም እስማማለሁ"፣ 17.6% "እስማማለሁ"፣ 23.3% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 19% "አልስማማም"፣ 23.3% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.10 ነው፡፡

የዚህ አሉታዊ ሀሳብ ደጋፊዎች 36.4% ሲሆኑ ተቃዋሚዎች 42.3% ናቸው፡፡ መወሰን ያልቻሉም በርካታ ናቸው፡፡ የደጋፊና የተቃዋሚ ቁጥሮች የተቀራረቡ ቢሆኑም አማካይ ነጥቡ ለትንሽ ወደ አወንታዊነት አዘንብሎ ይታያል፡፡

4.3. በአማርኛ መማሪያ መጻህፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ማራኪ ናቸው፡፡

ለዚህ ሀሳብ 31% "በጣም እስማማለሁ"፣ 35.2% "እስማማለሁ"፣ 16.2% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣10.5% "አልስማማም"፣ 7.1% "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.70 ነው፡፡

በመረጃው መሰረት 66.2% መላሾች ሀሳቡን ሲደግፉ 17.6% ብቻ ተቃውሞ አቀርበዋል፡፡ ስለዚህ በብዙሃን ምላሽ መሰረት በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ማራኪ ናቸው፡፡

4.4. የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ማንበብ ያስጠላኛል፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ 11.2% "በጣም እስማማለሁ"፣ 7.6% "እስማማለሁ"፣ 7.9% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 29.5% "አልስማማም"፣ 43.8% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.83 ነው፡፡

ከመላሾቹ እንደሚታየው አሉታዊ ሀሳቡን የደገፉት 18.8% ብቻ ሲሆኑ፣ ተቃዋሚዎች 73.3% ናቸው፡፡ ስዘሊህ በብዙሃኑ ሀሳብ መሰረት ተማሪዎች የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ማንበብ አያስጠላቸውም

4.5. በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ምንባቦች በግልጽ ቋንቋ የቀረቡ ናቸው፡፡

ለዚህ ሀሳብ 29% "በጣም እስማማለሁ"፣ 33.3% "እስማማለሁ"፣ 16.6% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 13.8% "አልስማማም"፣ 6.9% "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.64 ነው፡፡

ከመረጃው መረዳት እንደሚቻለው ሀሳቡ 62.3% ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን 20.7% ተቃውሞ ገጥሞታል፡፡ ስለዚህ በብዙሃን ምላሽ መሰረት በአማርኛ ቋንቋ መጽሀፍ ውስጥ ያሉ ምንባቦች በግልጽ ቋንቋ የቀረቡ ናቸው፡፡

4.6. የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ በስዕላዊ መግለጫዎች ስላልታጀበ አይስበኝም፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ 13.1% "በጣም እስማማለሁ"፣ 14.3% "እስማማለሁ"፣ 13.3% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 27.4% "አልስማማም"፣ 31.9% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል፡፡ አካማይ ነጥቡም 3.51 ነው፡፡

በመረጃው መሰረት የአሉታዊ ሀሳቡ ደጋፊዎች 27.4% ሲሆን ተቃዋሚዎች 59.3% ናቸው፡፡ ስለዚህ መጽሐፉ በስዕላዊ መግለጫዎች ባይታጀብም ተማሪዎችን መሳብ ችሏል ማለት ነው፡፡

4.7. በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች ጥሩ ናቸው፡፡

በዚህ ሀሳብ 29.3% "በጣም እስማማለሁ"፣ 37.6% "እስማማለሁ"፣ 14.3% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 10.2% "አልስማማም" 8.6% "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.88 ነው፡፡

በመረጃው መሰረት 66.9% መላሾች ሀሳቡን ሲደግፉ 18.8% ብቻ ተቃውመውታል፡፡ ስለዚህ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች ጥሩ ናቸው ማለት ነው፡፡

4.8. መጽሐፉ የቃላትን ዝርዝር ከነትርጉማቸው የሚያሳይ አባሪ ስለሌለው ብቃት የለውም፡፡

በዚህ ጥያቄ ላይ 29.5% "በጣም እስማማለሁ"፣ 24% "እስማማለሁ"፣ 21% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 16% "አልስማማም"፣ 9.5% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 2.52 ነው፡፡

ይህን አሉታዊ ሀሳብ የደገፉት 53.5% ሲሆኑ 25.5% ደግሞ ተቃውሞውታል፡፡ በርካታ ተማሪዎችም ለመወሰን ተቸግረዋል፡፡ ስለዚህ "መጽሀፉ የቃላትን ዝርዝር የሚያሳይ አባሪ ስለሌለው ብቃት የለውም" የሚለው ሀሳብ ሚዛን ደፍቶ ታይቷል፡፡

4.9. መጽሐፉ አስተማሪም ባይኖርም ተማሪውን መምራት ይችላል፡፡

ለዚህ ሀሳብ 17.9% "በጣም እስማማለሁ"፣ 17.1% "እስማማለሁ"፣ 19.3% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 23.8% "አልስማማም"፣ 21.9% "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 2.85 ነው፡፡

ይህንን ሀሳብ የተቃወሙት 45.7% ሲሆኑ ደጋፊዎች 35% ናቸው፡፡ ቁጥሮቹ የተቀራረቡ ቢመስሉም አጠቃላይ ውጤቱ ወደ አሉታዊነት አዘንብሎ ይታያል፡፡ ስለዚህ መጽሐፉ ያለአስተማሪ ተማሪውን መምራት አይችልም ማለት ነው፡፡

4.10. መጽሀፉ የቋንቋን ትምህርት ዓላማዎች አያንጸባርቅም፡፡

በዚህ ሀሳብ 12.1% "በጣም እስማማለሁ"፣ 13.1% "እስማማለሁ"፣ 29% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.52 ነው፡፡

በተጠቀሱት መረጃዎች መሰረት 60% መላሾች ሀሳቡን የተቃወሙት ሲሆኑ 25.2% ደግፈውታል፡፡ ስለዚህ በብዙሃን ሀሳብ መሰረት መጽሀፉ የቋንቋን ትምህርት ዓላማዎች አያንጸባርቅም ማለት ነው፡፡

4.11. መጽሐፉ የቋንቋ ዘርፎችን ሁሉ አካቶ ያቀርባል፡፡

ለዚህ ሀሳብ 18.8% "በጣም እስማማለሁ"፣ 14.5% "እስማማለሁ"፣ 16.7% "መወሰን ያስቸግረኛ"፣ 25.5% "አልስማማም"፣ 24.5% "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 2.65 ነው፡፡

በመረጃው መሰረት 50% መላሾች ሀሳቡን ተቃውመውታል፡፡ 33.3% ደግሞ የሀሳቡ ደጋፊዎች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ለመወሰን የተቸገሩ ናቸው፡፡ ስለዚህ መጽሐፉ የቋንቋ ዘርፎችን አካቶ እንደማያቀርብ ብዙዎቹ ተስማምተውበታል፡፡ አማካይ ነጥቡም ምላሹ በአሉታዊ ክልል ውስጥ መሆኑን ያሳያል፡፡

4.12. መጽሐፉ በምዕራፍና በክፍለ ጊዜ ስላልተከፋፈሉ ለአጠቃቀም ምቹ አይደለም፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ 11% "በጣም እስማማለሁ"፣ 11.7% "እስማማለሁ"፣ 21.4% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 28.6% "አልስማማም"፣ 27.4% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል አማካይ ነጥቡም 3.50 ነው፡፡

መረጃው እንደሚጠቀመን 22.7% መላሾች ብቻ ሀሳቡን ሲደግፉት 55% ተቃውመውታል፡፡ ስለዚህ መጽሀፉ በምዕራፍና በክፍለ ጊዜ ባይከፋፈልም ለብዙዎቹ ተማሪዎች በአጠቃቀም ላይ ችግር አላመጣም፡፡

በተላውጠ አራት ከቀረቡት አስራ ሁለት ጥያቄዎች ሶስቱ ብቻ አሉታዊ መልስ ሲያገኙ የቀሩት በሙሉ አዎንታዊ ምላሽ አግኝተዋል፡፡ የተላውጠው አማካይ ነጥብ 3.33 ነው፡፡ ስለተላውጠው የተጠቃለለ መረጃዎችን ለማግኘት አባሪ "ሸ"ን ይመልከ

## 4.6 የወላጆች፣ የህብረተሰቡና የእኩዮች አመለካከት

በዚህ ተላውጠ ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ሶስት የተለያዩ ወገኖችን ይመለከታሉ፡፡ የመጀመሪያው አራቱ ሀሳቦች የወላጆችን አመለካት የሚጠይቁ፣ በመሐል ያሉ አራት ጥያቄዎች ስለአካባቢው ህብረተሰብ አመለካከት የሚጠይቁ ሲሆኑ የመጨረሻዎቹ አራቱ ደግሞ ስለ ተማሪው እኩዮች አመለካከት የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ጠቅላላ ጥያቄዎች አስራ ሁለት ሲሆኑ ስድስት በአዎንታዊ፣ ስድስቱ ደግሞ በአሉታዊ ሀሳብ መልክ የተቀመጡ ናቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የተሰጠው መልስ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

4.6.1. ወላጆቼ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጬ ለከፍተኛ ትምህርት እንድገፋበት አይፈቅዱም፡፡

ለዚህ ሀሳብ 7.4% "በጣም እስማማለሁ" 7.1% ፣ "እስማማለሁ" 31.4%፣ "መወሰን ያስቸግረኛል"20.2%፣ "አልስማማም" 5.8%፣ "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.66 ነው፡፡

በዚህ መረጃ መሰረት ተማሪዎች አማርኛን መርጠው ቢማሩ የማይከለክሉ ወላጆች 54% ሲሆኑ የማይፈቅዱት 14.5% ብቻ ናቸው፡፡ በርካታ ተማሪዎች ደግሞ የወላጆቻቸውን አቋም ለመወሰን ተቸግረዋል፡፡

4.6.2. ወላጆቼ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያለኝን ዝንባሌ ያበረታታሉ

በዚህ ሀሳብ ላይ 25.7% "በጣም እስማማለሁ" 23.3%፣ "እስማማለሁ" 30% ፣ "መወሰን ያስቸግረኛ" 11.7%፣ "አልስማማም" 9.3% ፣ "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.45 ነው፡፡

በጥቅሉ የሀሳቡ ደጋፊዎች 49% ሲሆኑ ተቃዋሚዎ 21% ናቸው፡፡ በዚህም ላይ በርካታ ተማሪዎች /30%/ የወላጆቻቸውን አቋም መወሰን አልቻሉም፡፡

4.6.3. ወላጆቼ በቤት ውስጥ በአማርኛ እንድናገር አይፈልጉም

ለዚህ ሀሳብ 9.5% "በጣም እስማማለሁ"፣ 6% "እስማማለሁ"፣ 8.3% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 21% "አልስማማም"፣ 55.2% "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 4.06 ነው፡፡

የቀረበውን አሉታዊ ሀሳብ የተቃወሙት 76.2% ስለሆኑ አማርኛ የቤት ውስጥ በስፋት ይነገራል ማለቱ ነው፡፡ በቤታቸው አማርኛን እንዳይናገሩ የሚከተሉትና ምናልባትም የወላጆቻቸውን ቋንቋ ብቻ እንዲናገሩ የሚገደዱት 15.5% ብቻ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ ጥቂት ተማሪዎች ለመወሰን የተቸገሩ ናቸው፡፡

4.6.4 የሰፈሬ ሰዎች "አማርኛ ብዙሃን ኢትዮጵያዊያንን ስለሚያገናኝ መማር ጥሩ ነው" እያሉ እንድማር ያበረታቱኛል፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ 27.9% "በጣም እስማማለሁ" ፣ 21.2% "እስማማለሁ"፣ 25% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 13.1% "አልስማማም"፣ 12.9% "ፍጹም አልስማማም" በማት መልሰዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.38 ነው፡፡

በመረጃው መሰረት ይህ ሀሳብ 49.1% የተደገፈ ሲሆን 26% ተነቅፏል፡፡

25% ተማሪዎች መወሰን አልቻሉም፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች አማርኛን እንዲማሩ በርካታው የአካባቢ ህብረተሰብ ይደግፋል ማለት ነው፡፡

4.6.5. የሰፈሬ ሰዎች "ከተማሩ አይቀር እንግሊዝኛ እንጂ አማርኛ ወንዝ አያሻግርም" እያሉ በትምህርቴ እንዳልገፋ ተስፋ ያስቆርጡኛል፡፡

ለዚህ ሀሳብ 11% "በጣም እስማማለሁ"፣ 11% "እስማማለሁ"፣ 16.4%፣ "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 23.6% "አልስማማም" 38.1%፣ "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.67 ነው፡፡

ይህንን አሉታዊ ሀሳብ 61.7% ተማሪዎች ሲቃወሙት 22% ተማሪዎች ደግፈውታል፡፡ ጥቂት መወሰን ያልቻሉ ተማሪዎች ቢኖሩም አብዛኛው ህብረተሰብ ተማሪዎች እንግሊዝኛ ወደው እንዲማሩና አማርኛን እንዲጠሉ አያደርግም ማለት ነው፡፡

4.6.6. **ብዙ ጎረቤቶቼ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ገፍቼ ጋዜጠኛና ደራሱ እንድሆን ይመክሩኛል፡፡**

በዚህ ሀሳብ ላይ 21.7% "በጣም እስማማለሁ"፣ 13.3% "እስማማለሁ"፣ 23.3 "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 19% "አልስማማም" 22.6% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 2.92 ነው፡፡

በመረጃው መሰረት 41.6% የአካባቢ ህብረተሰብ ተማሪዎቹ ጋዜጠኛና ደራሲ እንዲሆኑ ይመክራሉ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ መወሰን ያልቻሉ በርካታ ተማሪዎች ቢኖሩም ተማሪዎች ጋዜጠኛና ደራሱ እንዲሆኑ ከመምከር አኳያ ጎኑ ጎልቶ ተንጸባርቋል፡፡

4.6.7 **የአካባቢ ሰዎች "አማርኛ የጨቋኞች ቋንቋ ነው" እያሉ ይጠሉታል፡፡**

በዚህ ሀሳብ ላይ 7.1% "በጣም እስማማለሁ"፣ 4% "እስማማለሁ"፣ 11% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 16.2% "አልስማማም"፣ 61.7 "ፍጽም አልስማማም" በማለት መልሰዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 4.21 ነው፡፡

ከመረጃው ግልጽ ሆኖ እንደሚታየው 77.9% ተማሪዎች ሀሳቡን ሲቃወሙት 11.1% ብቻ ተቀብለውታል፡፡ ስለዚህ አብዛኛው ህብረተሰብ አማርኛን የጨቋኞች ቋንቋ አድርገው በማሰብ አይጠሉም፡፡

4.6.8 **ጓደኞቼ የአማርኛን ባህል ያደንቃሉ፡፡**

ለዚህ ሀሳብ 37.9% "በጣም እስማማለሁ"፣ 20% "እስማማለሁ"፣ 26.2% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 7.1% "አልስማማም" 8.8%፣ "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል፡፡ አማካይ ነጥቡ 3.71 ነው፡፡

የዚህ ሀሳብ ደጋፊዎች 57.9% ሲሆኑ ተቃዋሚዎች 15.9% ናቸው፡፡ መወሰን ያልቻሉ በርካታ ተማሪዎች ቢኖሩም የብዙ ተማሪዎች ጓደኞች የአማሮችን ባህል ስለሚያደንቁ በቀደምት ጽሁፋዊ መረጃዎች መሰረት አማርኛ ቋንቋም ያደንቃሉ ማለት ነው፡፡

4.6.9 **ጓደኞቼ አማርኛ ቋንቋን ይጠላሉ፡፡**

በዚህ ሀሳ ላይ 5% "በጣም እስማማለሁ"፣ 2.9% "እስማማለሁ"፣ 14.8 "መወሰን ያስቸግረኛ"፣ 24% "አልስማማም"፣ 53.3% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 4.19 ነው፡፡

በመረጃው መሰረት ሀሳቡ 77.3% ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ሀሳቡን የደገፉት 7.9% ብቻ ሲሆኑ ቀሪዎቹ መወሰን ያልቻሉ ናቸው፡፡ ስለዚህ የብዙሃን ተማሪ እኩዮችና ጓደኞች አማርኛ ቋንቋን አይጠሉም፡፡ ተጠያቅያዊ አካሄድ በ "1.6" ላይ በተገለጸው መሰረት ይሆናል፡፡

4.6.10 ጓደኞቼ ከሌሎች ቋንቋዎች ይበልጥ አማርኛን በስፋት ይጠቀማሉ፡፡

ለዚህ ሀሳብ 65.2% "በጣም እስማማለሁ"፣ 20% "እስማማለሁ"፣ 5.5% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 3.6% "አልስማማም"፣ 5.7% "ፍጹም አልስማማም" ብለዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 4.35 ነው፡፡

ከመረጃዎቹ በግልጽ እንደሚታየው 85.2% ተማሪዎች በሀሳቡ ላይ ሲስማሙ 9.3% ብቻ አልተስማሙም፡፡ መወሰን ያልቻሉትም በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡ ስለዚህ ብዙሃኑ የተማሪ ጓደኞችና እኩዮች ከሌሎች ቋንቋዎች ይበልጥ አማርኛን በስፋት ይጠቀሙበታል፡፡

4.6.11. ጓደኞቼ "የአማርኛ ትምህርት ቀላል ነው" እያሉ ይንቃሉ፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ 19% "በጣም እስማማለሁ"፣ 14.8% "እስማማለሁ"፣ 15.2% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 23.3% "አልስማማም"፣ 27.6% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.26 ነው፡፡

መረጃዎቹ እንደሚጠቁሙት 50.9% መላሾች ሀሳቡን አልተቀበሉትም፡፡ ሀሳቡን የደገፉት 33.8% ሲሆኑ ቀሪዎቹ መወሰን ያልቻሉ ናቸው፡፡ ስለዚህ አማርኛ ቋንቋ በብዙ የተማሪ ጓደኞችና እኩዮች ዘንድ አይናቅም፡፡

በዚህ ተላውጦ ላይ ከቀረቡ አስራ ሁለት ጥያቄዎች ከአንዱ በስተቀር ሌሎቹ ሁሉ አዎንታዊ ሆነው ተመልሰዋል፡፡ ስለዚህ የተማሪ ወላጆች ህብረተሰቡን እኩዮች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አዎንታዊ አመለካከት አላቸው ማለት ነው፡፡

የዚህ ተላውጦ (ሁለት) አማካይ ነጥብ 3.73 ሲሆን ለዝርዝሩ አባሪ "ረ" ይመልከቱ፡፡

## 4.7. ትምህርት ቤቶችን መማሪያ ክፍሎችን፣ ድጋፍ ሰጪ ነገሮችን የማስተማር ዘዴዎችን በተመለከተ፡፡

በዚህ ተላውጦ ስር በርዕሱ የተጠቀሱት አራት ጉዳዮች ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡ አራቱንም ጉዳዮች በተመለከተ አስራ ሁለት አውንታዊና አሉታዊ ሀሳቦች ተደባልቀው የቀረቡ ሲሆን ዝርዝሩ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

4.7.1. በመማሪያ ክፍላችን በቂ መቀመጫ ስላ ተዝናንተን እንቀመጣለን፡፡

በዚህ ሀሳብ 25% "በጣም እስማማለሁ"፣ 18.3% "እስማማለሁ"፣ 7.4% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 13.3% "አልስማማም"፣ 36.2% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል አማካይ ነጥቡም 2.83 ነው፡፡

ከመረጃዎቹ መረዳት እንደሚቻለው በሀሳቡ ላይ ከተስማሙት መላሾች ይልቅ የተቃወሙት በልጠው ተገኝተዋል፡፡ ተስማሚዎ 43.3% ሲሆኑ ተቃዋሚዎቹ 49.3% ናቸው፡፡ አማካይ ነጥቡም ምላሹ በአሉታዊ ክልል ውስጥ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተዝናንተው ሊቀመጡ አልቻሉም፡፡

4.7.2. የአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በአጉል ሰዓት ሻይ ስለሆነ የመማሪያ ክፍሉ ሙቀት ያስጨንቀናል፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ 18.6% "በጣም እስማማለሁ"፣ 11.4% "እስማማለሁ"፣ 15.5% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 26.9% "አልስማማም"፣ 27.6% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል አማካይ ነጥቡም 3.34 ነው፡፡

በመረጃው መሰረት የተሰነዘረው ሀሳብ 30% ድጋፍ ሲያገኝ 54.5% ተነቅፏል፡፡ ስለዚህ በርካታ ተማሪዎች የመማሪያ ክፍሉ ሙቀት አያስጨንቃቸውም፡፡

4.7.3. በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የመማሪያ ክፍላችን ስነ ስርዓት በሚገባ ይጠበቃል፡፡

ለዚህ ሀሳብ 31.2% "በጣም እስማማለሁ"፣ 24% "እስማማለሁ"፣ 14.8% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 16% "አልስማማም"፣ 14% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል አማካይ ነጥቡም 3.42 ነው፡፡

መረጃው እንደሚጠቁመን 55.2% ወላጆች ሀሳቡን ተቀብለውታል፡፡ 30% መላሾች ሀሳቡን ቢቃወሙትም በብዙሃን ምስክርነት መሰረት በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የመማሪያ ክፍል ስነ ስርዓት ይጠበቃል፡፡

4.7.4. የክፍላችን ጥቁር ሰሌዳ ተበላሸ ስለሆነ ጽሁፍ አይቀበልም፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ 6.2% "በጣም እስማማለሁ"፣ 7.4% "እስማማለሁ"፣ 7.9% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 28.1% "አልስማማም"፣ 50.5% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል አማካይ ነጥቡም 4.09 ነው፡፡

በመረጃው መሰረት 78.6 መላሾች ሀሳቡን ውድቅ አድርገውታል፡፡ በሀሳቡ የተስማሙትም ሆኑ መወሰን ያልቻሉት ጥቂቶች ናቸው፡፡ ስለዚህ በየክፍሎቹ የሚገኙት ጥቁር ሰሌዳዎች ደህና ናቸው ማለት ነው፡፡

4.7.5. የአማርኛ መማሪያ ክፍላችን ብርድ በማያስገባ ተስማሚ ቦታ ላይ ይገኛል፡፡

ለዚህ ሀሳብ 23.1% "በጣም እስማማለሁ"፣ 22.6% "እስማማለሁ"፣ 16.9% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 18.1% "አልስማማም"፣ 19.3% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል አማካይ ነጥቡም 3.12 ነው፡፡

ይህ ሀሳብ 45.7% የተደገፈ ሲሆን 37.4% ተነቅፏል፡፡ አቋም ልወሰዱትም በረካታ ናቸው፡፡ ስለዚህ ደጋፊዎችና ተቃዋሚዎች ተቀራራቢ ቢሆኑም አማካይ ነጥቡ ለትንሽ ወደ አወንታዊነት አድልቶ ይታያል፡፡ ይህ ማለት በአማርኛ ትምህርት ክፍል ውስጥ ከሚበርዳቸው ተማሪዎች የማይበርዳቸው ይበዛሉ ማለት ነው፡፡

4.7.6. የአማርኛ ትምህርት በልዩ መረጃ መሳሪያ ቀርቦልን አያውቅም፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ 42.6% "በጣም እስማማለሁ"፣ 22.1% "እስማማለሁ"፣ 88% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 10.5% "አልስማማም"፣ 16% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል አማካይ ነጥቡም 2.35 ነው፡፡

ከመረጃው እንደምንረዳው 64.7% መላሾች ሀሳቡን የደገፉ ሲሆን 26.5% ተቃውመውታል፡፡ ስለዚህ በብዙሃን ምስክርነት መሰረት የአማርኛ ትምህርት በልዩ መረጃ መሳሪያ አይቀርብም፡፡

4.7.7. የአማርኛን ትምህርት በተለያዩ ዘዴዎች ስለምንማር ይስበናል፡፡

ለዚህ ሀሳብ 19.8% "በጣም እስማማለሁ"፣ 20.7% "እስማማለሁ"፣ 15% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 20.7% "አልስማማም"፣ 23.8% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል አማካይ ነጥቡም 2.92 ነው፡፡

የቀረበው ሀሳብ 40.5% ሲደግፍ 44.5% ተነቅፏል፡፡ ቀሪዎቹ ለትንሽ ተቃዋሚዎች ስለበለጡ አማካይ ነጥቡ ወደ አሉታዊ ክልል አጋድሎ ይታያል፡፡ ስለዚህ የአማርኛን ትምህርት በተለያዩ ዘዴዎች ስለማይማሩ ብዙ ተማሪዎች አይሳቡም፡፡

4.7.8. የአማርኛ ትምህርት የአቀራረብ ዘዴን ትምህርቱን እንዲጠላ አድርጎኛል፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ 13.6% "በጣም እስማማለሁ"፣ 11% "እስማማለሁ"፣ 15.5% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 31.2% "አልስማማም"፣ 28.8% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል አማካይ ነጥቡም 3.51 ነው፡፡

መረጃው እንደሚያሳየው ይህ አሉታዊ ሀሳብ 60% የተነቀፈ ሲሆን 24.6% ተደግፏል፡፡ በዚሁ ተላውጦ በ "5.6" እና በ "5.7" ላይ በቀረቡት መረጃዎች መሰረት የአማርኛ ትምህርት በልዩ መረጃ መሳሪያና በተለያዩ ዘዴዎች አይቀርብላቸውም፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህኛው መረጃ እንደምንረዳው የቱንም ያህል የአቀራረብ ዘዴው ደካማ ቢሆን ተማሪዎች ትምህርቱን እንዲጠሉ አላደረገም፡፡

4.7.9. ትምህርት ቤታችን ወቅታዊ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ስለሚያቀርብልን ለአማርኛ ትምህርት እየተበረታታን ነው፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ 7.9% "በጣም እስማማለሁ"፣ 9.8% "እስማማለሁ"፣ 11.7% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 22.4% "አልስማማም"፣ 48.3% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል አማካይ ነጥቡም 2.06 ነው፡፡

ከመረጃዎች ግልጽ ሆኖ እንደሚታየው የተሰነዘረው ሀሳብ 17.7% ብቻ ሲደገፉ 70.7 ተነቀፏል፡፡ ስለዚህ ትምህርት ቤቶች ወቅታዊ ጋዜጣዎችንና መጽሔቶችን እያቀረቡ ተማሪዎችን ለአማርኛ ትምህርት አያበረታቱም፡፡

4.7.10. በትምህርት ቤታችን ቤተመጽሐፍት የአማርኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላት ባለመኖራቸው ተቸግረናል፡፡

ለዚህ ሀሳብ 21.9% "በጣም እስማማለሁ"፣ 11% "እስማማለሁ"፣ 19.3% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 23.3% "አልስማማም"፣ 24.5% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል አማካይ ነጥቡም 3.18 ነው፡፡

በመረጃው መሰረት በሀሳቡ ላይ የተሰማሙት 32.9% ሲሆኑ ያልተስማሙት 47.8% ናቸው፡፡ አቋም ያልወሰዱ ተማሪዎች በርካታ ናቸው፡፡ ያም ሆነ ይህ በትምህርት ቤታቸው መዝገበ ቃላት አጥተው ከሚቸገሩት ተማሪዎች የማይቸገሩት በርክተው ተገኝተዋል፡፡

4.7.11. በትምህርት ቤታችን ቤተ መጽሀፍት የአማርኛን ትምህርት የሚያግዙ በቂ ልቦለድና ልቦለድ ያልሆኑ መጻህፍት አሉ፡፡

በዚህ ሀሳብ ላይ 24.8% "በጣም እስማማለሁ"፣ 21.7% "እስማማለሁ"፣ 20.2% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 14.3% "አልስማማም"፣ 19% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል አማካይ ነጥቡም 3.19 ነው፡፡

ከመረጃው እንደሚታየው 46.5% መላሾች ሀሳቡን ሲቀበሉ 33.3% አልተቀበሉትም፡፡ አቋም ያልወሰዱ ተማሪዎችም በርካታ ናቸው፡፡ ስለዚህ በብዙዎች ግምት የአማርኛን ትምህርት የሚያግዙ በቂ ልቦለድና ልቦለድ ያልሆኑ መጽሀፍት አሉ፡፡

4.7.12. በትምህርት ቤታችን የአማርኛን ትምህርት የሚያግዙ በቂ ክበባት አልተቋቋሙም፡፡

ለዚህ ሀሳብ 33.6% "በጣም እስማማለሁ"፣ 18.6% "እስማማለሁ"፣ 11.4% "መወሰን ያስቸግረኛል"፣ 16.7% "አልስማማም"፣ 19.8% "ፍጹም አልስማማም" በማለት መልሰዋል አማካይ ነጥቡም 2.70 ነው፡፡

በመረጃው መሰረት 52.2% መላሾች ሀሳቡን ሲደግፉ 36.5% ተቃውመውታል፡፡ ስለዚህ በብዙሃ ሀሳብ መሰረት በትምህርት ቤቶች የአማርኛን ትምህርት የሚያግዙ በቂ ክበባት አልተቋቋሙም፡፡

## 4.8. የተማሪዎች አስተያየት

በመጠይቁ ላይ ከአምስቱ ተላውጦች መጨረሻ ላይ ተማሪዎች ፍላጎታቸውንና ስሜታቸውን በተመለከተ አጠቃላይ አስተያየት እንዲሰጡ ሁለት ጥያቄዎች የቀረቡላቸው ሲሆን የተገኙትን መላሾች ከሰንጠረዥ አስራ አንድና አስራ ሁለት ይመልከቱ፡፡

ሠንጠረዥ አስራ አንድ

ሀ. የአማርኛ ቋንቋ የምትወዱ ከሆነ ከምን ዓይነት ዘዴ መማር ትፈልጋላችሁ?

| ተ.ቁ | የቀረቡት ዘዴዎች | ደግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|---|
| 1 | በተለያዩ ልቦለዶችና ልቦለድ ባልሆኑ መጽሐፎች ተደግፎ ሲቀርብ | 141 | 33.6 |
| 2 | ቅኔና ምሳሌያዊ አነጋገሮች ትኩረት ተሰጥቷቸው ሲቀርቡ | 60 | 14.3 |
| 3 | በቀልድና በድራማ መልክ ቢቀርብ | 35 | 8.3 |
| 4 | በዘይቤያዊና በፈሊጣዊ አነጋገር ታጅቦ ቢቀርብ | 29 | 6.9 |
| 5 | አሁን ባለው መልኩ ይቀጥል | 20 | 4.8 |
| 6 | በመጽሐፎችና በጋዜጦች ተደግፎ ቢቀርብ | 19 | 4.5 |
| 7 | ሰዋሰዋዊ ትምህርት በልዩ ዘዴ ቢቀርብ | 17” | 4 |
| 8 | በተለያዩ መረጃ መጽሀፎች ተደግፎ ቢቀርብ | 16 | 3.8 |
| 9 | ለማትሪክ ፈተና የሚጠቅሙ ነጥቦች ተለቅመው ቢቀርቡልን | 16 | 3.8 |
| 10 | በጥያቄና መልስ መልክ ቢቀርብ | 14 | 3.8 |
| 11 | በውይይትና በክርክር መልክ ቢቀርብ | 11 | 2.6 |
| 12 | በቂ ዕውቀት ባለው የአማራ ተወላጅ ቢቀርብ | 5 | 1.2 |
| 13 | የቃላት ትምህርት3 ቢተኩርበትና በመዝገበ ቃላት ቢታገዝ | 5 | 1.2 |
| 14 | በግጥምና በስነ ቃሎች ታጅቦ ቢቀርብ | 2 | 0.5 |
| 15 | በሬዲዮና በቴሌቪዥን እየታገዘ ቢቀርብ | 2 | 0.5 |
| 16 | ድርሰቶችን እየፃፍን እንድንለማመድ ቢደረግ | 1 | 0.2 |
| 17 | በቂ የክፍልና የቤት ስራዎች ቢሰጠን | 1 | 0.2 |

በሠንጠረዥ አስራ አንድ ላይ የቀረበው መረጃ መሰረት በርካታ መለሾች ከጠቀሱት ዘዴዎች ዋና ዋናዎቹ፡-

- የአማርኛ ትምህርት በተለያዩ ልቦለድ ጽሁፎች እንደደገፍ፣
- ቅኔያዊ፣ ምሳሌያዊ፣ ዘይቤያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮች እንዲኮርባቸው፣
- ትምህርቱ ተማሪዎችን መሳብ እንዲችል በቀልድና በድራማ መልክ እንዲቀርቡ፣
- መጽሔቶችና ጋዜጦች ተጨማሪ የትምህርት መሳሪያ እንዲሆኑ፣
- የሰዋሰው ትምህርት በማይከብድ ልዩ ዘዴ እንዲቀርብ፣
- ትምህርቱ በልዩ መረጃ መማሪያ እንዲደገፍ የሚሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ደግሞ በመምህራን እጅ ያሉና በታታሪዎ ሁሉ ሊተገበሩ የሚችሉ ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ አስራ ሁለት

ለ. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የማትወዱ ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው?

| ተ.ቁ | የቀረቡ ምክንያቶች | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|---|
| 1 | መጽሐፉ ስድ ጽሁፍና መልመጃ ስለሚበዛው | 21 | 5 |
| 2 | ከአንድ መጽሐፍ ስለምንማርና ተጨማሪ ባለመኖሩ | 20 | 4.8 |
| 3 | የመምህሩ አቀራረብ ስለማይስበን ስለማይማርከን | 20 | 4.8 |
| 4 | የሰዋሰው ትምህርት ስለሚከብደኝ | 7 | 1.7 |
| 5 | የትምህርት አቀራረብ ዘዴው አሰልቺ ስለሆነ | 6 | 1.4 |
| 6 | ብዙ አሰልቺ ቃላትን ስለያዘ | 4 | 1 |
| 7 | ትምህርቱ ስለሚከብድ | 3 | 0.7 |
| 8 | ቅኔ ስለማይገባኝ | 3 | 0.7 |
| 9 | ቋንቋዬ ስለሆነና ተራ ሆኖ ስለታየኝ | 2 | 0.5 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 10 | ትምህርቱ ፈተናው ስለማይገናኝ | 2 | 0.5 |
| 11 | ምሳሌያዊ አነጋገርና የቅኔ ትምህርት በጥሩ ዘ ዴ ስለማይቀርቡ | 1 | 0.2 |
| 12 | ምንም ስሜት ስለማይሰጠኝ | 1 | 0.2 |

በሠንጠረዥ አስራ ሁለት መሰረት ከ1-3 የተጠቀሱት የጥላቻ ምክንያቶች፣ የመጽሐፉ የይዘት ምርጫ አለመስተካከልና ተጨማሪ ነገር አለመኖር እንዲሁም የመምህሩ የአቀራረብ ድክመት ናቸው፡፡ እነዚህ ደግሞ በቀላሉ ሊስተካከሉ የሚችሉ ነገሮች በመሆናቸው ጥላቻው ሊቀንስ ወይም ሊወገድ ይችላል ማለት ነው፡፡

## 4.9. የምላሾች ንጽጽር

በእያንዳንዱ ተለውጦ ላይ የሁለት መቶ ሰላሳ ተማሪዎች ምላሽ ከአነሰተኛው እስከ ከፍተኛው ድረስ የተገኘው ነጥብ ከትምህርት ቤት፣ በጾታ፣ በብሔረሰብና በትምህርት ዘርፋቸው አኳያ ተለያይቶ በሰንጠረዥ ተሰርቷል፡፡ /የትምህርት ቤቶችን ውጤት በተመለከተ፣ አባሪ "በ" ከ1-5፣ ከጾታ፣ ከብሔረሰብ ከትምህርት ዘርፍ አኳያ የተገኙ ውጤቶችን በተመለከተ፣ አባሪ "ተ" ከ1-5 ይመልከቱ/፡፡ ሰንጠረገሮቹን በማየት በእያንዳንዱ ነጥብ ላይ የመላሾችን ብዛት ማነፃፀር ይቻላል፡፡ ንጽጽሩ ይበልጥ ሳይንሳዊና አሳማኝ እንዲሆን በተለያዩ በታቲስቲካዊ ስሌቶች ተሰርቶ ቀርቧል፡፡

በዚህ መሰረት በአምስቱም ተለውጦዎቹ ላይ፡-

- በሁለት ትምህርት ቤቶቹ ምላሾች መካከል፣
- በወንዶችና በሴቶች ምላሾች መካከል፣
- በዘጠነኛና በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ምላሾች መካከል ከታትስቲካዊ ፋይደ ያለው ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ በኮምፒውተር አማካይት ስሌቱ ተሰርቶ እንዲነፃፀሩ ተደርጓል፡፡ /የተሰራው በ"አናቫ" ስሌት ነው/

በሌላም በኩል ከሁለት እስከ አምስት ያሉት ተላውጦች ከዋነኛው ተላውጦ አንድ ጋር የውጤት ተመሳሳይነት እንዳላቸውና እንደሌላቸው ለማወቅ በ"ቲ-ቴስት" አማካይነት እንዲነጻጸሩ ተደርጓል፡፡

በመጨረሻም የየተላውጦው ምላሽ ተጣምሮ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ የ"ካይ ስኳር" ስሌት ተሰርቶ የቀረበ ሲሆን የሁሉንም ንጽጽራዊ ውጤቶች እንደሚከተለው እናቀርባለን፡፡

4.9.1. የትምህርት ቤቶች ምላሽ ንጽጽር

በተላውጦ አንድ፣ ሁለት፣ አራትና አምስት ስሌት መሰረት የ"ኤፍ" ሬሺዮ እንደ ቅደም ተከተላቸው "1.21፣ 1.40፣ 0.48፣ 1.21" ሲሆን በ"0.05" የፋይዳ እርከን ላይ የተገኘው ነጥብ "3.84" ነው፡፡ ከሁሉም ተላውጦዎች የ"ኤፍ" ---- ከ "አልፊው" ነጥብ /3.84/ ያነሰ በመሆኑ በተጠቀሱት ተላውጦዎ ላይ በትምህርት ቤቶች ምላሽ መካከል ስታትስቲካዊ ፋይዳ ያለው ልዩነት የለም፡፡ ይህ ማለት የትምህርት ቤቶችና የቤተሰብ ሁኔት መለያየት በተማሪዎቹ አመለካከት ላይ ለውጥ አላመጣም፡፡

በተለውጦ ሶስት ላይ በተሰራው ስሌ መሰረት የ "ኤፍ" ሬሸየም 14.62" ሲሆን በ"0.05" የፋይዳ እርከን ላይ የተገኘው ነጥብ "3.84" ነው፡፡ የ "ኤፍ" ዋጋ ፋይዳ ያለው ልዩነት አለ ማለት ነው፡፡ ተላውጦ ሶስት መምህራንን የሚመለከት ሲሆን የመምህራንን አመለካከት፣ ችሎታና ጠባይ በተመለከቱ በትምህርት ቤቶች ምላሽ መካከል ልዩነት መኖር የመምህራኑ ችሎታ፣ ጠባይና አመለካት ከትምህርት ቤቶች ምላሽ መካከል ልዩነት መኖሩ የመምህራ ችሎታ፣ ጠባይና አመለካከት ከትምህርት ቤት ትምህርት ቤት የተለያየ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህ ደግሞ ሊሆን የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ ዞሮ ዞሮ ግን መምህራንን በተመለከተ ከሁሉም ትምህርት ቤቶች የተገኘው መረጃ አዎንታዊ ነው፡፡

4.9.2. የወንዶችና የሴቶች ምላሽ ንጽጽር

ከተላውጦ አንድ እስከ አምስት ያሉት ሁለት ስታቲስቲካወ ስሌታቸው እንደሚያሳየው የ "ኤፍ" ሬሾዮ እንደቅደም ተከተላቸው "2.25፣ 1.66፣ 2.05፣ 3.03፣ 0.81" ሲሆን በ"0.0"" የፋይዳ እርከን ላይ የተገኘው ነጥብ "3.84" ነው፡፡ የሁሉም የ "ኤፍ" ዋጋ ከ "አልፋው" ነጥብ /3.84/ ያነሰ በመሆኑ በወንዶችና በሴቶች ምላሾች መካከል ስታትስቲካዊ ፋይዳ

ያለው ልዩነት የለም፡፡ ስለዚህ በአምስቱም ተላውጦዎች ላይ ጾታን ምክንያት ያደረገ ልዩነት እንደሌላ ፤ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 4.9.3. **የእኩዮች ተጽኖ ና የትምህርት ቤቶች ምላሽ ንጽጽር**

በተላውጦ አንድና ሁለት ስሌት መሰረት የ "ኤፍ" ሬሺዮ እንደቅደም ተከተላቸው "12.29፣ 10.33" ሲሆን በ "0.05" የፋይዳ እርከን ላይ የተገኘው ነጥብ "3.84" ነው፡፡ በሁለቱም ተላውጦዎች የ"ኤፍ" ዋጋ ከ "አልፋው" ነጥብ /3.84/ የበለጠ በመሆኑ በተላውጦ አንድና ሁለት ላይ በእኩዮች ተጽኖ ና የትምህርት ቤቶች ምላሾች መካከል ስታቲስቲካዊ ፋይዳ ያለው ልዩነት አለ ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል በተላውጦ ሶስት፣ አራትና አምስት ስሌት መሰረት የ "ኤፍ" ሬሽዮ እንደቅደም ተከተላቸው "0.20፣ 1.08፣ 0.0" ሲሆን በ "0.05" የፋይዳ እርከን ላይ ከሚታየው "3.84" ያነሱ በመሆናቸው በሶስቱም ተላውጦዎች በእኩዮች ተጽኖ ና የትምህርት ቤቶች ምላሾች መካከል ስታቲስቲካዊ ፋይዳ ያለው ልዩነት የለም፡፡

የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን፣ መማሪያ መጻህፍትን፣ ትምህርት ቤቶችን፣ መማሪያ ክፍሎችን፣ ድጋፍ ሰጪ ነገሮችንና የማስተማር ዘዴዎችን በተመለከተ የእኩዮች ተጽኖ በመኖርና ባለመኖር መካከል የምላሽ ልዩነት የለም፡፡ ነገር ግን የተማዎቹን የግል አመለካከት፣ የወላጆችንና የህብረተሰቡን እንዲሁም የመምህራና ጸባይ በተመለከተ የምላሽ ልዩነት አለ፡፡ ክፍላቸው እስከተለያየ ድረስ የምላሻቸው መለያየት ሊኖር ይችላል፡፡ ታዲያ በሁለቱም ተላውጦዎች ላይ የነጥብ አሰጣጥ ልዩነት ይኑር እንጂ የሁሉም ምላሽ አዎንታዊ ነው፡፡

## 4.9.4. **የተላውጦ አንድና የሌሎች ተላውጦዎች ንጽጽር**

በተላውጦ አንድና ሁለት እንዲሁም አንድና ሶስት መካከል የተሰራው ስሌት እንደሚያመለክተው የ "ቲ" ዋጋ እንደ ቅደም ተከተላቸው "1.49" እና "1.45" ነው፡፡

በ "0.05" የፋይዳ እርከን ላይ የተገኘው ነጥብ ደግሞ "1.96" ሲሆን የሁለቱም የ "ቲ" ዋጋ ከ "አልፋው" ነጥብ /1.96/ ያነሰ ነው፡፡ ስለዚህ በተላውጦ አንድና ሁለት እንዲሁም አንድና ሶስት ምላሾች መካከል ስታቲስቲካዊ ፋይዳ ያለው ልዩነት በተላውጦ አንድና አራት እንዲሁም አንድና አምስት መካከል የተሰራው ስሌት እንደሚያሳየው  የ"ቲ" ዋጋ እንደ

ቅደም ተከላቸው "13.36" እና "19.5" ነው፡፡ በ "0.05" የፋይዳ እርከን ላይ የተገኘው ነጥብ "1.96" ሲሆን የሁለቱም የ "ቲ" ዋጋ ከ "አልፋው" /1.96/ የበለጠ ነው፡፡ ስለዚህ በተላውጦ አንድና አራት እንዲሁም አንድና አምስት ምላሾች መካከል ስታቲስቲካዊ ፋይዳ ያለው ልዩነት አለ ማለት ነው፡፡

## 4.10 የተላውጦዎች ተጣምሮ

የተጣምሯዊ ስሌት ውጤት ወደ አሉታዊ አንድ /-1/ እየራቀ ከሄደ ተጣምሮ አሉታዊ መሆኑን ሲያመለክት ወደ አዎንታዊ አንድ /1/ እየቀረበ ከሄደ ተጣምሮው አዎንታዊ መሆኑን ያሳያል፡፡ በዚህ መሰረት ከአምስቱም ተላውጦዎ የተገኙት ምላሾች እርሰ በርስ ሲነፃፀሩ ሁሉም አዎንታዊ ተጣምሮነት ያላቸው ሲሆን በተለይ በተላውጦ አንድና ሁለት ማለትም በተማሪው ግላዊ አመለካከትና በወላጆች በህብረተሰቡና በእኩዮች ምላሾች መካል ከሁሉም የተሻለ ተጣምሮነት ታይቷል፡፡ የስሌቱም ይዘት "0.55" ሲሆን ከአሉታዊ አንድ ወደ አዎንታዊ አንድ የቀረበ ነው፡፡ ለዝርዝሩ የሚከተለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ፡፡

ሠንጠረዥ አስራ ሦስት

የተላውጦዎች የእርስ በርስ ተጣማሪነት

| ተላውጦዎች | ተላውጦዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 1 | 1.00 | 0.55 | 0.26 | 0.35 | 0.12 |
| 2 | 0.55 | 1.00 | 0.21 | 0.32 | 0.11 |
| 3 | 0.26 | 0.21 | 1.00 | 0.30 | 0.30 |
| 4 | 0.35 | 0.32 | 0.30 | 1.00 | 0.40 |
| 5 | 0.12 | 0.11 | 0.31 | 0.40 | 1.00 |

## 4.11 ቃለመይቃዊ መልሶች

አጥኚው በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ከሚገኙት የዘጠነኛ ና የአስረኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን ጋር ቃለመጠይቃዊ ውይይት አድርጓል፡፡ ቃለመጠይቁ ስድስት ጥያቄዎችን ያቀፈ ሲሆን ጥያቄዎቹና መልሶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ምን ዓይነት አመለካከት አላቸው?

ለዚህ ቃለመጠይቅ ሶስት መልሶች ተመዝግበዋል፡፡

ሀ. በአማርኛ ቋንቋ ላይ አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ጥቂት ተማሪዎች ቢኖሩም አብዛኛዎቹ ጥሩ አመላካከት አላቸው /ሰባት መላሾች/ 58.3/ ይህ መልስ ሰጥተዋል/

ለ. በአሁኑ ጊዜ ብዙ ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጠው ትምህርት አልገባ አያላቸው "ገብተን የምንማረው አማርኛ ብቻ ነው" እያሉ በጥሩ ስሜት እየተማሩ ነው፡፡ /ሶስት መላሾች/ 25% ይህን መልሰዋል/

ሐ. ተማሪዎች በሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ላይ ከሚያሳዩት ባህርይ የተለየ በአማርኛ ቋንቋ ላይ የሚያሳዩት ነገር የለም፡፡ /ሁለት መልሶች /16.7/

2. ተማሪዎች የአማረኛን ትምህርት እንዴት ይቀበላሉ?

ለዚህ ቃለመጠይቅ ሁለት መልሶች ተሰጥተዋል፡፡ አብዛኛዎቹ መላሾች ሁለቱንም ሀሳቦች ሲያቀርቡ ጥቂቶቹ አንዱን ብቻ አቅርበዋል፡፡

ሀ. ለተማሪዎች የአማርኛ ትምህርት አቀባበል ወሳኙ የመምህሩ አቀራረብ ነው፡፡

መምህሩ በመጽሐፉ ላይ ብቻ ሳይወሰን የተማሪዎችን ፍላጎትና ስሜት እየተቆጣጠረ ሳይጨነቁና ሳይጠበቡ በሳቅና በፈገግታ እንዲማሩ የሚያደርግ ከሆነ ከፍለ ጊዜውን በጉጉት የሚጠቀብቁትና የሚወዱት ይሆናል፡፡ ተማሪዎች ጥሩ መምህር ካገኙ የአማርኛን ትምህርት በደንብ ይቀበላሉ፡፡ /አስራ ሁለቱም መላሾች/ 100%/ የሰነዘሩት ሀሳብ/

ለ. አብዛኛዎቹ በጥሩ ሁኔታ የሚቀበሉ ሲሆን ጥቂቶቹ ብቻ "እናውቃለን"፡፡

በሚል ስሜት ትምህርቱን የሚንቁ ይመስላሉ፡፡ ጥቂቶቹ ደግሞ የብሔረሰብባቸውና የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ካለመሆኑ የተነሳ እንዲሁ የሚወሉት ይመስላሉ፡፡ ያም ሆነ ይህ

የሚንቁትና የሚጠሉት ተማሪዎች ከሚወዱት ጋር ሲነፃፀሩ እምንት በመሆናቸው የጉላ ችግር ሆኖ አይቀርብም፡፡ እነሱም ቢሆኑ በመምህራን አቀራረብ ሊስተካከሉ ይችላሉ፡፡ /ስምነት መላሾች/ 66.7%/

3. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ትልቁ ችግር ምንድነው? በዚህ ቃለመጠይቅ ላይ ሶስት መልሶች ቀርበዋል፡፡

ሀ. የተማሪዎች ከአንደኛ ደረጃ ጥሩ መሰረት ይዞ አለመምጣትና ከደረጃ በታች ሆኖ መገኘት በመምህራን አቀራረብ ላይ ትልቅ ችግር ፈጥሯል፡፡ አብዛኛዎ ተማሪዎች ደረጃቸውን በመወሰን መልኩ ማንበብና መፃፍ አይችሉም፡፡ /ዘመን መላሾች/75%

ለ. ጥቂቶቹም ቢሆኑ በቋንቋው ላይ ንቀትና ጥላቻ ያላቸው ተማሪዎች እንዲሁም የትምህርት ቤት መሪዎች በግልጽና በስውር ከሚሰነዝሩትዘለፋ የተነሳ አንዳንድ መምህራን በወኔ የመስራት የራሳቸው ወድቋል፡፡ /ስድስት መላሾች/ 50%

ሐ. የማትሪክ የአማርኛ ጥያቄዎችና የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ትምህርት አለመጣጣማቸው በመጠኑም ቢሆን ተማሪዎች ለክፍል ትምህርት ያላቸውን ትኩረት እንዲቀንሱ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ /አስማት መላሾች/ 41.7%

4. አሁን በስራ ላይ ስላለው የአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ምን አስተያየት አለዎት? ለዚህ ቃለመጠይቅ ስድስት መላሾች /100%/ “የአሁኑ መጽሀፍ ከበፊቱ የተሻለ ቢሆንም ብዙ ጎድለቶች አሉ” ካሉ በኋላ የሚከተሉትን ምክንያቶች አቅርበዋል፡፡

ሀ. መጽሐፉ በምንባቦች ምርጫም ሆነ በአቀራረቡ ተማሪዎችን የመሳብ አቅም የለውም፡፡ /አራት መላሾች/ 80%

ለ. በርካታ ርዕሶች በዘጠነኛ ክፍል የቀረቡ ሆነው በአስረኛም ስለሚሰጡ አሰልቺ ይሆናሉ፡፡ ለምሰሌ ምሳሌያዊ አነጋገር፣ ዘይ፣ ቅኔ፣ የስም ገላጭ፣ የግስ ገላጭ፣ የግጥም ዓይነቶችና ስያሜዎች ወዘተ. ተደጋጋሚዎች ናቸው፡፡ /ሶስት መላሾ/ 50%

ሐ. የይዘቶች ተከታታይነቱ የተዛባ ነው፡፡ /ሁለት/ 41.7%

መ. ከተማሪዎች ደረጃ ላይ የከባዱ ነጥቦችም አሉ /አንድ መላሽ /33.3%/

5. ወደፊት የሚዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት በማንና እንዴት ቢዘጋጁ ይሻላል?

5.1. ዝግጁቱን በተመለከተ

ሀ. ከዘጠነኛ እስከ አስረኛ ክፍል በየክፍሉ የሚቀርቡት ይዘቶች በየክፍሉ የሚቀርቡ ይዘቶች የተለያዩና ተከታታይነት ያላቸው ቢሆኑ/ሰባት መላሾች / 58.31/

ለ. ሁሉንም የቋንቋ ዘርፎች አመጣጥነው የያዙ ቢሆኑ /አምስት መላሾች /41.71/

ሐ. የምንባቦች ምርጫ ወደ ልበወለዶች ያዘነበለ እና ተማሪዎችን መሳብ የሚችል ቢሆን / አራት መላሾች /33.31/

መ. ተቆርጠው የሚወሰዱ ምንባቦች ምንጫቸው በተገቢው መልክ ቢጠቀስ፡፡ ምክኒያቱም አንዳድ ቀንደል ሃሳቦችን መረዳት ስለሚያስቸግር መምህሩ ሙሉውን ጽሑፍ አንብቦ መረዳትና መግለጽ እንዲችል ነው፡፡ / ሁለት መላሾች / 16.7

ሠ. የመምህር መምሪያ ያለውና በክፍለ ግዜ የተከፈለ ቢሆን / አንደ መላሽ /8.3/

6. ተማሪዎች በአማረኛ ቋንቋ ትምህርት እንዲማረኩና በደስታ እንዲማሩ ምን መደረግ አለበት  ለዚህ ቃለመጠየቅ ስድስት ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

ሀ. ተማሪዎች መማር የሚፈልጉትን ይዘቶች በፍላጎታው መሰረት መምረጥና አቅልሎ ማቅረብ /ዘጠኝ መላሾች/ 75/

ለ. መምህራን ዝግጅታቸውን ማሳመርና የአቀራረብ ስልታቸው አሰልቺ እንዳይሆን መቀያየር / ሰባት መላሾች/ 58.3%/

ሐ. ልበወለድ ጽሁፎችን ለተለያዩ የአማረኛ ትምህርት ዘርፎች የማስተማሪያ ጽሑፎች አድርጎ መጠቀም /አምስት መላሾች /41.7%/

መ. በክፍሉ መጽሐፍ ላይ ብቻ አለመወሰንና ወቅታዊ ነገሮችን ከጋዜጦችና ከመጽሔቶች ፈላልጎ ማቅረብ / አምስት መላሾች /41.7%/

ሠ. የተማሪዎችን ሞራል የሚነኩ ቃላትን አለመናገር እና አፀያፊ ተግባራትን አለመፈፀም/ ሶስት መላሾች/25 %/

ረ. ስለ አማርኛ ቋንቋ የተዛባ አመላካከት ያላቸው ተማሪዎች መለወጥ

/ሁለት መላሾች /16.7%/

## 4.12 ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች ንፅፅር

1. በ1፡2 ላይ ለተማሪዎች የቀረበው ጥያቄ ‹‹ ግድ ሆኖብኝ እንጂ አማርኛ መማር አልፈልግም›› የሚል ሲሆን 82.2% ተማሪዎች ተቃውመውታል፡፡ ስለዚህ ‹‹ ተማሪዎች አማርኛን መማር ይፈልጋሉ›› ብለን ነበር፡፡ ከመምራን የተነኘው መረጃም ‹‹ ተማሪዎች ጥሩ መምህር ካገኙ የአማርኛ ትምህርት በደንብ ይቀበላሉ›› የሚል ስለሆነ መረጃዎቹ ተመሳሳይ ናቸው፡፡

2. በ1፡4 ላይ ለተማሪዎች የቀረበው ጥያቄ ‹‹ የአማርኛ ትምህርት ስለሚቀለኝ እንቀዋለው ›› የሚል ሲሆን የተገኘው መልስ 80.5% ተቃውሞ ነው፡፡ ስለዚህ ‹‹ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አማርኛን አይንቁም›› ብለን ነበር፡፡ ከመምራን የተገኘው መረጃዎች ‹‹ ጥቂቶች ብቻ እናውቃለን›› በሚል ስሜት የሚንቁ ይምሰሉ እንጂ ‹‹አብዛኛዎቹ በጥሩ ሁኔታ ይቀበላሉ›› ስለሚል መረጃዎቹ ተመሳሳይ ናቸው፡፡

3. በ‹‹1.6›› ላይ ለተማሪዎች የቀረበው ጥያቄ "አማርኛ ቋንቋ ያስጠላኛል" የሚል ሲሆን 91% ተቃውሞ ገጥሞታል፡፡ በዚህ መሰረት አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አማርኛን እንደማይጠሉ አረጋግጠዋል፡፡ የኸው ጥያቄ በ"2.10" ላይ "ጓደኞቼ አማርኛ ቋንቋን ይጠላሉ"በሚል መልክ የቀረበ ሲሆን 77.3% ተቃውሞ ገጥመውታል፡፡ ከዚህም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አማርኛን እንደማይችሉ አረጋግጠናል፡፡ ከመምህራን የተገኘ መረጃም ከጥቂት በስተቀር አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በአማረኛ ላይ ጥሩ አመለካከት አላቸው ስለሚል መረጃዎቹ ተደጋጋፊ ናቸው፡፡

4. 1.13 ላይ ተማሪዎች ደስ ብለቀዋቸው የሚማሩትን የአማርኛ ትምህርት ርእሶች እንዲመርጡ በተጠየቀው መሰርት ‹‹ ልቦለድን ማዳመጥ›› የሚለው አንደኛ ሆኖ የተመረጠ ሲሆን ከመምራን የተገኘው መረጃም በመፃፍት ዝግጅት ወቅት የምንባቦች ምርጫ ወደ ልቦለድ ፅሁፎች እንዲያዘነብልና ልቦለድ ፅሁፎችን ለተለያዩ የአማርኛ ትምህርት ዘርፎች መጠቀም ተማሪዎችን እንደሚማርክ ይጠቁማል፡፡ ስለዚህ የተማሪዎች ምርጫና የመምህራን ጥቆማ ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

መማሪያ መፅሀፍትን አስመልክቶ ከተማሪዎች የተገኘ መረጃ እንደሚጠቁመን መፅሀፉ የቋንቋ ዘርፎችን አካቶ ያልያዘ ፣ ያላስተማሪ ተማሪዎችን መምራት የማይችል፣ የቃላት ዝርዝርና ትርጉማቸውን የማያሳይ ብቃት የጎደለው መሆኑን ነው፡፡ ከመምርራን የተገኘው መረጃ ደግሞ በጥቅሉ መፅሀፉ ከበፊቱ የተሻለ ቢሆንም ብዙ ድክመቶች እንዳሉበት ነው፡፡

ለምሳሌ ምንባቦች ተማሪዎችን መሳብ የማይችሉ፣ ቅደም ተከተላቸው ያልተስተካከለና ደረጃውን ያልመጠነ መሆናቸው በመምህራን ተገልጸዋል፣ ስለዚህ መረጃዎቹ ተመሳሳይ ናቸው፡፡

5 ‹‹ አማርኛን እንዴት ብትማሩ ትፈልጋላችሁ›› ተብሎ በማጠቃለያ ጥያቄ ‹‹ሀ›› ላይ ተማሪዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ ካቀረቡት በርካታ ሀሳቦች ዋነኞቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ❖ ትምህርቱ በልቦለድ ፅሁፎች ፣ እንዲሁም በመፅሄቶችና ጋዜጣዎች ተደግፎ ቢቀርብ ፣ በቀልድና በድራማ መልክ ተማሪን እንዲስብ ተደርጎ ቢሰጥ መምህራንን ፡-

  የአማርኛ ትምህርት እንዴት ቢቀርብ ተማሪዎቹ ተደስተው ይማራሉ /ተብሎ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ ሲመልሱ፡-

- ❖ ልቦለድ ፅሁፎችን ለተለያዩ የአማርና የትምህርት ዘርፎች የማስተማሪያ ጽሁፍ አድርጎ መጠቀም፣ ወቅታዊ ነገሮችን ከጋዜጦችና መጽሄቶች ለቃቅሞ ማቅረብ እንዲሁም መምህራን አቀራረባቸው አሰልቺ እንዳይሆን መቀያየር ተማሪዎችን እንደሚያስደስት ጠቅሰዋል፡፡

  እነዚህ ሀሳቦች ተመሳሳይ ሲሆኑ በሌላም በኩል አማርኛን የሚጠሉ ጥቂት ተማሪዎች ለትላቻቸው ምክንያት አድርገው የጠቀሱዋቸው ነጥቦች፡-

- ❖ መጽሀፉ ልቦለድ ያልሆኑ ጽሁፎችና መልመጃ ስለሚበዛው
- ❖ ከአንድ መጽሀፍ ብቻ ስለምንማርና ተጨማሪ ስለሌለው
- ❖ የመምህሩ አቀራረብ ስለማይስበንና ስለማይማርከን የሚሉ ናቸው፡፡

  ስለዚህ በሁሉም አቅጣጫ የተጠቀሱት ነጥቦች ተደጋጋፊ ሲሆኑ ተማሪዎች መማር የሚፈልጉት ፣ ትምህርቱ በልቦለድ ተደግፎ ሲቀርብ፣ ወቅታዊ ነገሮች ከጋዜጦችና መጽሄቶች ሲቸመሩ፣ መምህራን ትምህርቱ ሊስብ በሚችል መልኩ አዘጋጅተው ሲያቀርቡ ነው፡፡

## 4.13 የምልከታ ሪፖርት

አጥኚው የሁለቱንም ትምህርት ቤቶች ግቢና ቤተመጽሐፍት ተዛዙሮ የጎበኘ ሲሆን የአማረኛ ክፍለ ግዜ ትምህርታዊ ሂደቶችን የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በመገኘት ተመልክቷል፡፡

### 4.13.1 የት/ቤቶች ግቢና የቤተመጽሐፍት ሁኔታ

የጥናቱ ናሙና ትምህርት ቤቶች አብዛኛዎቹ ግቢያቸው በጣም ሰፊ ነው፡፡ በተለይ የሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ በጀርባ በኩል አጥር የሌለው ሲሆን የደነባው ሙሉ ለሙሉ የታጠረ ነው፡፡

ናሙና ት/ቤቶች ሁሉ ቤተ መጽሀፍት አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ ት/ቤቶቹ ወቅታዊ ጋዜጦችንና መጽሄቶችን እንዲሁም ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያግዙ አዳዲስ መጽሀፍት እየተከታተሉ አይገዙም፡፡ እደዚህም ሆኖ ቤተ/መጽሁፍቱ የሚናቁ አይደሉም፡፡

### 4.13.2 መማሪያ ክፍሎችና የትምህርት ሂደት

የመማሪያ ክፍሎቹን ስንመለከት አብዛኛዎቹ ከሚገባው በላይ በተማሪ ተጨናንቀው ይታያሉ ፡፡ ለምሳሌ አጥኚው ከጎበኛቸው ክፍሎች በአንድ ክፍል ያገኛቸው ተማሪዎች አነስተኛ ቁጥር ሰባ ስድስት ሲሆን ከፍተኛው ዘጠና አራት ነው፡፡ በርካታዎቹ ክፍሎች ከ ሰማኒያ እስከ አንድ መቶ አጭቀው ይዘዋል፡፡ ከተማሪዎቹ ብዛት የተሳ መቀመጫ በማነሱ ሶስት ሆነው ሁለት ወንበሮችን በመገጣጠም የተቀመጡበትም ክፍሎች አሉ፡፡

በተጎበኙት ሁሉም ክፍሎች ጥሩ የትምህርት ሂደት ይከናወን ነበር፡፡ ተማሪዎቹ በፀጥታ ይማራሉ፣ በቂ ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡ በርግጥ ከተለመደው የክፍሉ መጽሀፍ በስተቀር አንድም መምህር ልዩ መርጃ መሳሪያ ሲጠቀም አልታየም፡፡

## 4.14 የምልከታ ውጤትና የተማሪዎች ምላሽ ንፅፅር

የአጥኚው የምልከታ ውጤት ሊታይ ከሚችለው የተማሪዎች ምላሽ ጋር ሲነፃጸር ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ ነው፡፡ ለምሳሌ የመቀመጫ ማነስና መጨናነቅ፣ የተማሪዎች በጸጥታ መማር፣ የመምራን ልዩ መረጃ አለመጠቀም የት/ቤቶች ወቅታዊ መጽሄቶችና ጋዜጦችን

አለመግዛት እነዚህን ሁሉ በተመለከተ ከተማሪዎች የተገኙት መረጃዎችና አጥኚው በምልከታ ያገኛቸው መረጃዎች አንድ አይነት ናቸው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# 5. አጠቃሎ፣ ግኝትና አስተያየት

## 5.1 አጠቃሎ

በመግቢያው ክፍል እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋነኛው አላማ በሰኮሩና ደነባ ሁለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት ለማወቅ ሲሆን በዚህ አብይ አላማ ስር አምስት ዝርዝር አላማዎች የሚገኙ ሲሆን ለነዚህ ዝርዝር አላማዎች በጥናቱ የተገኙ ግኝቶችን ጠቅለል ባለ መንገድ እናያለን፡፡

- ❖ በቋንቋና በቋንቋ ትምህርት አመለካከት ዙሪያ የተገረጉ ጥናቶች ተከልሰዋል፡፡ በዚህ መሰረት ተማሪው በቋንቋና በቋንቋ ትምህርት ላይ ሊኖረው የሚገባውን አመለካከት የሚወስኑ በርካታ ነገሮች መኖራቸውና በዋነኛነት ወላጆች፣ እኩዮች እንዲሁም መምህራን፣ የመማሪያ መጽሀፍት ፣የትምህርት ቦታዎች፣ድጋፍ ሰጪ ነገሮችና የማስተማር ዘዴዎች እንደሚጠቀሱ ተብራርተዋል፡፡
- ❖ የተማሪዎች ግላዊ አመለካከት ፣ የመምህራን ጸባይ፣ የእኩዮች ተጽኖ፣ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ሁኔታ፣ የትምህርት ቤቶች ፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ ዲጋፍ ሰጪ ሁኔታዎችና የማስተማር ዘዴዎች ተላውጦችንና ስልሳ አራት ጥያቄዎችን የያዘ መጠይቅ ለ230 ተማሪዎች ተበትኖ የተሰበሰበው መረጃ ውጤትና ማብራሪያው በምዕራፍ አራት ቀርቦዋል፣ በስታቲካዊ ስሌትና ንጽጽርም ታይቶዋል፡፡
- ❖ በቃለ መጠይቅ አማካኝነት ተጨማሪ መረጃዎች ከመምህራን ተሰብስበዋል፡፡ መረጃዎቹ እንደ አስፈላጊነታቸው ከተማሪዎች ምላሽጋር እየተነጻጸሩ ቀርበዋል፡፡
- ❖ ከተማሪዎች የተገኙ አንዳንድ መረጃዎችን በአይን አይቶ ለማረጋገጥ በት/ቤቶች ጊቢና በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ትምህርት እየተከናወነ ምልከታ ተደርገዋል፡፡ በምልከታ የተገኙ መረጃዎችን ከተማሪዎች ምላሽ ጋር እየተነጻጸሩ ተብራርተዋል፡፡ ከነዚህ ሁሉ ተግባራት በኃላ የተጠቀሱት ጥያቄዎች ያገኙት መልሶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በሰኮሩና ደነባ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ዘንድ አማርኛ ቋንቋና የቋንቋው ትምህርት ተቀባይነቱ በጣም ጥሩ ነው፡፡ ጥቂት የሚጠሉና የሚንቁ ተማሪዎች መኖራቸው

ቢረጋገጥም አብዛኛዎቹ የሰኮሩና የደነባ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች አማረኛ ቋንቋ ና የቋንቋውን ትምህርት ይወዳሉ፡፡

2. ወላጆች፤ የተማሪው እኩዮች በአማረኛ ቋንቋ ላይ አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ሲሆን ተማሪዎችም ቋንቋውን እንዲማሩ ይደገፋሉ፡፡ በተዛማጅ ጽሁፍ ክላሳ እንደተመለከትነው ወላጆች ፣ እኩዮች ቋንቋውን የሚጠሉና የተማሪዎችን መማር የማይደግፉ ቢሆን ኖሮ ተማሪዎቹም ባልወደዱት ነበር፡፡ አሁን ግን ተመሳሳይ ሀሳብ በመገኘቱ ጽሑፉ መረጃዎችና አጥኚው የሰበሰባቸው መረጃዎች ተጣጥመዋል ማለት ነው፡፡

3. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በችሎታቸው ፣በትምህርት አቀራረባቸውና በጠባያቸው በጥሩ ሁኔታ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው፡፡ በተዛማጅ ፅሁፍ ክለሳ የቋንቋ መምህር ተጽህና ከፍተኛ እንደሆነና ተማሪዎች መምህሩን ከጠሉ የቋንቋውንም ትምህርት እንደሚጠሉ ተረድተናል፡፡ በዚህ ጥናት ግን መምህሩንም ሆነ የቋንቋውን ትምህርት አልጠሉም፡፡

4. የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ተቀባይነቱ መካከለኛ ነው፡፡ መጽሀፉ ብዙዙ ድክመቶች እንዳሉበት ከመምህራን የተጠቀመ ሲሆን ካለፈው መጽሀፍ የተሻለ መሆኑ አልተዘነጋም፡፡ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው የተወሰኑ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉበት፡፡

5. ት/ቤቶችና መማሪያ ክፍሎች ፣ እንዲሁም ድጋፍ ሰጪ ነገሮችና የማስተማር ዘዴዎች፣ ተማሪውን ወደ ቋንቋ ትምህርት ለመሳብ እንዲችሉ መሟላት ከሚገባቸው ነገሮች ከሀገሪቱ አቅም ማነስ የተነሳ ያልተሟሉ ቢኖሩም መሰረታዊ የሆኑ ነገሮች ደግሞ አልታጡም፡፡ በተማሪ ብዛት ይጨናነቅ እንጂ ክፍሎች፣ወንበሮች፣ሰሌዳዎች እቤተ-መጽሀፍት ወዘተአሉን፡፡ ይህ በተማሪዎች ምላሽና በአጥኚው ምልከታ የተረጋገጠ ሲሆን ችግሩ ጎልቶ ተማሪዎች ትምህርቱን እንዲጠሉት አላደረገም፡፡

እነዚህ አምስት ተናጠላዊ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው አብይ የጥናቱን አላማ ከግብ ያደርሳሉ፡፡በዚህ መሰረት ውጤቱ ሲጠቃለል አብዛኛዎቹ የሰኮሩና የደነባ ት/ቤት ተማሪዎች በአማርኛ እና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አዎንታዊ አመለካከት አላቸው፡፡

## 5.2 ግኝት

ቀጥለን ከተማሪዎችና ከምምህራን ምላሾችና ከአጥኚው ምልከታ የተጠናከሩትን ግኝቶች ጠቅለል አድርገን እናቀርባለን፡፡

1. አብዛኞቹ የሰኮሩና ደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን አይንቁም፣ አይጠሉም፤ ይልቅስ ይወዳሉ፤ መማር ይፈልጋሉ፡፡
2. አብዛኞቹ የሰኮሩና ደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በስፋት ይጠቀማሉ፤ ሲያነቡና ሲያዳምጡም ከሌሎች ቋንቋዎች ይልቅ በአማርኛ ሲሆን ይገባቸዋል፡፡
3. አብዛኞቹ የሰኮሩና ደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አማርኛ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን አይፈልጉም፡፡
4. የሰኮሩና ደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ልቦለድን ማዳመጥ፣ ቅኔንና ምሳሌያዊ አነጋገሮችን መማር እንዲሁም ውይይት፣ ክርክርና ጭውውት ይበልጥ ያስደስታቸዋል፡፡
5. አብዛኛዎቹ የሰኮሩና ደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ወላጆቻቸው አማርኛን ይወዳሉ፣ ልጆቻቸውም በአማርኛ ትምህርት ላይ ያላቸውን ዝንባሌ ይደግፋሉ፡፡ በተጨማሪም ልጆቻቸው አማርኛን በቤት ውስጥ ቢናገሩበት እና ከፍተኛ ትምህርት ቢገፉበት አይቃወሙሙም፡፡
6. ብዙዎቹ የሰኮሩና ደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ መምህራን ጥሩ ጠባይና በቂ እውቀት ያላቸው ሲሆን ቋንቋውን በደንብ ያስተምራሉ፡፡ ተማሪዎቻቸውም አማርኛን እንዲወዱና በፍላጎታቸው መሰረት እንዲማሩ ይመክራሉ፤ ያበረታታሉ፡፡
7. የዘጠነኛ ክፍል የመማሪያ መፅሀፍት ለትምህርት እንዲመች ሆኖ ያልተከፋፈለና ስእላዊ መግለጫ የሌሉት ቢሆንም ብዙዎቹ ተማሪዎች ምንባቦቹንም ሆነ ማንበቡን እንዲሁም መጽሐፉን አይጠሉም፡፡ መጽሐፉ ለሁሉም ተማሪዎች

የተዳረሰ ቢሆንም አባሪዎችንና የቋንቋ ዘርፎችን ሁሉ አመጣጥኖ ስላልያዘና ያለአስተማሪ ተማሪን መምራት ስለማይችል ብቃት ይጎድለዋል፡፡

8. የሰኮሩና ደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማረኛ ትምህርት በልዩ መረጃ መሳሪያና በተለያዩ ዘዴዎች አይቀርብም፡፡

9. የሰኮሩና ደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛን ትምህርት የሚያግዝ ክበባትን አላቋቋሙም፤ ወቅታዊ ጋዜጦችና መጽሔቶችን በመከታተል ገዝተው አያውቁም፡፡

10. የሰኮሩና ደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አማርኛ መማር የሚፈልጉት፣

- ትምህርቱ በልቦለድ ጽሁፎች፣ በጋዜጦችና በመጽሄቶች ተደግፎ ሲቀርብ ፣
- ቅኔያዊ ፣ ምሳሌያዊ፣ ዘይቤያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮች እንዲተኮርባቸውና የሰዋሰው ትምህርት እንዳይከብድ ሆኖ በልዩ ዘዴ ሲቀርብ ፣
- ትምህርቱ በቀልድና በድራማ እንዲሁም በልዩ መረጃ መሳሪያ ተደግፎ ሲቀርብ ነው፡፡

## 5.3 አስተያየት

አጥኚው በጥናቱ ግኝት መሰረት የሚከተሉትን አስተያየቶች ያቀርባል፡፡

አንድ ትምህርት እንዲወደድ ከሚያደርጉት ነገሮች ዋነኞቹ የተማሪዎችን ደረጃና ፍላጎት መጠበቅ ናቸው፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከሚቀርቡት ርእሶች ተማሪዎች እንዲተኮርበት የፈለጉት ፣ ልቦለድ ጽሁፎችን ነው፡፡ ስለዚህ የስርአተ ትምህርት ባለሙያዎች በዝግጅት ወቅት ልዩ ትኩረት ቢሰጣቸውና ልቦለድ ፅሁፎች ለተለያዩ የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ማስተማሪያ ሆነው ቢቀርቡ ጥሩ ነው፡፡ ምክንያቱም የልቦለድ ታሪክ ስለሚስባቸው ተማሪዎች ለማንበብ፣ ለማዳመጥና ለመናገር ደስ ይላቸዋል፡፡ በዚህም የማንበብ የማዳመጥና የመናገር ክህላቸውን ያዳብራሉ፡፡ ልቦለድ ጽሁፍን በተወሰነ ገጽ አሳጥሮ በመጻፍ ወይም እሱን የመሰለ ሌላ ልቦለድ ጽሁፍ እንዲጽፉ በማድረግ የፅሁፍ ክህላቸው እንዲዳብር ማድረግ ይቻላል፡፡በተጨማሪም ሰዋሰዋዊ ትምህርቶችን ማለትም ልዉ ልዉ ቃላትንና ጥያቄዎችን ሀረጎችንና አረፍተ ነገሮችን፣ ስሞችን፣ግሶችን፣ ቅጽሎችን ወዘተ በልቦለድ ጽሁፎች ማስተማር ይቻላል፡፡ ቅኔያዊ፣ምሳሌያዊ፣ዘይቤያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮችን በልቦለድ ጽሁፍ ውስጥ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ልቦለድን ተማሪዎች እስከወደዱት ድረስ ለሁሉም የአማርኛ ቋንቋ ዘርፎች የማስተማሪያ መሳሪያ አድርጎ መጠቀም የበለጠ ውጤት ያስገኛል፡፡ ጥቂት አማርኛን የሚጠሉ ተማሪዎችም ‹‹ ልቦለድ ያልሆነ ጽሁፍ ስለሚበዛ ነው የጠላነው›› ስላሉ፣ ከላይ እንደተገለጸው ፣ልቦለድ ጽሁፍ ከተተኮረበት እነዚህ የሚጠሉትም ይወዱታል ማለት ነው፡፡

አብዛኛዎቹ የሰኮሩና ደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ጥሩ ጠባይ፣ በቂ እውቀትና፣ ጥሩ አቀራረብ ያላቸው ቢሆንም ጥቂቶቹ የተማሪዎችን ፍላጎት ጠብቀው የሚያቀርቡ አቀራረባቸውም የማይስብና የማይማርክ፣በመማሪያ መፅሀፉ ላይ የግል ጥረታቸውን የሚያክሉና ለተማሪዎች በቂ የጥያቄ እድል የማይሰጡ ናቸው፡፡በጣም ጥቂቶቹ ደግሞ የሰጡትን የክፍልና የቤት ስራ የማያርሙ፣ ሳይዘጋጁ ክፍል የሚገቡ፣ ተማሪዎችን የሚያንቋሽሹና ቁጡና ተሳዳቢዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የተጠቀሱ የመምህራን ድክመቶች ለቋንቋ ትምህርት መጠላት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ስለሚችሉ በስራ ላይ ያሉት በሙያ ማሻሻያ ስልጠና ፣ ገና ማሰልጠኛ ውስጥ ያሉት ደግሞ በሚሰጣቸው የሙያ ትምህርቶች አማካኝነት ከአንድ የቋንቋ መምህር የሚጠበቁ ጥያቄ ግዴታዎችና ስለ ተማሪዎች አያያዝ ሥነ-ልቦናዊ ዕውቀቶች በቂ ስልጠናዊ ዕውቀቶች በቂ ስልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡

ስለዚህ ትምህርት ሚኒስቴር፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚያሰለጥኑ ኮሌጆች ሁሉ በስልጠና ላይ ልዩ ትኩረት ቢሚያደርጉ መልካም ነው፡፡ ይህ ከሆነ በቋንቋውና ከትምህርት ላይ የሚታየው አዎንታዊ አመለካከት እየጎለበተ ይሄዳል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰልቺና አስጠሊታ እንዳይሆን በተገቢው መረጃ መሣሪያዎችና በልዩ ልዩ የማስተማር ዘዴዎች መቅረብ አለበት፡፡ ስለዚህ ት/ቤቶች ለመረጃ መሰሪያዎች ዝግጅት የሚሆኑ ማቴሪያሎችን ማቅረብ ሲኖርባቸው፣ መምህራን ደግሞ በአግባቡ ሰርተው ስራ ላይ ማዋል ይኖርባቸዋል፡፡

ከተማሪዎችና፣ ከአብዛኛው መምህራን በተገኘው መረጃ መሰረት የአስራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ብዙ ጉድለቶች አሉበት፡፡ ምንባቦቹም ሆኑ የአቀራረብ ስልቶቹ ተማሪዎችን የመሳብ ሀይል የላቸውም፡፡ አሁን በስራ ላይ ያሉት የአስራ አንደኛና ሌሎች የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍት ልቦለድ መጽሀፍትን በርከት አድርገው፣ የቋንቋ ዘርፎችን አመጣጥነው፣ ለአቀራረብ በሚያመችና መሚማርክ መልክ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ከሆነ መፅሀፍቱ ይወደዳሉ፤ መፅሀፍቱ ከተወደዱ ደግሞ የቋንቋውም ትምህርት ይወደዳል፡፡

አዘጋጆችን በተመለከተ በስራው ርቀው ያሉ ጥቂት የቢሮ ባለሙያዎች ብቻ ከሚያዘጋጁት፣ ልምድና ብቃት ያላቸው መስራት በልዩ መስፈርት ተመርጠው፣ በቂ ጊዜና ባጀት ተመድቦለት ከቢሮ ባለሙያዎችም ጋር እየተወያዩ ቢያዘጋጁ መልካም ነው፡፡

አብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መማሪያ ክፍሎች ከሚገባው በላይ በተማሪዎች የተጨናነቁና መቀመጫውም የታጣበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህ ደግሞ ለቋንቋ ትምህርት ምቹ አይደለም፡፡

ተማሪዎችን ለመቆጣጠር፣ የሁሉንም ደብተሮችና ስራዎች በሚገባ ለማየትና ለማሳተፍ ችግር ነው፡፡ ስለዚህ መንግስትና ሕዝቡ ተረዳድተው የመማሪያ ክፍሎችን ቁጥር መጨመርና በየክፍሉ ያሉት የተማሪዎች ብዛት ከስልሳ እንዳይበልጥ ጥረት ማድረግ /ይህ የሀገሪቱ ድህነት አኳያ የተሰጠ አስተያየት እንጂ ቴዳጎጂካዊ በሆነ መልኩ ከታየ የአንድ ክፍል የተማሪ ብዛት ከአርባ መብለጥ የለበትም፡፡/

ተማሪዎች ሁል ጊዜ ለክፍሉ ከተመደበው መጽሀፍ ብቻ ከሚማሩ መምህራን ከተለያዩ ጋዜጦችና መፅሔቶች ወቅታዊ ጉዳዮችን እየፈለገ በመጨመር ቢያቀርብ ጥሩ ነው፡፡ ሁል ጊዜ አንድ አይነት ምግብ ብቻ መመገብ እንደሚያሰለች ሁሉ ተማሪዎች በእጃቸው ከያዙት መጽሀፍ ብቻ መማራቸው ብቻ እንዳያሰለቻቸው ለለውጥ ያህል ማደባለቅና ወቅታዊ ሁኔታዎችን ማሳወቅ ጥሩ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አዎነወታዊ አመለካከት እየጨመረና እየጎለበተ ይሄዳል፡፡

ት/ቤቶች የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት የሚያግዝና የሚያጠናክሩ ክበባትንና ፕሮግራሞችን ማደራጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ለምሳሌ የስነ ጽሁፍ ክበብ፣ የጋዜጠኝነት ክበብ፣ የድራማ ክበብ፣ የውይይትና የክርክር ፕሮግራሞች፣ ወዘተ.በየት/ቤቶች ተቋቁመው በሚገባ ተግባራዊ ቢሆኑ የአማርኛን ትምህርት ማገዝ ብቻ ሳይሆን ትምህርቱም እንዲወደድ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

## ዋቢ መፃህፍት

Abraham Demoz. 2009. European loan words in an Amharic. daily news paper. Langus in Africa. Cambrige.

Alfred, N, smith. 2009. "The importance of attitude in foreign languge learning". English Teaching forum. Vol. 10, No. 1, page 15-20.

Allwright, L. 2011. "What do we want teaching materials for?" KLT Journal vol. 36, No. 1 page 5-8.

Anderson Anders, Norrl. 2012. Multilingualism and attitude: an xplorative descriptive study among secondary school students in Ethiopia and Tanzania. Uppsala university.

Arb Desta. 2013. Elements of General Methods of Teaching. Addis Ababa: Addis Ababa university.

Bender, M.L. et al (eds). 2014. Language in Ethiopia. London: Oxford university press.

Bowntree, B. 2015. Educational technology in curriculum development. London: Harper and Row publishers.

Brumfit, C.J. and Robert, J. 1966. Introducation to language and language teaching. New York: Mc Graw Hill Book campany.

Cailods, Fled. 1989. The prespects for educational planning. A workshop organized IIEP on the Occasion of its XXV$^{th}$ Anniversary: paris imperimerie Gauthiervillars.

Cerroll, B. John. 1965. "The contributions of phychological theory and educaioal reassearch to the teaching of foreign language". Modern language journals vol. 49, No. 5 page 273-281.

Chastain Kenneth. 1988. Developing second language skills: Theory and practice. Newyork: Harcourt Brace Jovanovich, publishers.

Coombs, P.H. 1968. The world educational crisis. London: Oxford university press.

Cooper, R.L. 1976. “Governmet language policy” in bender, M.L. et al (eds) 1976. Laugage in Ethiopia. London: oxford university press. Page 187—190.

Cunningworth Alan. 1984. Evaluating and selecting EIT teaching materials. Oxford: Heinmann educational Books Lt.

Dsalegn Chalchisa. 1995. “Assessment of the condition of research in educational testing” Proceedings of the national workshop on. Stregnthening Educational research. Institute of educational research. Addis Ababa Univeristy. Page 239-252.

Dubin, Frida. 1990. Course design programs and materials for language teaching. Cambride: Cambridge university press.

Dubin, Frida and Olshtain, Elite, 1980. Course design developing programs and materials for language learning. Cambridge:; Cambridge university press.

Dunhill. 1964. Discipline in the Classroom. London: university of London press Ltd.

Dunopal. 2009. Beghing English with young children. London: Macmilan publishers.

KLY, M. Christopher. 1986. “An analysis of Discomfort, risktaking, socialbility, and motivation in the L2 “Language learning vol. 36, No. 1 page 1-25.

Perguson Charles A. 2011. A Sociolinguistic survey of language and attitude in Ethiopia. Washington D.C. George Town university.

Genesee Fred, Rogers Pierre, and Holobow Naomi. 2009. “the Social psychology of secord language learning: another point of View”. Language learning vol. 33, No. 2, page 209-224.

# አባሪዎች

## ጂማ ዩኒቨርስቲ

## የድህረምረቃ ትምህርት ቤት

## የአማርኛ ቋንቋና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል

በጂማ ዞን በሰኮሩ ወረዳ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በአማረኛ ትምህርት ቋንቋ ላይ ያላቸው አመለካከት / Attitude/

*ለማጥናት የተዘጋጀ መጠይቅ*

*የመጠይቅ ዓላማ- ተማሪዎች በአማረኛ ና በአማረኛ ትምህርት ቋንቋ ላይ ያላቸው አመለካከት / Attitude/ በጥናት አረጋግጦ ጠቃሚ አስተያየት ለማቅረብ ነው*

*ይህ መጠይቅ በተማሪዎች ብቻ የሚሞላ ሲሆን አምስት የተለያዩ ጉዳዮችን ለመመልከት ያለመ ሲሆን እነሱም፤-*

1. *የተማሪዎች ግላዊ አመለካከት*
2. *የእኩዮች /peers/ አመለካከት*
3. *የአማረኛ ቋንቋ መምህር ጠባይ*
4. *የአማረኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ሁኔታ*
5. *የትምህርት ቤቶች ፤ የመማሪያ ክፍሎች፤ ዲጋፍ ሰጪ ሁኔታዎችና የማስተማር ዘዴዎች ናቸው፡፡*

*መጠይቁ ሲሞላ ስም አይፃፍም፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዳችሁ ከግላዊ አመለካከታችሁ አኳያ የምትሰጡት መልስ በምስጥር የሚጠበቅ ስለሆነ ምንም ሳትፈሩ ትክክል መስሎ የታያችሁትን እንድትመልሱ በትህትና እጠይቃለው፡፡*

ስለትብብራችሁ በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

**አጥኚው**

*ሀምሌ* 2010

**ጂማ**

## ስለራሳችሁ ና ስለቤተሰባችሁ የሚፈለግ መረጃ

### *መመሪያ*

እያንዳንዱን ጥያቄ በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ በጽሁፍ መልስ ለሚፈልጉ ጥያቄዎች በጽሁፍ እንድታሰፍሩ ና ከጽሁፍ ውጭ ያሉትን ሌሎች ጥያቄዎች የራይት ምልክት ብቻ በማድረግ እንድትሞሉ በአክብሮት እጠይቃለው፡፡

ሀ. ስለራሳችሁ

ት/ቤት---------------------------------------------------------- ክፍል------------------------------

ፆታ--------------- ዕድሜ----------------------- ሐይማኖት-------------------------------------

የትውልድ ቦታ------------------------------------ አሁን ምትኖርበት/ሪበት ወረዳ

አፍ መፍቻ ቋንቋ---------------------------------አሁን የምትናገረው/ሪው ቋንቋ ወይም

ቋንቋዎች -----------------------------------------------------------

## አባሪ “ሀ”

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | መወሰን ያስቸግረኛል | አልስማማም | ፍጹም አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | በአማረኛ ቋንቋ ትምህርት ገፍቼ ጋዜጠኛ ና ደራሲ መሆን ፈልጋለው | | | | | |
| 2. | ግዲ ሆኖብኝ እንጂ የአማረኛ ቋንቋን መማር አልፈልግም | | | | | |
| 3. | አብዛኛዎቹ የምማራቸው የአማረኛ ቋንቋ ትምህርት ከፍላጎቴ ጋር ይጣጣማሉ | | | | | |
| 4. | የአማረኛ ቋንቋ ያስጠላኛል | | | | | |
| 5. | የአማረኛ ቋንቋ ተናጋሪ ብሔረሰቦችን አከብራለው | | | | | |
| 6. | ብዙ ግዜ የአማረኛ ትምህርት ውጤት ዝቅተኛ ነው | | | | | |
| 7. | ሳነብና ሳዳምጥ ከሌሎች ቋንቋዎች ይልቅ በደንብ የሚገባኝ በአማረኛ ቋንቋ ሲሆን ነው | | | | | |
| 8. | ጓደኞቼ አማርኛ ቋንቋን ይጠላሉ | | | | | |
| 9. | ጓደኞቼ ከሌሎች ቋንቋዎች ይበልጥ አማርኛን በስፋት ይጠቀማሉ | | | | | |
| 10 | ጓደኞቼ የአማርኛ ትምህርት ቀላል ነው | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | እያሉ ይንቃሉ | | | | | |
| | **የአማርኛ ቋንቋ መምህር ጠባይ፣ ችሎታና አመለካከት** | | | | | |
| 11 | መምህሩ ተማሪዎች አማርኛንና የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት እንዲወዱ ጥረት ያደርጋል | | | | | |
| 12 | መምህሩ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በቂ እውቀት የለውም | | | | | |
| 13 | መምህሩ የተማሪዎቹን ተሳትፎ የሚቀሰቀስ ማራኪ አቀራረብ አለው | | | | | |
| 14 | መምህሩ ተማሪዎችን የሚያንቋሽሽ ቁጡና ተሳዳቢ ነው፡፡ | | | | | |
| 15 | መምህሩ የግል ጥረቱን እያከለ የቋንቋ ችሎታዎችን /ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ/ በሚገባ ያለማምዳል | | | | | |
| 16 | መምህሩ ብዙ ጊዜ ሳይዘጋጅ ክፍል ይገባል | | | | | |
| 17 | መምህሩ ተማሪዎች ከፍላጎታቸው መሰረት ተደስተው እንዲማሩ ያማክራቸዋል | | | | | |
| 18 | መምህሩ ማርክ /ነጥብ/ አሰጣጡ አድሏዊ ነው | | | | | |
| 19 | መምህሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንዲገፉ ያበረታታቸዋል፡፡ | | | | | |
| 20 | መምህሩ አማርኛን እንደማይወዱና ለደሞዝ ሲል ብቻ እንደሚያስተምር ይናገራል | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 21 | መምህሩ ሚሰጠውን የክፍልና የቤት ስራዎች ያርማል | | | | | |
| 22 | መምህሩ ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ በቂ ዕድል አይሰጥም | | | | | |
| | **የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍት ሁኔታ** | | | | | |
| 23 | በትምህርት ቤታችን በቂ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍት አሉ | | | | | |
| 24 | የአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ የተማሪዎችን ፍላጎት አያንጸባርቅም | | | | | |
| 25 | በአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ማራኪ ናቸው | | | | | |
| 26 | የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ማንበብ ያስጠላኛል | | | | | |
| 27 | በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ምንባቦች በግልጽ ቋንቋ የቀረቡ ናቸው | | | | | |
| 28 | የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ በስዕላዊ መግለጫዎች ስላልታጀበ አይስበኝም | | | | | |
| 29 | በአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች ጥሩ ናቸው | | | | | |
| 30 | መጽሀፉ የቃላትን ዝርዝር ከነትርጉማቸው የሚያሳ አባሪ ስለሌለው ብቃት የለውም | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 31 | መጽሀፉ አስተማሪ ባይኖርም ተማሪውን መምራት ይችላል | | | | | |
| 32 | መጽሀፉ የቋንቋውን ትምህርት ዓላማዎች አያንጸባርቅም | | | | | |
| 33 | መጽሀፉ የቋንቋ ዘርፎችን ሁሉ አካቶ ያቀርባል | | | | | |
| | **ትምህርት ቤቶችን፣ መማሪያ ክፍሎችን፣ ድጋፍ ሰጪ ነገሮችንና የማስተማሪያ ዘዴዎችን በተመለከተ** | | | | | |
| 34 | በመማሪያ ክፍላችን በቂ መቀመጫ ስላለ ተዝናንተን እንቀመጣለን | | | | | |
| 35 | የአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በአጉል ሰዓት ላይ ስለሆነ የመማሪያ ክፍሉ ሙቀት ያስጨንቀናል | | | | | |
| 36 | በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የመማሪያ ክፍላችን ስነ ስርዓት በሚገባ ይጠቃል | | | | | |
| 37 | የክፍላችን ጥቁር ሰሌዳ የተበላሸ ስለሆነ ጽሁፍ አይቀበልም | | | | | |
| 38 | የአማርኛ መማሪያ ክፍላችን ብርድ በማያስገባ ተስማሚ ቦታ ላይ ይገኛል | | | | | |
| 39 | የአማርኛ ትምህርት በልዩ መርጃ መማሪያ ቀርቦልን አያውቅም | | | | | |
| 40 | የአማርናን ትምህርት በተለያዩ ዘዴዎች | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ስለምንማር ይስበናል | | | | | |
| 41 | የአማርኛ ትምህርት የአቀራረብ ዘዴው ትምህርቱን እንዲጠላ አድርጎናል | | | | | |
| 42 | ትምህርት ቤታችን ወቅታዊ ጋዜጦችንና መጽሄቶችን ስለሚያቀርብልን ለአማርኛ ትምህርት እተበረታታን ነው | | | | | |
| 43 | በትምህርት ቤታችን ቤተ መጽሐፍት የአማርኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላት ባለመኖራቸው ተቸግረናል | | | | | |

## አባሪ “ለ”

### ለመምህራን የሚቀርቡ ቃለመይቃዊ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ምን ዓይነት አመለካከት አላቸው?
2. ተማሪዎች የአማርኛ ትምህርት እንዴት ይቀበላሉ?
3. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ትልቁ ችግር ምንድነው?
4. አሁን በስራ ላይ ስላለው የአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ምን አስተያየት አሉዎት?
5. ወደፊት የሚዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት በማንና እንዴት ቢዘጋጁ ይሻላል?
6. ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንዲማረኩና በደስታ እንዲማሩ ምን መደረግ አለበት?